# ቁም ነገር





## ቁም ነገር
## የእርስዎና የቤተሰብዎ መፅሔት

# 200 ኛ ልዩ ዕትም

እየመጣ ነው!

ምርትና አገልግሎትዎን ያስተዋውቁ!

ቁም ነገር መፅሔት በቅርብ ጊዜ ሳምንታዊ! !

ፀሓፍት አዝናኝ፤ አስተማሪና ቁም ነገር አዘል የብዕር ትሩፋታችሁን እንድታቀርቡ ትጋበዛላችሁ!

ይቀጥላል...

# ማውጫ


13






16

30



7

ይልቅ ወሬ ልንገርህ፡- ስለ ሀና ላላንጎ የመደፈር ድራማ!

14

የጉዞ ማስታወሻ፡- ከአዲስ አበባ እስከ የከሬን

24

መሠረታችንን ማን ይሆን የቀማን!?

36

‹‹አመለካከታችን ካልተለወጠ ህግ ብቻውን ሁሉን ነገር ሲያስፈፅም አይችልም››


# ደብዳቤዎቻችሁ

## ‹የዩኒቨርሲቲዎቻችን ገመና በደንብ ይፈተሽ›

ባለፈው ቁም ነገር መፅሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር 191 ላይ ስለ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ህይወት ያወጣችሁትን ጽሑፍ ተመልክቼዋለሁ፡፡ በእውነቱ የዩኒቨርሲቲዎቻችን ገመና ከዚህ ከፍ ባለ ሁኔታ መፈተሽ ያለበት ይመስለኛል፡፡ በዝሙት አዳሪነት ስራ ላይ የተሰማሩ ሴቶች ሳይቀሩ ‹በስራችን ገቡ› በማለት ሰላማዊ ሰልፍ እስከመውጣት የደረሱባቸውን ተማሪዎች ጉዳይ ተማሪዎችና መምህራን እንዲሁም ወላጆች በሚገባ ሊወያዩበት ይገባል እላለሁ፡፡ በተለይም የዩኒቨርሲቲዎቹ አስተዳደሮች ዝምታን ከመምረጥ ተጨባጭ መረጃ ለህዝቡ ሊሰጡ ይገባል ባይ ነኝ፡፡ መንግስትም በመፅሔቱ ላይ እንደተጠቀሰው የፖሊሲና የስትራቴጂ ስልጠና ብሎ ለአንድ ወር ያህል ተማሪዎቹን ከሚያደክማቸው መሰረታዊ የሥነ ምግባር ትምህርትና የዩኒቨርሲቲ ህይወትን የተመለከቱ ስልጠናዎችን ቢሰጥ ችግሩ ሊቃለል ይችላል እላለሁ፡፡

መምህር ዳመና ቱሉ/ከአርሲ ነገሌ/

## ‹የዶክተሩ ጥንካሬ ለሌሎች አርአያ ነው›

የቁም ነገር መፅሔት ቋሚ አንባቢ ነኝ ለማለት እችላለሁ፡፡ ባለፈው ቁጥር 191 ዕትማችሁ ላይ ስለ ዳኑ የአጥንት ህክምና ማዕከል ባለቤት ዶክተር ኤልያስ መሐመድ ጋር ያደረጋችሁትን ቆይታ አንብቤያለሁ፡፡ ዶክተሩ ከተማሪነት ደረጃ ተነስተው ያስተማራቸውን ህዝብ በአጥንት ህክምና ለመርዳት ይህንን የመሰለ ግዙፍ የህክምና ተቋም ማቋቋም መቻላቸው ያስመሰግናቸዋል፡፡ ጥንካሬያቸውና የስራ ፍቅራቸው ለሌሎች የህክምና ሰዎች አርአያ ነው ለማለት እችላለሁ፡፡ ነገር ግን የዳኑ የህክምና ማዕከል የት ቦታ እንደሚገኝ አልገለፃችሁምና በሚቀጥለው ዕትማችሁ ላይ ብትነግሩን ህክምናውን ልናገኝ እንችላለን፡፡

ወ/ሮ ወይንሸት ዓለሙ/ከሰሜን ማዘጋጃ/

## ‹እውቅና የሌላቸው ዩኒቨርሰቲዎች ጉዳይ እልባት ቢሰጠው›

ባለፈው ቁም ነገር 191 ዕትማችሁ ላይ በወሬ ልንገርህ ዓምድ ላይ የእውቅና ፈቃዳቸው የተሰረዘባው ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች የፃፋችሁትን አንብቤያለሁ፡፡ በሀገራችን የግል ኮሌጆች የመማር ዕድሉን ላላገኙ ተማሪዎች ጥሩ ዕድል ቢሆንም በአቋራጭ ገንዘብ ለማግኘት የሚሰሩ ኮሌጆች እንዳሉ ግልፅ ነው፡፡ በእርግጥ ለእነዚህ ሁሉ ህገ ወጥ ኮሌጆች መበራከት ተጠያቂው ራሱ መንግስት ነው፡፡ የሆነ ቤት ተከራይተው በህገ ወጥ መንገድ ተማሪዎችን ሲመዘግቡ ዝም ብሎ ተማሪዎች ተምረው ሊመረቁ ሲሉ ህጋዊ አይደሉም ማለት አንድ ሀላፊነት ከሚሰማው የመንግስት ተቋም የሚጠበቅ አይደለም፡፡ እኔ ልጄን በሴንትራል የጤና ኮሌጅ አስተምሬ ሁለት ዓመት ተምራ አሁን ተዘግቷል ተብሏል፡፡ በጣም ያሳዝናል ፡፡ ለእነዚህ ተማሪዎች መፍትሔ እንደሚሰጥ እጠብቃሁ፡፡

ታምሩ ከተማ/ከናዝሬት/

## ‹ የአፍሪካ ቱጃር መሪዎች እነዚህ ብቻ ናቸውን›

በአፍሪካ ከሃያ ዓመታት በላይ በስልጣን ላይ ያሉ መሪዎች ቁጥራቸው በጣም ብዙ ነው፡፡ ለረዥም ዓመታት በስልጣን ላይ መቀመጥ በአፍሪካ ገንዘብ ለመመዝበርና ለመዝረፍ እድል እንደሚፈጥር ግልፅ ነው፡፡ ባለፈው ዕትማችሁ ያወጣችኋቸው ቱጃሮቹ የአፍሪካ መሪዎች የሀብታቸው መጠን ራሱ አለመታወቁ የዘረፉቸውን መጠን ያሳያል ብዬ አስባለሁና የእኛንም ሀገር ቱጃር ባለስልጣናት በነካ እጃችሁ ብትነግሩን ደስ ይለናል፡፡

ታምርአየሁ ካሴ/ከባህር ዳር

**የሚቀጥለው ዕትም**

**ቁምነገር መፅሔት ቁጥር 193 ታህሳስ 4 ቀን 2007 ዓ.ም ይጠብቁት!**






በቁም ነገር ሚዲያና ኢንተርቴመንት
ኃ/የተ/የግ/ማ ሥር እየታተመ በየ15 ቀኑ የሚወጣ በኪነ
ጥበብና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር መፅሔት

**በ1994 ዓ.ም ተመሰረተ**

13ኛ ዓመት ቁጥር 192

---

**ዋና አዘጋጅ:-** ታምራት ኃይሉ / 0911 23 20 15
የካ ክ/ከተማ ቀበሌ 13/14 የቤት ቁጥር 212
**አዘጋጆች:-** ፍስሃ ጌትነት
- ሳሚ አብ
**ሪፖርተር:-** ትዕግስት ታደለ
**አማካሪ:-** ካሣ ለገሠ (ከ አሜሪካ ቨርጂኒያ)
**ግራፊክስ ዲዛይነር:-** ተክለ ኪዳነ አምባዬ
**ኮምፒውተር ፅሁፍ:-** አለምብርሃን ሃፍቱ
**ሽያጭና ስርጭት:-** ቴዎድሮስ ንጉሴ /0913-887175/
**ሕትመት ክትትል:-** በዛብህ ተክሉ/0911-416800/
**የሕግ አማካሪና ጠበቃ:-** ጳውሎስ ተሰማ
/0911-234441/

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
ቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 17/18 የቤ.ቁ 401
ካሳንቺስ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር ወረድ ብሎ
ምናለ ህንጻ አንደኛ ፎቅ
ስልክ:- 011-5-507410 / ፋክስ:-011-5-507410
ፖስታ:- 25099 ኮድ 1000 አ.አ
ኢሜይል:- kumneger10@gmail.com
አታሚ ፋኖስ ጌት አታሚዎች
ቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 15 ቀበሌ 04 የቤ.ቁ334
ስልክ:- 011-4700324

# ከአዘጋጁ



## ድንዛዜው አልበዛም ወይ መፋዘዙ
## በቃ በሉ አልበዛም ወይ ግድ ማጣት
## ሃላፊነትን መዘንጋት

ድምፃዊት ዘሪቱ ከበደ

ሰሞኑን አንዳንድ ደስ የማይሉ ዜናዎችን ሰምተናል፡፡ የመጀመሪያው በአዲስ አበባ አንዲት የ16 ዓመት ልጃገረድ በአምስት ወጣቶች ተደፍራ ህይወቷ ስለማለፉ ሲሆን ሌላው በሀድያ ዞን ነዋሪ የሆኑ የ55 ዓመቷ ወይዘሮ ‹ቀናሁ› በሚል ስሜት ተነሳስተው የ30 ዓመት የትዳር አጋራቸውንና የ4 ልጆች አባት የሆኑትን ግለሰብ በመጥረቢያ አንገታቸውን በመምታት መግደላቸውን የተመለከተ አሰቃቂ ዜና ነው፡፡ የእኚህን ወይዘሮ ድርጊት ልዩ የሚያደርገው ባላቸውን ከገደሉ በኋላ ጓሮ የእንሰት ማሳ ውስጥ መቅበራቸው እንደሆነ የቴሌቪዥን የፖሊስ ፕሮግራም ዘገባ ያስረዳል፡፡

የዚህ አይነት የሚዘገንን ዜና መስማት ከለመድን ሰነባብተናል፡፡ ከአሁን በፊትም አሲድ ስለደፋ ወጣት፣ አይን በጩቤ ስላወጣ አባወራ፣ ብልት በቢላዋ ስለቆረጡ ባልቴት ወዘተ ሰምተናል፡፡ የአንዳንዶቹ ወንጀሎች አስከፊነትና አደጋው ከባድ ስለነበር ጉዳዩ ወዲያውኑ ወደ ሚዲያዎች ከወጣ በኋላ በሰላማዊ ሰልፍና በትላልቅ ሆቴሎች የፓናል ውይይት ሲታጀብ ተመልክተናል፡፡ ይህንኑ ሰብአዊ ስሜት መሠረት በማድረግም አንዳንዶቹ ለችግሩ መባባስ ዋነኛ ተጠያቂዎች የፍትህ አካላት መሆናቸውን በመጥቀስ የህግ መላላት ውጤት ነው ሲሉ ተደምጠዋል፡፡

ቁም ነገር መፅሄት በዚህ ረገድ የህግ ችግር አለ ብላ አታምንም፡፡ እንደ ጥንቱ የሐሙራቢ ህግ «ዓይን ያወጣ ዓይኑ ይውጣ፤ በመጥረቢያ የገደለም በመጥረቢያ ይገደል» ካልተባለ በቀር የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ በቂና ተመጣጣኝ የቅጣት ድንጋጌዎች አሉት፡፡

ለእንደነዚህ አይነት ዘግናኝ ድርጊቶች መፍትሔው ህግ ብቻ ሳይሆን ነፃና ግልፅ ውይይት ነው፡፡ በመሆኑም ወንጀልን አስቀድሞ የመከላከል ሥራዎች መሰራታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በትዳርና በፍቅር ግንኙነት ውስጥ ችግሮች ሲፈጠሩና አለመግባባቶች ሲከሰቱ ከጠብ በራቀ መንገድ በምን መልኩ በሰላማዊ መንገድ መፍታት እንዳለብን የሥነ ልቦና እና የማህበረሰብ ሳይንስ ባለሙያዎች መድረክ ፈጥረው ህብረሰቡን ሊያስተምሩ ይገባል፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች የሙያ ብቻ ሳይሆን የዜግነትም ግዴታ አለባቸው እንላለን፡፡

ቁም ነገር መፅሔት ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ እንዳለችው የአሁኑ አይነት ዘግናኝ ወንጀሎች ሲፈፀሙ አጥፊዎችን በህጉ አግባብ ማስቀጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ «ለምን ሆነ?» በሚለው ጉዳይ ላይ ከእርግማን ወጥተን በቤተሰብ ጉዳይና በፍቅር አመሰራረት ዙሪያ ላይ በግልፅ ስንወያይ ብቻ ነው ለሌሎች አስተማሪ የሆነ መፍትሄ የምናገኘው፡፡ መገናኛ ብዙሃኖቻችንም ከ18 ሰዓታት የአውሮፓ ኳስ ዘገባ ወጥተው እሴት ለሚጨምሩ የወገኖቻችን ጉዳዮች ትንሽ ጊዜ ሊሰጡ ይገባል እንላለን፡፡

**እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ይባርክ**

ቁም ነገር መፅሔትን በfacebook.com/kumneger magazine ማግኘት ይችላሉ፡፡ ቁም ነገርን ላይክ ያድርጉና ቤተሰብ ይሁኑ!
የቁም ነገር መፅሔት ዕትሞች በwww.afroage.com ድረገፅ ላይ ያገኛሉ!

ያለፈው ዕትም ቁጥር 191




ቁጥር 190




ቁጥር 189






# ሃናና ሀበሻ ‹ፕራንክ›

## ከሄርሜላ እስከ ካሚላት

## ከአበራሽ እስከ ፍሬህይወት- ከሃና እስከ ????

### መነሻ

በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን /ኢቲቪ3/ እና በኢቢኤስ ቲቪ ላይ ከሚቀርቡ የመዝናኛ ፕሮግራሞች መሀከል ‹ጨዋታ› ሐበሻ ፕራንክ ፕሮግራም አንዱ ነው፡፡ በኮንታክት መልቲ ሚዲያ ተዘጋጅቶ የሚቀርበው በዚህ ፕሮግራም ላይ ‹የካሜራ ትኩረት› የተሰኘ የመዝናኛ ትርኢት ይቀርባል፡፡ ከውጪ ሀገር የመዝናኛ ፕሮግራም ላይ ተኮርጆ በሀገር ውስጥ ድንገቴ ትወና በመስራት በስውር ካሜራ ተቀርፆ የሚቀርበው ዝግጅት በማናቸውም ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የህብረተሰባችንን የአስተሳሰብ ደረጃ የት ድረስ እንደሆነ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ፕሮግራም ነው፡፡ ፕሮግራሙን ላልተመለከታችሁና ላላያችሁ ሰዎች ይህ አጭር መግለጫ የፕሮግራሙን ምንነት ያሳያል፡፡

### አንድ

በቅድሚያ ሁለት ወጣቶች/አንድ ወንድና ሴት/ በካሜራው ፊት ይሆኑና ‹አሁን እኔ መንገድ ላይ እቆምና እሷ ዩኒፎርም ለብሳ ከትምህርት ቤት ስትመጣ አስቆማትና አታልፊም ከእኔ ጋር ካልሄድሽ እላታለሁ፡፡ በዚህ ጊዜ በአካባቢው የሚያልፉ ሰዎች ሁኔታውን ተመልክተው ምን እንደሚያደርጉ አብረን እንመለከታለን› በማለት ወደ ትወናቸው ይገባሉ፡፡ ይህን ጊዜ አንድ ስውር ካሜራ ድምፃቸውንና ምስላቸውን በመኪና ውስጥ ሆኖ ይቀርፃል፡፡ ወጣቱ ፀጉሩን አንጨባሮ ዩኒፎርም ለብሳ ደብተሯን ሸጉጣ ከትምህርት ቤት የምትመጣውን ወጣት መንገድ ላይ በማስቆም ‹ዛሬ ከእኔ ጋር ነው የምትውይው› ይላታል ጮክ ብሎ፡፡ ልጅቱም አስቀድማ በተዘጋጀችበት መልኩ መተወን ትጀምራለች፡፡‹ወደ ቤቴ መሄድ አለብኝ፤ አሳልፈኝ እባክህ› እያለች አላፊ አግዳሚውን እየተመለከተች ትናገራለች፡፡ ወጣቱ ግን በአካባቢው ሰዎች ማለፍ ሲጀምሩ‹ሳልፈቅድልሽ ከዚህ

ቦታ እንዳትንቀሳቀሺ፤ ዛሬ ከእኔ ጋር አብረን ሄደን ጫት እንቅማለን፤ ከእኔ ጋር ነው የምትውይው › ይላታል፡፡ ልጅቱ አሁንም እየተነጫነጨች ‹እባክህ ልቀቀኝ ? ወደቤቴ መግባት አለብኝ› ትላለች፡፡ በአካባቢው የሚያልፉ ሰዎች የልጅቱንና የወጣቱን ጭቅጭቅ ቢሰሙም ገልመጥ ብለው ያልፉሉ፡፡ በዛች አጭር የትወና ደቂቃ በአካባቢው ከሚያልፉ አስር ሰዎች ስምንቱ ወጣቱ የልጅቷን እጅ ይዞ ከእኔ ጋር ካልሄድሽ ሲላት ‹ተው እንጂ› የሚል የለም ተገላምጦ አይቶ ከማለፍ ውጪ፡፡ ምናልባት አንድ ሁለቱ ቆም ብለው ጭቅጭቁን ከተመለከቱ በኋላ‹ ምንድነው ያለፍላጎቷ የምታደርጋት?› ለማለት ሲከጅሉ ይታያል፡፡ ነገር ግን ልጁ ጠጋ ብሎ ‹ምንድነው?› ብሎ ሲያፈጥባቸው አንገታቸውን ጠምዝዘው ሲሄዱ ይታያል፡፡ ከብዙ የምንቸገረኝ ትዕይንት በኋላ ግን ‹ሆን ተብሎ የሚሰራ ድንገቴ ትወና በመሆኑ ወጣቶቹ ተቃቅፈው አንድ ላይ ሲሄዱ ይታያል፡፡

## ሁለት

እነዚሁ ወጣቶች ልብስ ቀይረው በመንገድ ላይ ይጓዛሉ፡፡ ወጣቱ ድንገት ወደ ወጣቷ ሄዶ ‹ሞባይልሽን አምጪ!› ብሎ ይቀበላትና ‹ከእዚህ አካባቢ ጥፊ› ይላታል፡፡ ልጅቷ ግን እየተከተለችው ‹ሞባይሌን መልስልኝ እንጂ?› እያለች በአካባቢው የሚያልፉ ሰዎች እንዲሰሙ ጮክ ብላ ትለምነዋለች፡፡ ወጣቱ ግን ወደ ኋላ ተመልሶ ልጅቷን እንደ መማታት እየዛተባት ‹አልሰጥሽም ሂጂ ከዚህ አካባቢ› ይላታል፡፡ በአካባቢው ወጣቱ ሞባይሏን ሲነጥቃት የተመለከቱም ሆኑ ‹ሞባይሌን መልስልኝ› የሚለውን የልጅቱን ጥያቄ ያዳመጡ ሰዎች ‹ ለምንድነው ሞባይሏን የምትሰጣት?› ሲሉ በስውር ካሜራው አይታዩም፡፡ ቆም ብለው ጭቅጭቃቸውን ከሰሙና ከተመለከቱ በኋላ መንገዳቸውን ነው የሚቀጥሉት፡፡ በመጨረሻ ወጣቶቹ በስውር ካሜራ ፊት የሚተውኑ ተዋንያን መሆናቸውን አሳውቀው ተቃቅፈው እስከሚሄዱ ድረስ የዚህ አይነት ትዕይንት በተደጋጋሚ ይታያል፡፡

ይህ ለመዝናኛነት ተብሎ የሚሰራ ትወና የማህበረሰባችንን የ‹ያገነባኛል›ን የሀላፊነት ደረጃ› ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡ ሴቶችን በመንገድ ላይ ማንም ጎረምሳ ‹አታልፊም ›ብሎ ሲያስቆማትና ሲጎትታቸው ‹ለምን?› ብሎ የሚጠይቅ ሰው የለም፡፡ ከሴቶች ጥቃት አንፃር ብቻ ሳይሆን ከልዩ ልዩ ማህበራዊ ችግሮቻችን አንፃር በዚሁ ‹ሀበሻ ፕራንክ/ጨዋታ› በተሰኘው ፕሮግራም ላይ ቀርቦ ተመልክተናል፡፡ አስፋልት ላይ ቆሞ የሚሸና... የመንገድ አካፋይ ብረት ለመሸጥ የሚነቅል ... ከመንገድ ዳር የኔ ብጤ ላይ ሳንቲም የሚነጥቅ... ወዘተ ዝርዝሩ ብዙ ነው፡፡ የተለያዩ ህብረተሰብን የሚጎዱ ተግባራት ሲፈፀሙ ‹ለምን?› ብለው የሚጠይቁና መደበኛ ሥራቸውን ትተው ለሌላው መብት የሚታገሉ ሰዎች የሉም፡፡ ወይም ቁጥራቸው እጅግ ሲበዛ አነስተኛ ነው፡፡

የዚህ አይነት ለማህበረሰቡ ጠቃሚ የሆኑ መልዕክቶች የሚተላለፉበት ፕሮግራም በስፖንሰር እጦት ሲንገታገት መመልከት ደግሞ ሌላው የማህበረሰባችንን የአስተሳሰብ ‹ልምሻ› ማሳያ ነው፡፡ (ከፕሮግራሙ አዘጋጅ ጋር የተደረገውን ቃለ ምልልስ በገፅ 10 ላይ ይመልከቱ )



***********

## የሃና ላላንጎ ጥቃት

ሰሞኑን የማህበራዊ ድረ ገፆችንና የተለያዩ መገናኛ ብዙሃንን አጨናንቆት የከረመው ወሬ የ16 ዓመቷ ታዳጊ ልጃገረድ ሃና ላላንጎ ላይ የተፈፀመው ጥቃትና ከዚሁ ጥቃት ጋር በተያያዘ የደረሰባት ሞት ነው፡፡ዓመታትና ወራትን እያለፈ ከመከሰቱ በቀር የሃና ጉዳይ ቀደም ሲል በሀበሻ ፕራንክ ፕሮግራም ላይ የተመለከትነው የህብረተሰባችን ቸልተኝነት ውጤት አንድ ማሳያ ነው፡፡ የዚህ አይነት አስከፊና የማህበረሰባችንን የሞራል ደንብ የሚጥስ ተግባር ሲፈፀም የአንድ ሰሞን መነጋገሪያ ከመሆን ያልዘለሉ የተለያዩ የጥቃት ሰለባ የሆኑ ሴቶችን እናስታውሳለን፡፡ ወደ ኋላ መለስ ብለን ባለፉት ዓመታት የተከሰቱና የመገናኛ ብዙሃን ትኩረት ያገኙ የጥቃት ሰለባ ሴቶችን ታሪክ ስንመለከት ተመሳሳይ ድርጊቶችን እናስተውላለን፡፡

***********

## የሄርሜላ ታሪክ

የዛሬ 15 ዓመታት ገደማ ሄርሜላ የምትባል ወጣት ‹አፈቀርኩሽ› በሚል ሰበብ አንድ ጎረምሳ መግቢያ መውጫ ያሳጣታል፡፡ ልጅቱ ትምህርቷን እንኳ መከታታል የማትችልበት ደረጃ ላይ ስትደርስ ለቤተሰቦቿ ጉዳዩን ታሳውቃለች፡፡ ቤተሰቦቿም የችግሩ ፈጣሪ የተባለውን አፍቃሪ ወጣት አግኝተው ለማነጋገር ይሞክራሉ፡፡ ከነእርሱ አቅም በላይ ሲሆን ለፖሊስ ያመለክታሉ፡፡ ፖሊስ ወጣቱን ይዞ ቢመረምርም በፍቅር ሳቢያ የሆነ መሆኑን በመገንዘብ ‹አጠገቧ እንዳትደርስ› በማለት በምክር ይለቀዋል፡፡ ወጣቱ ግን ከስህተቱ ከመታረም ይልቅ ሄርሜላን በሀይል የራሱ ለማድረግ ቆርጦ ይነሳል፡፡ በሁለቱ መሀከል የገቡ ቤተሰቦቿንም በገጀራ በማስፈራራት ልጅቱን ሌላ ስጋት ላይ ይጥላታል፡፡ጉዳዩ በኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ቢያዝም መፍትሔ አላመጣም፡፡ ለዓመታት የተፈጠረው ችግር በመገናኛ ብዙሃን ላይ ከቀረበ በኋላ ልጁ ተይዞ ክስ ይመሰረትበታል፡፡ ፍርድ ቤት ቀርቦም ከተፈረደበት በኋላ ‹ሊያመልጥ ሲል › በሚል ምክንያት እዛው ፍርድ ቤት ደጃፍ ላይ በጥይት ይገደላል፡፡ ምንም እንኳ አርቲስት ሰማከኝ በለው ‹አላበድኩም ያገርኝ› የተሰኘ ነጠላ ዜማ ከማውጣቱና ታሪኩ ዳይሬክተር ዮናስ ብርሃነ መዋ ‹ሄርሜላ› የተሰኘ ፊልም ለመስራቱ ምክንያት ከመሆኑ በቀር ጉዳዩ መሰረታዊ የሴትና የወንድ ልጅን የፍቅር ግንኙነት ማስተማሪያ ሆኖ በማህብረሰቡ ውስጥ አልተስተዋለም፡፡ በመሆኑም ሌሎች ዘግናኝ የሴት ልጅ ጥቃት ዜናዎች መሰማታቸው ቀጠለ፡፡

***********

## የካሚላት ታሪክ

ካሚላት መህዲ በ1999 ዓ.ም የገና ዋዜማ ከታላቅ እህቷ ጋር ከምትሰራበት ሱቅ አምሽታ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ገደማ ወደ ቤቷ ስትሄድ አንድ



ሰው ወደ አጠገባቸው መጥቶ አሲድ ፊቷ ላይ ደፍቶ ይሰወራል፡፡ ካሚላት በወቅቱ በደረሰባት የፊት መቃጠል ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባት ሲሆን በሀያት እና በየካቲት 12 ሆስፒታል ህክምና ቢደረግላትም የፊቷ ቆዳ ከ96 ከመቶ በላይ መቃጠሉ በሀኪሞች ይረጋገጣል፡፡ ይህ አስከፊ አደጋ በአዲስ አበባ ብዙሃን መገናኛ ኢቲቪ 2 ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ እስከሚቀርብ ድረስ የካሚላት ጉዳት ሚስጥር ሆኖ ቆይቷል፡፡ ጉዳዩ በመገናኛ ብዙሃን ቀርቦ የአደጋው አስከፊነት ድንጋጤ ከፈጠረ በኋላ በተለያዩ ወገኖች አስተያየቶች መሰጠት ጀመሩ፡፡ ጉዳዩን ፈፅሞታል ተብሎ በካሚላት የተገለፀው ደምሰው ዘርይሁን ከነግብረ አበሮቹ ተይዞ ምርምራ እየተካሄደ መሆኑን ፖሊስ ይፋ አደረገ፡፡

ድርጊቱን ፈፅሞታል የተባለውን ወጣት በተመከለተም ብዙዎች ስሜታዊ ሆነው ‹አውሬ ነው፤ ሊሰቀል ይገባል› ብለው በመገናኛ ብዙሃን ላይ ሳይቀር ሲናገሩ ተደምጧል፡፡ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው የሴቶች ጉዳይ ማህበራትና አመራሮችም ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ በህግ አስፈፃሚ አካላት ላይ ተፅእኖ ለመፍጠርና ከበድ ያለ ቅጣት እንዲፈረድበት ጠየቁ፡፡ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ያለው ወጣት ‹እኔ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ እንደውም ፍቅረኛዬ ነች› ብሎ የፎቶግራፍ ማስረጃዎችን ይፋ እስከሚያደርግ ድረስ (ቁም ነገር መፅሔት 6ኛ ዓመት ቁጥር 62፤ መጋቢት 1999ዓ.ም) በተፈጠረው ድርጊት ዙሪያ ግራና ቀኝ ለማየትና የችግሩን መሰረት ለመመርመር ፍላጎት ያለው አካል አልነበረም ለማለት ይቻላል ጉዳዩ ውሎ ሲያድር ቀደም ሲል የነበረው ስሜታዊነት በጠፋበት በዓመቱ ድርጊቱን ፈፅመውታል የተባሉት ሁለት ወጣቶች የዕድሜ ልክ እስራትና የሃያ ዓመት ፍርድ ተበየነባቸው፡፡ ወጣቶቹ ይግባኝ ጠይቀው የዕድሜ ልክ እስራቱ ወደ ሃያ ዓመት የሃያ ዓመቱ በነፃ እስከሚቀየር ድረስ የካሚላት ጉዳይ አነጋጋሪነቱ ቀጥሏል፡፡


***********

## የአበራሽ ታሪክ

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ አስተናጋጅ /ሆስተስ/ የሆነችው ወ/ሮ አበራሽ ሀይላይ መስከረም 2 ቀን 2004 ዓ.ም ገርጂ በሚገኘው ኮንዶሚኒየም ኪራይ ቤቷ በማግስቱ ወደ ደቡብ ሱዳን ጁባ ለምታደርገው በረራ ልብሶቿን እያስተካከለች ነው፡፡ ከትዳሯ ከተፋታች ገና አራት ወር እንኳን ያልሞላት አበራሽ በተከራየችው ኮንደሚኒየም ቤቷ ይህ ነው የሚባል የቤት ቁሳቁስ ገና አላሟላችም፡፡ ሁሌም በረራ ላይ ጊዜዋን የምታሳልፈው አበራሽ የቤት ሰራተኛ ለመቅጠር ገና አላሰበችም ነበር፡፡ በመሆኑም በዕለቱ ከምሽቱ 11 ሰዓት ገደማ ወደ ቤቷ ገብታ በማግስቱ ከጠዋቱ 12 ሰዓት ላለባት በረራ ቅድመ ዝግጅት ላይ ናት፡፡ ከምሽቱ 4 ሰዓት ገደማ ከቤቷ ደጃፍ አንድ ሰው ደጋግሞ በሯን ይቆረቁራል፤ ግለሰቡ ከደቂቃዎች በፊት ከአጎቷ ቤት የተለየችው የቀድሞ ባለቤቷ አቶ ፍስሀ ታደሰ ነበር፡፡ ከአጎቷ ቤት የተለየችው ግለሰብ ዳግመኛ

ከቀደሙት ጥቃቶችና ከልምዳችን ተነስተን ነገሩን ስንፈትሽ የሃና ጉዳይም ከቀናት በኋላ ይረሳና መደበኛው ህይወት ይቀጥላል፡፡ የሴት ልጅ ጥቃት ጉዳይ በመገናኛ ብዘሃንም ሆነ በማህበራዊ ድረ ገጾች ላይ ትኩረት ተሠጥቶት የሚዘገበው ጥቃቶች ሲደርሱ ነው፡፡

ፍሬህይወት



ቤት ድረስ መምጣቱ ቢያስገርማትም ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ አስቀድሞ ባቀደውና በተዘጋጀበት መሰረት በያዘው ጩቤ ሁለት ዓይኖቿን ለማውጣት የሚያደርስ ችካኔ ይፈፅማል ብላ ግን ፈፅሞ አልገመተችም ነበር (ቁም ነገር መፅሔት 10ኛ ዓመት ቁጥር 116፤ መስከረም 2004ዓ.ም)፡፡

ፖሊስ ማረፊያ ቤት አስቀምጦ ምርምራ ከጀመረ በኋላ ወሬው እንደተለመደው መገናኛ ብዙሃን ጆሮ ይደርሳል፡፡ ወሬውን የሰሙ ሁሉ የደርጊቱን ፈፃሚ ‹አውሬ፤ ሊሰቀል ይገባል!› ማለት ጀመሩ፡፡ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሴቶቹ ማህበራትና አደረጃጀቶች ሁለት የስብሰባ ፕሮግራሞችን በዳግማዊ ምንሊክ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤትና በሸራተን አዲስ አዘጋጁ፡፡ በመድረኮቹ ላይ ድርጊቱ ለምን ተፈፀመ?› በሚል መወያየት ላይ ያተኮረ ሳይሆን ይህንን የጭካኔ ደርጊት የፈፀመው ግለሰብ ሊሰቀል ይገባል በሚል የበቀል አስተያየት ላይ ያተኮረ ነበር (ቁም ነገር መፅሔት 10ኛ ዓመት ቁጥር 116፤ መስከረም 2004ዓ.ም)፡፡በሸራተን አዲስ የተዘጋጀው መድረክ ላይ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ ሰራተኞችን ያሳተፈ ስለነበር ሊወሰድ በታሰበው የፍርድ ቤት ውሎ ላይ የራሱ የሆነ ተፅእኖ ለማሳለፍ የታለመበት ነበር ለማለት ይቻላል፡፡

***********

## የፍሬህይወት ታሪክ

ጥቅምት 11 ቀን 2005 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡30 ገደማ ከካሳንቺስ ኢንተርኮንትኔንታል ሆቴል ወደ ኦሎምፒያ የሚወስደው መንገድ እንደወትሮው የትራፊክእንቅስቃሴአጨናንቆታል፡፡በተጨናነቀው በዚህ መንገድ ላይ ግን አንድ ሃችፓክ መኪና በአየር ላይ የሚበር በሚመስል ሁኔታ ይከንፋል፡፡ ከፊት ለፊቱ ባሉ መኪናዎች መንገድ የተዘጋበት የዚህ መኪና አሽከርካሪ ልክ ዮርዳኖስ ሆቴል ደጃፍ ጋር ሲደርስ ‹‹በአሳልፉኝ›› ምልክት በክላክስ አካባቢውን ያውከዋል፡፡

የክላክስ ድምፁ በተደጋጋሚ የተነፋላት ከፊት ለፊቱ ያለችው በተለምዶ ወያኔ ዲኤክስ መኪና አሽከርካሪ ክላክሱ ለእሷ የተነፋ አልመሰላትም ነበር፡፡ ወላጅ እናቷን ጭና ወደ ኦሎምፒያ አቅጣጫ መብራቱን ለመሻገር ጥረት ታደርግ የነበረችው አሽከርካሪ ከኋላዋ ያለውን ሰው ማንነት ለማረጋገጥ በመኪናዋ የጎን መስታወት /ስፖኪዮ/ ስትመለከት በፍ/ቤት በፍቺ ወረቀት የተለየችው የሁለት ልጆቿ አባት መሆኑን ተመልክታለች፡፡

የቀድሞው ባለቤቷ የክላክስ ጩኸትና በተደጋጋሚ በእጅ ምልክት እንድትቆም የሚያሳያት ዛቻ ያላማራት ሚስት የመንገዱን መብራት በፍጥነት አቋርጣ ወደ ኦሎምፒያ ደንበል አቅጣጫ ሽቅብ መንዳት ትጀምራለች፡፡ ከኋላዋ እየተከታተላት ያለው አሽከርካሪም የመጨረሻ ፍጥነቱን ጨምሮ ይከተላታል፡፡ አጠገቧ ያሉት እናት ወ/ሮ ተናኘ ሀ/ማርያም ባሏ ምን እንደፈለገ ቆማ እንድታናግረው አለበለዚያም የፀጥታ ሀይሎች ወዳሉበት እንድትነዳ ሲጠይቋት የሁኔታውን አስፈሪነት በመረዳት ሁለተኛውን አማራጭ ነበር የመረጠችው፡፡ እናም

ወደ ገጽ 32 ዞሯል




## ይልቅ ወሬ ልንገርህ



# ስለ ሀና ላላንጎ የመደፈር ድራማ!

ይህንን ወሬ ያገኘሁት ጦር ሀይሎች ሙሉ ወንጌል ከሚገኘው የታክሲ ተራ አስከባሪዎች ነው፡፡ከታሰሩት አንዳንዶቹ የእነዚሁ መረጃ ሰጪዎችም ጓደኞች ናቸው፡፡እነዚህ ሰዎች የነገሩን ምንነት ከፖሊስም በላይ የሚያውቁ ናቸው ቢባል ሀሰት አይሆንም፡፡የነገሩኝን ነገር እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ፡፡



በ21/1/07 ዓ.ም ምህረት ሀና በሴት ጓደኛዋ ምክንያት ያለ ወትሮ በምሳ ሰአት ወደ ቤት እንሂድ ብለው ያመራሉ፡፡ ይህ ሀሳብ የተፈጠረው በጓደኛዪቱ ሲሆን ቀድማ በሀና ጉዳይ ከአንድ ሹፍሬ ጋር ተስማምታ ነበር፡፡ ምሳ ይዛ ስለማትመጣ ምሳ እንብላ ብያት ይዣት እመጣለሁ ያኔ ትቀላጠፋለህ በሚል፡፡ ሀና እንደተባለው ወጥመድ ውስጥ ገባችና ጓደኛዋ አዘጋጅታቸው በነበሩ ሰዎች መስመር ውስጥ ገባች፡፡ አብረው ወደ ጦር ሀይሎች ጉዞ ተጀመረ፡፡ ሀና፣ ጓደኛዋ፣ ሹፌርና አንድ ረዳት፡፡ሀና ከመውረጃዋ ራቅ ብላ መሄዷ በክፉ አልጠረጠርችውም ፣ ብታቅማማም በጓደኛዋ ግፊት ግን ቶሎ እንመለሳለን ዛሬ ስለደበረን ሻይቡና ብለን ልክ በሰአታችን ወደ ቤት እንሄዳለን ብላ ካግባባቻት በኋላ ጉዞው ቀጠለ፡፡ ችግር የለም ልክ በሰአቱ እኛ እናመጣቿለን፣ ሰፈራችሁ ድረስ እናደርሳቿለን ተብለው ተነገሩ፡፡ የጉዞ መጨረሻ ሙሉ ወንጌል ታክሲ ታራ ነበር፡፡ እዛው ያ እነ ሀናን ይዞ የመጣው ታክሲ ለሌላ ሹፌር ተሰጠና እነ ሀናን ይዘዋቸው ከመጡት ሰዎች ጋር ከጋና ኤምባሲ ወረድ ብሎ ወደ ሚገኝ ቤት ሆነ፡፡ ተገባ፡፡ውስጥ ሌሎች ወንዶችም ነበሩ፡፡ጫት እና ሺሻ እንደ ጉድ የሚደራበት ቤት ነው፡፡የሀና ጓደኛ ከዚህ በፊትም ልማድ አላት ብሎኛል ይህንን ያስረዳኝ ሰው፡፡ ሀና ግን የመጀመሪያዋና ትንሽ እዚህ እንቆይና እንመለሳለን ተብላ ሻይ ተፈልቶላት እዛው ..አትፍሪ ተጫወቺ እየተባለች ቆይታለች፡፡

ጨሱ ጨሳጨሱ ያማራት አይመስለም፡፡ ሀና እየቆየች እየደከማት፣ እንቅልፍ እንቅልፍ እያላት ሄደ ከዛም ውስጥ ወደሚገኝ መኝታ ቤት አስገቧት፡፡ ይዟትም የገባው መጀመሪያ ሹፌሩ ነው ፡፡ ሀና ሰውነቷ ሞላ ያለ በሺሻ ቤት አንደበት ያልተበላችና ያረገበች ልጅ ነው የምትባለው፡፡ ከሹፌሩ በኋላም ሌሎች ተከታትለው ገብተው ድርሻቸውን ወስደዋል፡፡የሀና ጓደኛም እዛው ሌላ ክፍል ከሌሎች ወንዶች ጋር ነበረች፡፡ ያ አሺሺ ያነወዘው ስሜት ሀናን ስቃይ ውስጥ ከቷታል፡፡ በዚህ አይነት ጊዜው እየገፋ ሳለ ተማሪዎች የሚለቀቁበት ሰአት ደረሰ፡፡ሀና መንቃት አልቻለችም፡፡እንደ ሌሎቹ ብድግ ብላ እራሷን ጠራርጋ የምትዘጋጅበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ቢባል ቢባል አልተቻለም፡፡ ታክሲ መጣ ፡ ፡ ቢያንስ ታነክሳለች ተብሎ ነበር የተጠበቀው እሷግን ካለችበት መነሳትም አልቻለችም፡ ፡ እንዲህ ሆና እንዴት ነው የምንወስዳት ተባብለው እዛው ውይይት ተጀመረ፡፡ ጓደኛዋ የሆነ መላ ፈጥራ ሀኪም ቤት እንድትወስዳት ሀሳብ ተነሳ፡፡አይሆንም ለብቻዬ እፈራለሁ አለች፡፡ በቃ እስከማታ ልትነቃ ትችላለች እስከዛ አንዳችን ቤት ትረፍ ተባለ፣ ሹፌሩ ባለትዳር ስለሆነ ወደእሱ ቤት አይታሰብም፡፡ ሌላኛው እኔ ዘንድ ትሂድና ትረፍ ብሎ ተቀበለ፡፡ ሀናን ተሸክመው ጫኗት፡፡ የሀና ጓደኛም ምንም እንደማያውቅ ምንም እንደሌለ

ወደ ገጽ 12 ዞሯል






## ‹ስባለቤቴ ያስፈ የህይወት ታሪኬን ሁሉ መንገር ይኖርብኝ ይሆን እንዴ? ›

በዕምነት እባላለሁ፤የ33ዓመት ባለትዳር ሴት ነኝ፤በህይወቴ በርካታ ውጣ ውረዶችን አሳልፌያለሁ፤ በአሁኑ ጊዜ በፈጣሪ እርዳታ ነገሮች ተስተካክለውልኝ ትዳር ከመሰረትኩ ገና አንድ አመት አልሞላኝም፡፡ ባሳለፍኳቸው ጥቂት ወራቶች በትዳሬ ደስተኛ ነኝ፡፡ ባለቤቴ እጅግ በጣም ሲበዛ መልካምና ቀና ሰው ነው፡፡

ነገር ግን ባለቤቴ አንድ ነገርን አጥብቆ ይጠላል፤ እሱም ምንም ነገርን መደበቅ አይወድም ፤ ሁሉንም ነገር ቢነግሩትና ቢያውቅ እንደሚወድ ደጋግሞ ይነግረኛል፡፡ እኔም ይህን ስለማውቅ ከተዋወቅንበት ጊዜ አንስቶ ስለሚፈጠሩ ነገሮች ምንም የደበኩት ነገር ባይኖርም ከሱጋር ከመተዋወቄ በፊት ስላሳለፍኩት ህይወትም ሆነ በግሌ ሚስጥር ብዬ ስለያዝኳቸው ነገሮች ግን አልነገርኩትም፡፡ ይህም በመሆኑ ዘወትር በውስጤ ሚስጥሬ ብዬ የደበኩትን ነገር ለባለቤቴ ባለመናገሬ ምክንያት በትዳሬ ሳይ ችግር ያጋጥምኝ ይሆን በሚል ስጋት እሣቀቃለሁ፡፡ ውድ አማካሪ በእርግጥ ለባለቤቴ ያለፈ የህይወት ታሪክ እና ሚስጥሬን ሁሉ መንገር ይኖርብኝ ይሆን እንዴ?

በዕምነትነኝ /ከሾላ/

ውድ ጠያቂያችን በዕምነት ፡- ልክ እንዳንቺ ሁሉ ብዙዎቻችን አሁን አብረው በትዳር ከተሳሰረናቸው የትዳር አጋሮቻችን ጋር ከመተዋወቃችን በፊት ሌላ ህይወት ነበረን፡፡ ምናልባትም ይህ ያለፈ ህይወታችን አስቀያሚና ልናወራው ቀርቶ ፈፅሞ ልናስታውስ አንፈልግ ይሆናል ፤ ይህንን ከባለቤታችን ጋር ያልተጋራነውን፣ ለማውራት የማንፈልገው የግል ህይወታችን ለምሳሌ ፡- የቀድሞ ፍቅረኛችን ስናረግዝ ክዶን ያረገዝነውን ልጅ ካስወረድን ከሆነ ፣ ለብዙ ጊዜ አብሮን የቆየ ፍቅረኛችን ግልፅ ባልሆነ ምክንያት ከሌላ ሰው ጋር ትዳር መስርቶ ቢዘነጋን፣ ወሲባዊ ጥቃት ደርሶብን ከሆነና ሌሎች ከፍተኛ የሆነ የስነ- ልቦና መረበሽ የሚፈጥሩብንና ከአዕምሯችን እንዲወጡልን የምንፈልጋቸው ባለቤታችን የማያውቀው ድብቅ የሆነ የግል ሚስጥራችንን ለባለቤታችን ማሳወቅ ይገባናል ወይ? የሚለው የብዙዎቻችሁ ጥያቄ ነው?

ስለዚህ አንቺ ማጤን ያለብሽ አንድ ነገር፣ ሚስጥርሽን ለባለቤትሽ ብታካፍይ የባለቤትሽን ስሜት ሊጎዳው እንዲሁም ለአንቺ ያለውን ፍቅር ሊቀንስ እንደሚችል ወይም አጠቃለይ በትዳርሽ ላይ ችግር የሚፈጠርብሽ ከመሰለሽ ቆም ብለሽ አስቢ፡፡ ትዳር ውስጥ ግልፅነትና ታማኝነት ቢያስፈልግም ትዳርሽን ይጎዳል ብለሽ ያሰብሽውን ነገር ለትዳርሽ ብለሽ ብትደብቂ ምንም ክፋት የለውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ባለፈው ህይወትሽ የተከሰቱ ችግሮች ከአሁኑ የትዳር ህይወት ጋር ምንም የሚያያይዝ ወይም የሚያገናኝ ነገር ከሌለውና በአሁኑ ህይወትሽ ላይ ምንም ተጽኖ የማይፈጥር ከሆነ የግል ህይወትሽን በግል ሚስጥር አድርገሽ የመያዝ መብት አለሽ፡፡

ያለፈው ህይወትሽ በአሁኑ ትዳርሽ ላይ ችግር ሊፈጥር የሚችል ከሆነ ግን ቀደም ብለሽ ባለቤትሽን ማሳወቅ ይገባሻል ፡፡ ችግር የማይፈጥር ቢሆን እንኳን! አንቺ ለባለቤትሽ መንገር ከፈለግሽ ወይም ሚስጥርሽን በውስጥሽ መያዝ የሚያስጨንቅሽ ከሆነ በቅሚያ በጣም ለምታምኚት የቅርብ ጓደኛሽ ወይም ቤተሰብሽ ጠርተሽ አማክሪ፤ ይህን በማድረግሽ መጀመሪያ ሀሳብሽን ለባለቤትሽ እንዴት እንደምትገልጪ መለማመጃ ይሆንሻል፡፡ ሌላው ደግሞ የምታማክሪው ሰው ሚስጥርሽን ለባለቤትሽ ስትነግሪው ማስቀረትና መጨመር ያለብሽን ማብራሪያ እንዲሁም ሀሳብሽን በተሻለ መንገድ የምታቀርቢበትን ሁኔታ ያጋራሻል ፡፡ ለባለቤትሽ ያለፈ የግል ህይወትሽን ወይም ሚስጥርሽን ካካፈልሽው በኃላ ባለቤትሽ አስተያየት ከመስጠቱና በጉዳዩ ላይ ከመወያየታችሁ በፊት በነገሩ ላይ ትንሽ እንዲያስብበት ለብቻው ጥለሽው ከፊቱ ዞር በይ፡፡ በመጨረሻም መልካም ዕድል እንዲገጥምሽ እመኝልሻለሁ፡፡

# አቶ ሳሳንጎ አዮሶ

## ‹‹ልጄ ቶሎ ህክምና ብታገኝ ልትተርፍ ትችል ነበር››

በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን በተለይም በማህበራዊ ድረገፃች በርካታ ሠዎች የሚነጋገሩበት የወቅቱ አጀንዳ የታዳጊ ተማሪ ሃና ላላንጎ በ‹አምስት› ወንዶች ተገዳ መደፈርና ህይወቷ ማለፉን የሚመለከት ሆኗል፡፡ የ10ኛ ክፍል ተማሪ የነበረችው ሃና በሆስፒታል እያለች ህይወቷ ከማለፉ በፊት ለፖሊስ ሰጠችው የተባለውን ቃል መሠረት በማድረግ በተፈጸመው ድርጊት ዙሪያ መጀመሪያ የተነገረው ታሪክ ታዳጊዋ ታክሲ ባሳፈሯት ሠዎች ተወስዳ እንደተደፈረች የሚገልጽ ሲሆን አሁን አሁን ደግሞ ሌላ አዲስ ታሪክ እየተሰማ ነው፡፡

ሃና ላላንጎ በሴት ጓደኛዋ በተቀነባበረ ሴራ ወደ ሺሻ ቤት ተወስዳ ከ8 በሚበልጡ ወንዶች መደፈሯን የሚገልጹ ጽሁፎች በማህበራዊ ድረገፃች ተለቀዋል፡፡ የታዳጊዋ አባት አቶ ላላንጎ አየሶ ግን የሚወራው ሁሉ ያልተረጋገጠ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ከቁም ነገር መጽሔት ጋር ተከታዩን ቃለ ምልልስ አድርገዋል፡፡

**ቁም ነገር፡- ስለቤተሰብዎ ይንገሩን፤ ስንት ልጆች አሉዎት?**

አቶ ላላንጎ፡- የአምስት የቶችና የአንድ ወንድ ልጅ አባት ነኝ፡፡

**ቁም ነገር፡- ሃና ለቤተሰቡ ስንተኛ ልጅ ነች?**

አቶ ላላንጎ፡- 6ኛ ልጅ ነበረች፡፡

**ቁም ነገር፡- እርስዎ የት ነው የሚሠሩት?**

አቶ ላላንጎ፡- መብራት ሃይል ነው ተቀጥሬ የምሠራው፡፡

**ቁም ነገር፡- ሃና ከቤት ወጥታ ሳትመለስ የቀረችው መቼ ነበር፤ እስኪ ስለዚያ ቀን ያስታውሱን?**

አቶ ላላንጎ፡- ሁሌም ጥዋትም ማታም በታክሲ እንድትሄድ ነው የምነግራት፤ በታክሲ ነው የምትመላለሰው፡፡ ያን ቀን መስከረም 21 ጠዋት ት/ቤት ከሄደች በኋላ ግን በተለመደው ሠዓት ተመልሳ አልመጣችም፡፡ እኔ የመንግስት ሠራተኛ ነኝ፡፡ በዚያ ቀን ደግሞ እረፍት ላይ ነበርኩ፡፡ ሁሌም 10 ሰዓት ላይ ነበር ቤት የምትደርሰው፡፡ ያን ቀን ግን ብንጠብቃት ቀረች፡፡ 12 ሰዓት ድረስ ጠብቀን ስትቀር እዚያው ሠፈር አካባቢ ጓደኛዋ ስላለች እሷ ቤት ሄድን፡፡ እሷን ሄደን ስንጠይቃት በታክሲ ሳትሄድ አትቀርም፤ እኔ ሌላ የማውቀው ነገር የለኝም አለችን፡፡ ቤተሰቦቿን ሁሉ ገብቼ ‹‹እባካችሁ ዛሬ ከጠፋች ልጄ አትመለስም፣ ልጃችሁ የምታውቀው ነገር ካለ ትንገረን›› አልኳቸው፡፡ ምንም እንደማታውቅ ተናገረች፡፡ ከዚያ በኋላ ነው ለፖሊስ ሪፖርት ያደረግነው፡፡

**ቁም ነገር፡- ከስንት ቀን በኋላ ነው የተገኘችው?**

አቶ ላላንጎ፡- ከ11 ቀን በኋላ ነው፡፡

**ቁም ነገር፡- 5 ቀን በኋላ ነው የተገኘችው የሚለው መረጃ ታዲያ ከየት የመጣነው?**

አቶ ላላንጎ፡- እኔ ምንም የማውቀው ነገር የለም፡፡ እኛ የሠማነው ከ11 ቀን በኋላ ነው፡፡ መስከረም 21 ቀን ጠፍታ ጥቅምት 1 ቀን ነው የተገኘችው፡፡ 9 ሰዓት ላይ ነው ድምጽዋን በስልክ የሠማሁት፡፡ ከዚያ የሷን ታላቅ እህቶች እባካችሁ እዚህ ስልክ ላይ ደውላችሁ ልጄን የት እንዳለች ጠይቃችሁ አምጡልኝ አልኳቸው፡፡ እኔ በዚያ ሰሞን በጣም ተጎድቼ ጤናዬ ሁሉ ጥሩ አልነበረም፡፡ ከዚያ ደውለው የታክሲ ሹፌሩን አገኙት፡፡ ሃናን እሰጣችኋለሁ ብሎ መጣ፡፡ ሃናን ስጠን ሲሉት ደግሞ ያለችበት እወስዳችኋለሁ ብሎ እነሱንም ይዞ ሊጠፋ ፈለገ፡፡ ድጋሜ ጥፋት ሊያጠፉ፡፡ ከዚያ እሱን ትተው የታክሲውን ታርጋ ቁጥር በመያዝ ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮልፌ ቀራንዮ ለሚገኘው አመለከትን፡፡ ፖሊሶች በዚያ መሰረት ተጠርጣሪዎቹን ሊይዙ ችለዋል፡፡

**ቁም ነገር፡- ከዚያ በኋላ ሃና የት ነው የተገኘችው?**

አቶ ላላንጎ፡- ጦር ሃይሎች ሙሉ ወንጌል አካባቢ ነው የተገኘችው፡፡ ልጆች አፋፍሠው አመጧትና ወደ አለርት ሆስፒታል ወሰድናት፡፡ 11 ሰዓት አካባቢ ነበር፡፡ እዚያ ስንሄድ ካዩዋት በኋላ ልጅቷ ደክማለችና ይሄ ወንጀል ስለሆነ መጀመሪያ ለፖሊስ አሳውቁ አሉን፡፡ ዘነበ ወርቅ ፖሊስ ጣቢያ አካባቢ አመልክቼ ቶሎ ተባበሩልኝ ብዬ ወሰድኳቸው፡፡ ከሞላ ጎደል ቃሏን ተቀበሉ፡፡ ማታ ወደ 3 ሰዓት አካባቢ በአስቸኳይ የመንግስት ጉዳይ ስለሆነ ወደ ጋንዲ ውሰዷት ተባልን፡፡ እዚያም ሊቀበሉን አልቻሉም፡፡ ብዙ ተጨቃጨቅን፡፡ ከዚያ ወጥተን ደግሞ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሄድን፡፡ ሌሊቱን እዚያ አደርን፡፡ አልጋ ስላልነበር ታማሚዋም እኛም ወንበር ላይ ነበር ሌሊቱን ያሳለፍነው፡፡ ምንም ህክምና በዚያ ቀን አላገኘችም፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ ምርመራ ውጭ ጨርሰህና ተባልኩ፡፡ ሠገራም ሽንትም አልትራሳውንድም አስመርምረህና ተባልኩ፡፡ እንደገና በሽተኛዋን ተሸክሜ ወደ ግል ሃኪም ሄድኩ፡፡ ምርመራ ይዤ ስመጣ ደግሞ ወደ ጋንዲ ሪፈር ተፃፈላት፡፡ ጋንዲ ደግሞ ወደ ዘውዲቱ ሪፈር አሉኝ፡፡ በዚህ ምክንያት ለ4 ቀናት ያህል ምንም ህክምና አልተደረገላትም፡፡ የህክምና እርዳታ የተደረገላት ዘውዲቱ ከገባች በኋላ ነው፡፡ ብዙ መንገላታት ደርሶብናል፡፡ እንዲህ አይነት ችግር ሲከሰት መንግስት ያስቀመጣቸው ሠዎች አፋጣኝ በሆነ መንገድ ወደ መፍትሄ መግባት ነበረባቸው፡፡ የህክምናው ሁኔታ ዘግይቷል፡፡ መደፈሯን ሁሉ ነግረናቸው ነው ያን ያህል የዘገየው፡፡



**ቁም ነገር:- ዘውዲቱ ከደረሰች በኋላ ምን አይነት ህክምና አገኘች?**

አቶ ላላንጉ:- እንዳይዋት በጣም አዘኑ:: ህክምና ጀመሩ:: ከዚያ በፊት ግን ልክ እንደሌሎቹ ሆስፒታሎች ሁሉ እነሱም ውጭ አስመርምረህ ውጤት ይዘህ ና አሉኝ:: ተሸክሜ እሷን ይዤ ተንከራተትኩ:: ከዚያ ሁሉንም አስመርመሬ ውጤት ወሰድኩ::

**ቁም ነገር:-በህክምና በኩል የነበረው መጓተት ለሃና ህይወት ማለፍ ምክንያት ሆኗል ይላሉ?**

አቶ ላላንጉ:- ቶሎ ብትታከም ልትድን ትችል ይሆናል:: አይታወቅም፤ ፍርዱ የእግዝአብሔር ነው፤ ታክማም ላትተርፍ ትችላለች:: ግን ዘውዲቱ ከገባች በኋላ እዚያ ያሉ ዶክተሮች የቻሉትን ሁሉ አድርገዋል:: የሷን ሞራል ለመጠበቅ ዶክተሮችም ነገርሶችም ከጎኗ ሆነው እያለቀሱ ቁስሏን እያጠቡ ለማትረፍ ጥረዋል:: የእነዚህ ወገኖችን ጥረትና ሞራል መንካት አልፈልግም:: ግን ዘገየ:: ወዲያውኑ ችግር ሲደርስ ወደርምጃ ገብቶ ችግሩን መፍታት ነው መቅደም ያለበት:: ችግር ላይ ችግር ጨምሮ በዚህ ግባ በዚህ ውጣ የሚል ከሆነ ዋጋ የለውም:: ወደፊት እንዲህ አይነት ነገር አይደገም ነው መልእክቴ:: መጀመሪያ መቅደም ያለበት ነፍስ ማዳን ነው:: ከዚህ በኋላ ልጄን አላገኛትም:: ግን ለወደፊቱ ትምህርት መሆን አለበት:: የዘውዲቱ ሆስፒታልን መረጃ ሳይ ቁስሏ ወደ ጋንግሪን ተቀይሯል ይላል:: ይሄ የሆነው ህክምናው በመዘግየቱ ምክንያት ነበር::

**ቁም ነገር:- ሀና ስለደረሰባት ነገር የተናገረችው በሆስፒታል እያለች ነው?**

ላላንጉ:- አዎ::

**ቁምነገር:- ምንድነው ያለችው?**

አቶ ላላንጉ:- ሁሉንም ነገር ተናግራለች:: በታክሲ አፍነው እንደወሰዷት፣ በጩቤ እያስፈራሩ ብትጮሂ እንወጋሻለን ብለው ከወሰዱ በኋላ 5 ሆነው አስገድደው እንደደፈሯት ተናግራለች:: ከመርማሪ ፖሊሶች ጋር ሆነን 6 ተጠርጣሪዎች ሆስፒታል ቀርበው ስናሳያት ሶስቱ የደፈሩኝ ናቸው፣ ሶስቱ ግን የሉበትም ብላ አረጋግጣለች:: ቀሪዎቹን ሁለቱን ሠዎች ደግሞ ፖሊስ አድኖ ሊይዛቸው ችሏል:: በጥፋቱ እጁ አለበት ተብላ የተጠረጠረች ሴት ግን አልተያዘችም::

**ቁም ነገር:- ሃናን አሳልፋ የሰጠቻት እሷ ናት ብለው ያምናሉ?**

አቶ ላላንጉ:- እሱን እግዚአብሔር ነው የሚያውቀው:: ግን ሚስጥር ታውቃለች:: ሃና በጠፋች ጊዜ ለባለቤቴ ሃና ቀራንዮ አካባቢ ነች ብላ ተናግራለች:: ይሄንን በምን አወቀች? ተጠርጣሪዎቹም ቢሆኑ ጓደኛዋ ነች ለዚህ ያበቃቻት እያሉ ሲነጋገሩ ነበር:: ልጄም ሴቷን ያዙ ብላ ቃሏን ሠጥታ ፈርማለች::

**ቁም ነገር:- የሃናና የልጅቱ ግንኙነት ምንድነው?**

አቶ ላላንጉ:- ጓደኛዋ ነች:: ቤት ድረስ ትመጣለች::

**ቁም ነገር:- በፖሊስ ተይዛ ነበር?**

አቶ ላላንጉ:- አዎ! በፖሊስ ተይዛ ቃሏን ተቀብለው በዋስ ተለቃለች:: እኛ ደግሞ እሷ በቁጥጥር ስር ትዋልልን፣ ሚስጥር ከሷ ሊወጣ ይችላል እያልን ነው::

**ቁም ነገር:- ተጠርጣሪዎቹ ፍርድ ቤት ቀርበው ወንጀሉን አልፈጸምንም ብለዋል የሚለው ነገርስ?**

አቶ ላላንጉ:- ሀና እኮ ለይታቸዋለች:: እነሱም እኮ ለፖሊስ ቃላቸውን ሠጥተው መፀፀታቸውን ገልጸው ፈርመዋል:: ይሄ የፍርድ ቤት ጉዳይ ነው:: እዚያ ውስጥ አንገባ::

**ቁም ነገር:- ጉዳዩ በሚዲያ የተሰማው ዘግይቶ ነው፤ የዚያ ምክንያቱ ምንድ ነው?**

አቶ ላላንጉ:- እኔ ለሚመለከተው ለሴቶች ጉዳይ አሳውቄያለሁ:: ፖሊሶችም የሚያውቁት ጉዳይ ነው፤ እኔ ልጄን ለማዳን ነው የመጀመሪያ ሩጫዬ:: እዚያ ላይ ነው ደፋ ቀና ስል የከረምኩት::

**ቁም ነገር:- አሁን በሚዲያው ላይ እየተሠማ ያለው መረጃ የተለያየ እየሆነ ነው:: የተሳሳተ መረጃ እየወጣ ነው ያለው?**

አቶ ላላንጉ:- አንዳንዶች መረጃውን ከኛ ሳያገኙ የተሳሳተ መረጃ የሚያወጡ አሉ:: ጉዳዩ ከደረሠብን ከእኛ ከቤተሰብ እንደናንተ በግንባር ቀርበው ሳይጠይቁ ያልሆነ ነገር ያወጣሉ:: ቢጠይቁን እኛ በግልጽ እንነግራቸዋለን፤ ይሄ ለትምህርት ለሌሎች ኢትዮጵያዊያን እንዲሆን ህግ ደግሞ ለተጠቂት እንዲደርስ በማድረግ ትክክለኛውን እውነት ማስቀመጥ ስለሚገባ ሚዲያ የተሳሳተ ማውጣት የለበትም::

**ቁም ነገር:- ሀና የተደፈረችው ሺሻ ቤት ነው የሚባለውስ?**

አቶ ላላንጉ:- በፍፁም፣ ልጄ እንኳን ሺሻ ቤት ልትገባ ይቅርና ሰው ቀና ብላ የማታይ ልጅ ነች:: ከትምህርቷ መልስ መፅሐፍ ቅዱስ ላይ ነው የምትገኘው::

**ቁም ነገር:- ሀና ምን አይነት ባህሪ ያላት ልጅ ነበረች?**

አቶ ላላንጉ:- ምን ብዬ እገልፃታለሁ፤ ከሥራ ስመጣ እንኳ ገና ቤት ሳልደርስ ነው የውጪውን በር ከፍታ የምትጠብቀኝ፤ አሁን ብናገረው ምን ዋጋ አለው? ፍርዱን ግን እግዚብሔር ይስጥ፤ ልጄን መልሼ አላገኛትም፣ ግን የሌሎች ልጆች የዚህ አይነት ጥቃት እንዳይገጥማቸው ነው ደጋግሜ የምናገረው::

**ቁም ነገር:- እናመሠግናለሁ::**

## ክፍት የሥራ ቦታ

ቁም ነገር ሚዲያና ኢንተርቴይመንት ኃ/የተ/የግ/ ማህበር ከዚህ በታች መስፈርቱን የሚያሟሉ አመልካቾችን አወዳድሮ መቅጠር ይፈልጋል::

የሥራ መደቡ መጠሪያ:- የሽያጭ ሰራተኛ

ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ:- በማርኬቲንግ የኮሌጅ ዲፕሎማና ከዚያ በላይ

የሥራ ልምድ:- በሽያጭ ስራ ቢያንስ ሁለት ዓመት

ብዛት :- አምስት

ፆታ:- ሴት

ደሞዝ :- በስምምነት

የምዝገባ ጊዜና ቦታ:- ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን አንስቶ እስከ ህዳር 30 ቀን 2007 ድረስ ካሳንቺስ ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ወረድ ብሎ ገነት ሴራሚክ 1ኛ ፎቅ

ለበለጠ መረጃ :- 0912-421462/0911-232015



# ያረጋል የኋሴ

## ‹የሀናን ጉዳይ በካሜራ ብንቀርፀው እናገኝ የነበረው ነገር ተመሳሳይ ነው›

**ኮንታክት መልቲ ሚዲያ ፕሮዳክሽን ባለፉት ሁለት ዓመታት በኢቲቪ3 እና በኢቢኤስ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ‹ጨዋታ/ሐበሻ ፕራንክ› የተሠኘ የመዝናኛ ፕሮግራም ሲያስተላልፍ ቆይቷል:: ፕሮግራሙ በተለይ የካሜራ ትኩረት በተሠኘ ዝግጅቱ በሀገራችን ሚዲያዎች ባልተለመደ ሁኔታ በድብቅ ካሜራ የህብረተሰባችንን የአስተሣሰብ ደረጃ ለማሳየት የሚሞክር ነው:: ከእነኚህ የሁለት ዓመት ተሞክሮዎቹ በመነሳት የኮንታክት መልቲሚድያ ፕሮዳክሽን ባለቤትና ስራ አስኪያጅ ጋዜጠኛና አርቲስት ያረጋል የኋሴ ማህበረሠባችን ለሚያያቸው ህገወጥና ግብረገብነት የጎደላቸው ድርጊቶች የሚያሣየው ቸልተኝነት ጾታዊ ጥቃቶችን ስለመሣሰሉ አስከፊ ጉዳቶች እንደዳረጉት ይናገራል::**

**ቁም ነገር፡- በቅድሚያ በምን ሙያ እንደተመረቅክና፣ እየሠራኸው ያለው ሥራ ምን እንደሆነ ንገረኝ?**

*ያረጋል፡-* እኔ ያረጋል የኋሴ እባላለሁ:: በሙያዬ ጋዜጠኛና አርቲስት ነኝ:: በጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ተምሬያለሁ፤ ከዚያ ስድስት ኪሎ በቲያትሪካል አርት ተመርቄያለሁ:: በጋዜጠኝነቱ ከአስር ዓመት በላይ ሠርቼያለሁ:: በሶስቱም ዘርፎች (ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ህትመት) ላይ ሠርቼአለሁ:: ከዚያ እንግዲህ ባለፉት ሠባት ዓመታት ኮንታክት መልቲ ሚዲያ ፕሮዳክሽን የሚል ድርጅት አቋቁሜ በአብዛኛው ከመዝናኛው ዘርፍ ጋር የተገናኙ ሥራዎችን፤ ኤቨንቶችን (ኹነቶች) ማዘጋጀት፤ የቴሌቪዥንና የሬዲዮ ፕሮግራሞችን በመሥራት፤ በቅርብም የህፃናት መፅሐፍ አሣትሜያለሁ:: እንደዚህ ከመዝናኛ ጋር የተገናኘ ሥራ ነው እየሠራሁ ያለሁት::

**ቁም ነገር፡- በቴሌቪዠን ላይ እየተላለፈ ያለው ፕሮግራምህ መች ተጀመረ? ዓላማውስ ምንድን ነው?**

*ያረጋል፡-* ከጓደኛዬ ጋር ነው ፕሮግራሙን የጀመርነው:: አሁን አሜሪካ ሀገር ሄዷል:: ረታ ይባላል:: አብረን ስድስት ኪሎ የተማርን ጓደኛሞቾች ነን:: ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት ሀሣቡን አምጥተን መጀመሪያ ኢተቪ3 ላይ ‹ጨዋታ› በሚል ነው የጀመርነው:: አብዛኛው ነገሩ ጨዋታ ነው:: ሽወዳ አይነት ስልት ይኑረው እንጂ ጨዋታ ነው:: ጨዋታ ሲሆን እያንዳንዱ ተመልካች ራሱን የሚያይበት፤ ተፈጥሯዊ ትወና ያለበት ነገር ነው:: ስለዚህ ብዙ ሠው ወዶት፣ መርጦት፣ፈቅዶት የሚያየው ነው:: ከዚያ ውጪ ካለፈው አንድ ዓመት በላይ ኢቢኤስ ቴሌቪዥን ላይ ‹ሐበሻ ፕራንክ› የሚል ፕሮግራም ነበረን:: የስም ለውጥ ነው እንጂ ዝግጅቱ አንድ ነው:: ኢቲቪ3 ላይ የነበረንን የአንድ ዓመት ስምምነት ስንጨርስ ሌላ አማራጭ ሚዲያ ፈልገን ወደ ኢቢኤስ ሄድን፤ እነርሱም አድንቀው ተቀበሉን:: በዚህ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በላይ ሠራን:: የስም ለውጥ ነው እንጂ ባለቤቱም አዘጋጁም አንድ ነው::

**ቁም ነገር፡- ፕሮግራሙ መተላለፍ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ማህበረሠቡ ዘንድ (ያልተለመደ ነውና) ያለውን አቀባበል እንዴት አገኘኸው?**

*ያረጋል፡-* እንግዲህ ምን መሠለህ እኔ በባህሪዬ ፈታኝ የሆነ ነገር ደስ ይለኛል:: መዝናኛ ሣስብ በተለመደው መንገድ አይደለም:: እኔ 96.3 ላይ ‹ጥንቅሽ› የሚል የሬዲዮ ፕሮግራም ነበረኝ:: እዚያ ላይም የተማሪና አስተማሪ ግንኙነት፣ ማርክ አሠጣጥ፣ የዩኒቨርስቲ ውስጥ ፍቅር፤ ውሏቸው፤ አመጋገባቸው፤ የትምህርት ሁኔታ ላይ ምናምን፤ እንዲህ ወጣ ያለ የተማሪዎችን ስሜት የሚነካ የሬዲዮ ፕሮግራም ነበረኝ:: መዝናኛን ሣስብ ደግሞ ብዙ ልንሠራቸው የሚገቡ ክፍሎች አሉ:: የአቅም እጥረት ካልኖረ በስተቀር ብዙ ጊዜ የውጪዎችን መዝናኛ በጣም አያለሁ፤ በጣም ነው የሚያዝናናኝ፤ ከልጅነቴ ጀምሮ እያደገ የመጣ ነው:: ስለዚህ ረታ የተባለው ጓደኛዬም ይህ ፍላጎት ስለነበረው እንዲህ አይነት ፕሮግራም ሠርተን ኢቲቪ3 ላይ አስኬድነው:: ከዚያ በኋላ ደግሞ ኢቤኤስ አብዛኛው ነገር ወደ መዝናኛ ያደላል የሚል ሀሣብ ስለነበረን ኢቲቪ3 ላይ የነበረንን ኮንትራት ስንጨርስ ወደ ኢቢኤስ ገባን:: በተለይ ስንጀምረው በጣም ከባድ ተግዳሮት ነበር:: የእኛን ሠው ተሸውደህል ስትለው ግላዊ ስብዕናው የሚነካ ነው የሚመስለው:: ጣቢያ ድረስ ይዞን እስከመሄድ፤ በተለይ ተዋንያኖቻችንን ቀድመን ስለምንመክራቸው እንጂ ከእነርሡ ጋር ድብድብ ለመፍጠር እስከመሞከር፤ አንዳንድ ጊዜ ፀያፍ ነገሮች መናገርም ገጥሞናል:: እንደዚህም ሆኖ አሣይተናቸው የእነርሡ ፈቃደኝነት ከሌለ ፕሮግራሙ አይተላለፍም:: ታዋቂ ሰዎች ላይም ሆነ ማንኛውም ሠው ላይ የምንሠራው ፕሮግራም የተሸዋጆቹ በጎ ፈቃደኝነት አለው:: አንዳንድ ሠዎች ቶሎ ሊናደዱ ይችላሉ፤ ግን



የፕሮግራሙ አዘጋጆች ረታ ወርቁ ማሞ እና ያረጋል የኋሴ

በቀላሉ ጨዋታ መሆኑን በተለይ እኔ ነግሬያቸው አግባባቸዋለሁ:: ተግዳሮቱ በጣም ከባድ ነው:: አንዳንዶቹ እንደውም ፕሮግራሙ አየር ላይ ይዋል ብለው ፈቅደውልን ተሠርቶ ካለቀ በኋላ ይደውላሉ:: እናቴ ጋር ተማክሬ በቃ ይቅር አለችኝ ይሉሀል:: የወጣበትን ገንዘብ አስበው:: የመኪና ነዳጅ አለ፤ ተዋንያን አለ፤ የካሜራ አለ፤ በአንድ ሰዓት ውስጥ ብዙ ፎርማቶች ነው ያሉት እና በጣም ከባድ ነው::

**ቁም ነገር፡- ከይዘቱስ አንጻር ምን ያህል ቁም ነገር ላይ ያተኩራል? ተመልካቹስ ቁም ነገር የሚጠብቅበት ፕሮግራም ነው?**

*ያረጋል፡-* የሚገርምህ ሀበሻ ፕራክን ዝም ብለህ ስታየው የሚያስቅ ነገር አለው:: ልክ እንደ ውስጠ ወይራ የዚያን ያክል መልዕክት የማስተላለፍ ጉልበት አለው:: ካሜራ የት ይሁን፤ እነማን ይምጡ የሚለውን ነገር ሠው ግምት ውስጥ እያስገባም:: የእለት እንቅስቃሴ ውስጥ ነው ያለው፤ ተፈጥሯዊ ነው:: የኛ ተዋናዮች ሣያስበው በመሀል ገብተው ‹በቀደም› መንገድ ላይ አንተነህ አይደል የመታኸኝ?› ብለው አንዱን ይጠይቃሉ:: በዚህ ጊዜ አንዳንዱ ተለሣላሽና ነገሩን ቀለል አድርጎ የሚያይ ነው:: አንዳንዱ በጣም ይናደድና እንዲያውም እፈልግሀለሁ ብሎ ወደ ሌላ ነገር ውስጥ ይገባል:: ስለዚህ

አንድ ሰው ሲሸወድ ሚሊየኖች ስብዕናቸው ይታያል፡፡ ለምሣሌ ሸዊትን ማንሣት ይቻላል፤ እነ ሠራዊት፤ እነ ሠይፉ፤ እነ ብርሀኑ ተዘራ፣ ሃና ዮሐንስ ተሸውደዋል፡፡ ታዋቂዎቹም ላይ ስትመጣ መድረክ ላይ ከምናውቃቸው ፀባያቸው ወጣ ያለ የግል ባህሪያቸውን ታይበታለህ፡፡ እና እንዲያውም ብዙ ሠው እከሌን ሸውዱልኝ፤ አበበ ባልቻን፣ ሙሉዓለምን ሸውዱልኝ ይለናል፡፡ ስለዚህ ብዙ ሰው ‹‹እኔ ብሆንስ?›› እያለ የሚያየው ስለሆነ ይማርበታል፡፡ ጨዋታ ነው ስትለው ‹ሸወዳችሁኝ› ነው የሚለው፤ ግን እላይ ደርሷል ንዴቱ፡፡ አንድ ጊዜ አንዱን ኢንጂነር ከባድ ሸወዳ ነበር የሸወድነው፡፡ ሚስቱ ወልዳለች እና በዓመቱ ልደቱን ሊያከብሩ ነው፡፡ ከዚያ የሚስትየዋ እህት እኔ ጋር መጣችና ‹‹እህቴና የእህቴን ባል መሸወድ እፈልጋለሁ›› አለች፡፡ ‹‹እሺ ደካማ ጎናቸው ምንድን ነው? በምን መንገድ እንሸውዳቸው? ደም ግፊት አለባቸው ወይ? ልብ ድካም አለባቸው ወይ?›› ብለን ሁሉ በደንብ እንጠይቃለን፡፡ ስለዚህ ቀድመን በሥነልቦና ረገድ እንዘጋጃለን፡፡ እና እህቷ የወለደችበትን ሆስፒታል ነገረችን፤ በወቅቱ ሌላ ልጅ የወለደች ሴት አለች፡፡ ከዚያም አስፈላጊውን መረጃ ይዘን የእኛ ተዋናዮች ባልና ሚስት መስለው ተያይዘው ሄድን፤ ከዚያ የእኛ ተዋንያን ጨዋታ ጀመሩና ‹‹ሆስፒታሉ ውስጥ ከዓመት በፊት የወለዳችሁት ልጅ ከእኛ ልጅ ጋር ተቀያይሯል፡፡ እና ዲኤንኤ አስመርምረን ትክክለኛው ልጃችን እናንተ ጋር ያለው መሆኑን አረጋግጠናል›› ሲሏቸው ሚስትየው ተረጋግታ ነበር፤ ባልየው ግን ተናደደ፡፡ ከዚያ ተሸውደሀል ስንለው ‹‹ውስጤን እያወቅኩት፤ ማንነቴን እያወቅኩት ለምን ተናደድኩ? ለምን ተዋንያኑን አመናጨቅኳቸው፤ ይቅርታ ልጠይቃቸው›› ብሎ ሁሉ ነበር፡፡ እና በጣም ብዙ ተመልካች ነው ያለው፡፡ በጣም ብዙ ሠው ይማራል፡፡ እንደሚዲያ ማኅበረሠባዊ ሃላፊነት አለብን፡፡ እና የካሜራ ትኩረት የሚል ፕሮግራም አለን፡፡ ለምሳሌ መንግሥት ያሠራው አስፋልት ማካፈያ ብረት ይኖራል፡፡ እና (የእኛ ተዋናይ) አውቆ ቁራጭ ብረት ይዞ ብረቱን እየገዘገዘ የሆነ ሰው ሲያልፍ ‹በናትህ አግዘኝ› ይለዋል፡፡ አንዳንዱ ‹እንዴ ለምን? እንዲያውም ታያለህ ፖሊስ ጣቢያ ሄጄ እናገርልሃለሁ› ይላል፡፡ ሌላው ደግሞ መጥቶ ያግዘዋል፡፡ ብረት ለመዝረፍ አብሮ የሚያቋርጠው አለ፡፡ አንዳንዱ ደግሞ ለምን ብሎ የሚተናነቅ አለ፡፡ ለምሳሌ ችግኝ ተተክሎ መንከባከብ ሲገባው (የእኛ ተዋናይ) አውቆ እየነቀለ ‹አናቅለኝ› ብሎ መንገደኛ ይጠይቃል፡፡ ‹ቸኩለናል፡፡ በርታ በርታ› ብሎ ይሄዳል አንዳንዱ፡፡ አንዳንዱ ደግሞ መጥቶ ‹ና ወደ ህግ ቦታ እንሄዳለን› ይላል፡፡ አይቶ እንዳላየ ሆኖ ‹ኧረ ተመልከቱት፤ ችግኝ ይነቅላል› የሚል ሰውም አለ፡፡ ሙዝ ልጦ መንገድ ላይ መጣል የተለመደ ነው፡፡ በማንኪያ አይስክሬም እየበሉ አይስክሬሙን ከእነ ዕቃው መጣል በየጊዜው የምናየው ነው፡፡ መንገድ ላይ በሸንበቆ ታጥረው ከሚተከሉ ችግኞች ላይ ሸንበቆውን ለመንቀል ስትሞክር ‹ይህ የህዝብ ንብረት ነው፤ ቁጭ አድርግ›› የሚል ሰው አታገኝም፡፡ ምንአልባት ከሠባት ሠዎች ሁለቱ እንዲህ ቢሉህ ነው፡፡ለምሣሌየአስራስድስትዓመትልጅ፤ዩኒፎርም ለብሳ ሌላኛው በዕድሜ የሚበልጣት ተዋናያችን ዱርዬ መስሎ ፀጉሩን እያፍተለተለ ቁጭ ብሏል፡፡ ልጅቱ ዩኒፎርም ለብሣ ቦርሣ ተሸክማ ትመጣለች፡፡ እሡ ልጅቷን ተከትሎ እጇን ይጠመዝዛታል፤ ለመምታት ምናምን ይሞክራል፤ እሷ ታለቅሳለች፡፡ ይህን የሚያዩ ልጁን መምታት የሚችሉ ወጠምሻ ጎረምሶች ‹ባክህ የራሷ ጉዳይ፤ ተዋት› ብለው ነው የሚያልፉት፡፡ እናቶች፣ ሽማግሌዎች እያዩ ‹አሁን ምን አርጊ ነው የሚላት? ቢተዋትስ ?ለምንድነው?› ብለው ገፍተው አይጠይቁም፡፡ ከስንት አንድ ሰዎች ግን ፈራ ተባ እያሉ የሚጠይቁ አሉ፡፡ እነርሡም ቢሆኑ ምን አገባችሁ ሲሏቸው የሚመለሡ ሰዎች ናቸው፡፡ እንግዲህ በቀን በጠራራ ፀሀይ፤ ሴት ልጅ ስትደበደብ ኢቭን ለመደፈር እየተዘጋጀች ባለበት ሠዓት የእኛ ሰው አይከላከልም፡፡ አምስትና ስድስት ሠዎች ምንም ሣይረዷት አልፈው በኋላ ላይ አንድ ሠውዬ ሞተር አጥፍቶ ምናምን ከመኪና ወርዶ ሊከላከልላት መጣ፡፡ የእኛ ተዋናይ ‹‹ምን አገባህ?›› አለው፡፡ ‹‹ምን አድርጊ ነው የምትላት? አንተ ሴት እህት የለህም እንዴ?›› ብሎ የመኪናውን ቁልፍ ኪሡ ውስጥ መክተት ጀመረ፡፡ (ሊደባደብ ማለት ነው) በዚህ ጊዜ ተዋናዩ ቀድሞ ያዘውና ‹‹በቃ አንተ ሀላፊነትህን ተወጥተሃል›› አለው፡፡ ግን ያ የሆነው ብዙ ሠዎች አይተው እንዳላዩ ካለፉ በኋላ ነው፡፡

**ቁም ነገር፡- ታዲያ እንዲህ በየጊዜው የሚመለከታቸውን ችግሮች ምናገባኝ እያለ የሚያልፍ ማህበረሠብ መልሦ ደግሞ አንድ ጥቃት ከተፈጠረ በኋላ ጉዳዩን ሲያጫጩኸው የምናየው ለምን ይመስልሃል?**

ያረጋል፡- በቃ ቃሉ አንድ ነው፡፡ እኔ ኃላፊነት የሚሠማኝ ሠው ነኝ ወይ ብሎ እያንዳንዱ ሠው ራሡን መጠየቅ አለበት፡፡ በተቃራኒው’ኮ ይህቺ ልጅ የልጁ እህት፣ ሚስት፣ ልጅ ልትሆን ትችላለች፡፡ ያቺን ተማሪ ሣይረዳት አልፎ በኋላ ላይ መኪናውን አቁሞ ሊከራከርላት የመጣውን ሠው ሲመለከት ተከትሎ የመጣ አለ፡፡ ይህ ሠውዬ ሲቪል የለበሠ ፖሊስ ነው፡፡ ቀድሞ ነበር ልጅቷን መርዳት የነበረበት፡፡ የሀናን ጉዳይ ስናነሣ ቀድማ ጥርጣሬ ውስጥ አትገባም የሚል እምነት የለኝም፡፡ ይዘዋት ሲሄዱ፣ አንዳንድ ነገሮች ሲያደርጉ፤ ‹ይዘዋት ነው? ምን ሊያደርጓት ነው?› የሚል ሠው ሊኖር ይችላል፡፡ ግን በጉዳዩ ገብቶ ወይ ለፖሊስ ለመደወል፤ ወይ ልጆቹን ለመከተል የሚሞክር ሠው በቁጥር በጣም ትንሽ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሀላፊነት ጉዳይ ነው፡፡ በኋላማ እንደ መቀጣጫ፤ እንደ ማሣያ ይሆናል እንጂ ጥቅም የለውም፡፡ እኔ ሲገባኝም እንዲህ አይነት ወንጀሎችን ቀድሞ መከላከል ነው የሚያስፈልገው፡፡ ከዚያ በኋላ ሠዎቹን ወደ ህግ ማቅረብ ሁለተኛ ነገር ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ቤተሠብ ውስጥ ውይይት ያለበት ቦታ እንዲህ አይነት ነገር አይፈጠርም፡፡ እንዲህ አይነት ወላጆችና ልጆች ጠንቃቆች ናቸው፡፡ የሀና ጉዳይ የተፈጠረው ቀን ላይ ነው፡፡ በተቃራኒው እናስበው እስኪ፤ ማታ ቢሆን፤ ጨለማ ተገን ተደርጎ የሚፈጠር ቢሆን፤ የሆነ ግርግር ተፈጥሮ አጋጣሚን ጠብቆ ሊደረግ የሚችል ነገር ቢሆን ብለን ብናስብ ሁኔታው ከዚህ ይከፋል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ትልቁ ነገር የማህበረሠቡ ነው፡፡ ማህበረሠቡ እኔ ሃላፊነት የሚሠማኝ ነኝ ካለ ምንም አይመጣም፡፡

**ቁም ነገር፡- እንዲህ አይነት ችግሮች ከተፈጠሩ በኋላ ለተጠቂ ወገኖ ጉዳዩን ከአንድ ጫፍ ብቻ መመልከቱስ ተገቢ ነው?**

ያረጋል፡- ነገሩ ሲፈጠር ብዙ ጊዜ የሚታሠበው ጉዳቱ ነው፡፡ እኔ እንዲያውም የሀናን ነገር ስሠማ በልጆቹ የመጣ በቀል ነበር የመሠለኝ፡፡ ግን ሚዲያ ላይ ስሰማ ጉዳዩ ያ አይደለም፡፡ ማህበራዊ ሚዲያዎች ስትሠማ ደግሞ (ከወንጀለኞቹ ውስጥ) ምንም የለሁበትም የሚልም አለ፡፡ እሡን እግዜር ይወቀው፡፡ አንዳንዴ ከህግም ለማምለጥ መፈለግ ይኖራል፡፡ ግን በተቻለ መጠን የህግ ጉዳይ ነውና ከበስተጀርባው ያለው ነገር፤ ‹ከዚህ ሁሉ ተማሪ እሷ ላይ ሊፈጠር የቻለው ለምንድን ነው?› ተብሎ መመርመር አለበት፡፡ ይህን ማድረግ ወንጀለኞቹን ከመቅጣት በላይ አስተማሪነቱ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

**ቁም ነገር፡- እንደናንተ አይነት በሚዲያ ላይ የአየር ሠዓት ወስደው የማህበረሠቡን አስተሣሠብ የሚስውጡ ፕሮግራሞች በሚድያ ተቋማቱ የመታገዝና ስፖንሠር የማግኘት ዕድላቸውስ ምን ያህል ነው?**

ያረጋል፡- ፕሮግራማችን በጣም ብዙ ተመልካች እንዳለው ኢቲቪዎችም ሆኑ ኢቢኤሶች ያውቁታል፡፡ ፕሮግራሙ እየተላለፈ ሦስቱም ስልክ በጣም ቢዚ ይሆናል፡፡ ፌስቡክ

ወደ ገጽ 34 ዞሯል

## ሰለሞን እሸቴ እና ጓዶቹ የተመሰከረላቸው የሂሳብ አዋቂዎችና የተፈቀደላቸው ኦዲተሮች

Chartered Certified Accounting –UK and Authorized Auditor

We provide:-

- External and Internal Audit
- Performance Adult
- Compliance Audit
- Investigation Audit
- Training on Ethiopian Taxation
- Tax Advisory
- Liquidation, Mergers and Acquisition

ዋና ሥራ አስኪያጅ
ሰለሞን እሸቴ
Solomon Eshete

አድራሻ፡- 5 ኪሎ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ፋካሊቲ አጠገብ መካነ እየሱስ ህንፃ 3ኛ ፎቅ
Tel +251-911-40 49 89 / + 251-111-11 14 79 / Fax+251- 111-11 14 63
P.O.Box: 31003 / A.A, Ethiopia Email:- sol2000e@yahoo.com
Web:- Solomonesheteauditors.com solomonesheteco@ethionet.et

# ይልቅ ወሬ ልንገርህ...

መስላ ወደ ቤቷ ሄደች፡፡ ከወላጅ ተደውሎ ተጠየቀች አላውቅም አለች፡፡ ከልጆቹ ተደውሎ እስካሁን እንዳልተሻላትና እዛው እንደምታድር ተነገራት፡፡

እንደዚህ የሆነችው ለነገሩ አዲስ ስለሆነች ነው በደንብ ከተደረገች ይሻላታል ተብሎ ማታም በቁስሏ ላይ ቁስል ተጨመረባት፡፡አደረችበት፡፡ ቤተሰብ እስከ ትምህርት ቤት ሄዶ ነገሩን ለማጣራት ተሞከረ፡፡ መልስ አልተገኘም፡፡ ጓደኛዋ ተጠየቀች፡፡ መልስ የለም፡፡ ሌሎች የክፍል ልጆች ግን አብረው እንደነበሩና አብረው ሲሄዱ እንዳዮቸው ተናገሩ፡፡ የክፍል ሀላፊው በፖሊስ ተያዘ፡፡ በጓደኛዋም ላይ ክትትል ቀጠለ፡፡ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ግን ጓደኛ የተባለችው ልጅ ለሀና የምትቀይረው ልብስ እንደወሰደችላት፣ እየተመላለሰችም ትጠይቃት እንደነበረ ታውቋል፡፡ ይህንን ሁሉ ለወላጅ ባትናገርም፡፡ በአምስተኛ ቀን ፖሊስ አጨናንቆ ሲጠይቃት የሆኑ ልጆች በስልክ እየደወሉ እሷን እንደሚያስፈራሯትና ታክሲ ተራ አካባቢ የሚከታተሏት እንዳሉ አድርጋ ተናገረች፡፡ስልክ ቁጥሩንም ለፖሊስ ሰጠች፡፡ እስከ አምስተኛው ቀን ያለው በዚህ አለቀ፡፡

ከዚያ በኋላ ፖሊስ የስልክ ቁጥሩን ባለቤት ሲያፈላልግ ጥቆማ ደረሰው፡፡እነዛ ጠቋሚዎች እራሳቸው ሀና ላይ ሲከመሩ ከነበሩ ታክሲ አስከባሪዎች መካከል ናቸው፡፡ ታክሲ ተራ ወንጀል መደባበቅና ከፖሊስ ጋርም መሞዳሞድ ያለ ነው፡፡ ስልክ ቁጥሩ የታወቀበት መረጃ ደረሰውና ከአካባቢው ተሰወረ፡፡ ለፖሊሶች አዲስ ሀሳብም መጣ፡፡ ቢቃ ልጅቷን ይለቋታል እናንተ ወላጆቹን አሳምኑልን የሚል ነገር፡፡ ፖሊስም ነገሩን ጠለፋ አድርጎ ስለወሰደውም ጭምር ነገሩ በሰላም የሚፈታ ከሆነ ብሎ ለተከታታይ አምስት ቀናት ወላጆችን የማጽናናትና እየደረሰንበት ነው ታገሱ እያሉ ቆየ፡፡ ሌላ አምስት ቀንም ቢጨመርበት የሀና ቁስል እያመረቀዘ ሄደ፣እራሷን መቆጣጠር ሳትችል ቀረች፡፡ፖሊስ ቀነ ገደብ ሰጣቸው ለአፋኞቹ፡፡ በቶሎ ካልለቀቃችሁ እርምጃ እንወስዳለን የሚል፡፡ በመጨረሻ በ11ኛው ቀን ሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን አካባቢ በታክሲ አምጥተው ጣሏት፡፡የሐናን ጓደኛ ጨምሮ ሌሎች ሁለት ወንጀለኞች በዛው ታክሲ ከአካባቢው ተሰወሩ፡፡ የሐና እዛው መጣል ወላጅ ዘንድ ደረሰ፡፡ሄዱ፡፡ፖሊስ ነገሩን እንደማያውቅ ሆኖ ለማለፍ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡

አሁን ወደ እነዛ ታክሲ ተራዎች ስትሄዱ ልጅቷ የተደፈረችው በአምስት ሰዎች ብቻ ሳይሆን እዛ በሺሻና በጫት መርቅነው የነበረና ለጋ ገላዋን እያዩ ምራቅ ይውጡ የነበሩ ሁሉ ናቸው፡፡ ከአምስት በላይ፡፡አስገድዶ በመድፈር ሁሉም ወንጀለኞች ቢሆኑም ልጅቷን ለሞት የሚያደርስ ወሲብ የፈጸሙባት ሰዎች ግን ከፖሊስ ጋር ተባባሪና ጠቋሚ መስለው በመቅረባቸው እስካሁን አለመያዛቸውን እየተናገሩ ነው፡፡በተለይ ልጅቷ ወሲብ ሲፈጸምባት ሉብዙ ሰአታት እራሷን ስታ ስለነበረ በእሷ ላይ በትክክል ከፍተኛ ጉዳት ያደረሱትን ወንጀለኞች መለየት አትችልም፣ ፖሊስ ግን ጥቆማ ተሰጥቶታል ሊቀበል ግን አልፈለገም እየተባለ ነው፡፡ በተለይ



የጉሮሮና የፊንጢጣ ችግር ያደረሡባት ሰዎች ተጠቃለው አልታሰሩም፡፡ፖሊስ ልጅቷ በሺሻ ቤት መደፈሯንም እንዲነገርበት አይፈልግም፡፡ ወላጆችን ተጽናኑ እየተገኙ ነው ብሎ ከወንጀለኞች ጋር ሲደራደር እንደነበረም እንዲታወቅበት አይፈልግም፡፡ ሀና ጦር ሀይሎች አካባቢ የተጣለችውም ፖሊስ ያደርገው በነበረው ድርድር መሆኑንም እንዲታወቅበት አይፈልግም፡፡ እዛ መጣሏን እያወቀ ልጅቷን ወደ ሀኪም ቤት ከመውሰድ ይልቅ ወላጅ አባት ሳይቀሩ ሲያመለክቱ በዳተኝነት ነገሩን ለማድበስበስ የሞከሩትም ለዛ ነው፡፡ በሀና ላይ ችግር ያደረሱ ግን መረጃ በመስጠት ከፖሊስ ጋር የተባበሩ የተባሉ ወንጀለኞች እስካሁንም አልተያዙም፡፡የተያዙት ሀና በነቃ አእምሮዋ ሆና ችግር ሲፈጥሩባት ያየችውን ብቻ ነው፡፡

የሐናም ጓደኛ በተላላኪነት ተማሪዎችን ከትምህርት ቤት እየመለመለች ለሌሎች የማስበላትና የማታለል ተግባሯ ፣ ወንጀለኞች ያሉበት ቦታና ማንነታቸውንም በደንብ እያወቀች ለወንጀል ተባባሪና ዱላ አቀባይ መሆኗ ግምት ውስጥ ሳይገባ፣ ለፖሊስ መረጃ መስጠቷና በተራ አስከባሪዎች ዘንድ ጥብቅና ስለተቆመላት አልተያዘችም፡፡የእሷ መያዝ ሌሎች አስወጊ ተማሪዎችንም ለስጋት ስለሚዳርግና የተማሪን ገላ የለመዱ ቡድኖችን አንሰላ ስለሚያረቁት እንዲሁም በተማሪዎች ላይ እየተፈጸመ ያለው የወሲብ ንግድ ችግር ያጋጥመዋል፣ ገቢያችንን ያስቀርብናል፣ ሰለተባለ ይመስላል(ቦስተን ማራቶን ላይ ቦምብ በተደረገ ጊዜ አንድ ኢትዮጵያዊ ወንጀሉን እያወቀ እንዳላወቀ ሆነህል ተብሎ መከሰሱና እንደተፈረደበት ልብ ይለዋል)፡፡ የሺሻ ቤት አላፊው አልተያዘም፣ ስሙም አልተነገረም፡

በዚህ አጋጣሚ ሀና ወደ ሀኪም ቤትም ሄዳ ህክምና ማግኘት አልቻለችም፣ ለሀና ሞት የህክምና ተቋማችንም በዋናነት ጭምር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

ከሀና ታሪክ ጋር በተያያዘና የሳያት ደምሴንም ጉዳይ ማንሳት ይቻላል፡፡ ሳያት ደምሴ ከጥቂት ዓመታት በፊት ጦር ሀይሎች አካባቢ አፍሪካ ኮከብ ተብሎ በሚጠራ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትማር ነበር፡፡ አስረኛ ክፍል፡፡ እንዲሁ በጓደኛ ግፊት ሺሻ ቤት ገብታ በታክሲ ሹፌሮችና ረዳቶች እንደተደፈረች እናስታውሳለን፣ ራሷ ሬዲዮ ላይ ቀርባ ተናግራለች ለሰባት፡፡ሳያት የተደፈረችበት ቤት እስካሁንም ፖሊሶች የሚቅሙበት ቤት ነው፡፡እንዳውም ቅርንጫፍ ሺሻ ቤት ከፍቷል አማኑኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ ያለው የራዲካል ት/ቤት ተማሪዎች ላይ ጉዳት እያደረሰ ነው፡፡ ይህ ሺሻ ቤት ከራዲካል ት/ቤት ቢያንስ በ400 ሜትር ርቀት ነው የሚገኘው፡፡በጋራጅ ስለተሸፈነ አይታይም ብዙ የት ይደርሳሉ የተባሉ ቆነጃጅት ሴቶች ገብተው በቡድን ሳይቀር የሚደፈሩበት ቦታ ነው፡፡

አሁን አሁን ሊፒስቲክ ተቀብተው እንደሴት የሚያደርጋቸው ወንዶች ሳይቀሩ ሲወጡበትና ሲገቡበት አያለሁ፡፡ እዚህም በአብዛኛው ተማሪዎችን እየቀጠፉ ያሉት፣አንዳንድ የታክሲ ሹፌሮችና ረዳቶች እንዲሁም ስድ የጋራጅ ሰራተኞች ናቸው፡፡ቦታውን በደንብ ለመጠቆም ከራዲካል ትምህርት ቤት ፊት ለፊት ካለው የወጣቶች ማእከል አቅጣጫ ወደ ኮካ በሚወስደው መንገድ የገንዳ ማስቀመጫው አካባቢ ነው፡፡በጣም ብዙ ህጻናት የሚደፈሩበት ቦታ ነው፡፡ በሺሻ ቤት ምን ያህል የቡድን ወሲብ እንዳለ የሳያት ደምሴን ነገር ሰምተን በቀልድና በማላገጥ ማለፋችን አሁን በሀና ላይ ለደረሰው ነገር እንዳበቃን ልብ ልንልም ይገባል፡፡ ይህ ተማሪዎችን የማጥቃት ዘመቻ እስከ ትልልቅ ሆቴሎቻችን ድረስ እንደሚደርስ እንዲሁም በዚህ ነገር ከመንግስት ፈቃድ አግኝተው የሚንቀሳቀሱ ደላሎች እንዳሉበት እድሜያቸው ሳይፈቅድላቸው በብርና በተማሪ ደላላ ተታለው ብዙዎች እየተቀጠፉ እንደሆነ በእነ ሀና ላይ የደረሰው ነገርም ሳይቀድሙን እንቅደማቸው በሚል ስሌት እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡ እንደእውነት የሀና መደፈር በሀገር ውስጥ ሰው መሆኑን እንጂ ህገወጥ እያልን ያለነው በየሆቴሉ የብዙዎች ህይወት እንደሚያልፍ ይህም ወንዶች ሳይቀሩ ያሉበት መሆኑን፣ይህም በተለያየ ጊዜ በቪሲዲ ሳይቀር ያየነው እውነት መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ፍትህ ለተማሪዎቻችን!!!ፍትህ ለሃናዎች!! ፍትህ ለዜጎቻችን!! በል ቻዎ...(በሰይፈዲን ሙሳ)

# ይድረስ ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን!

## ከማህበረሠብ ሳይንስ ተማሪዎች ተፅፎ ያልተላከ ደብዳቤ




በዚሁ የህዳር ወር የመጀመሪያ ሣምንት ውስጥ በሣይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አዘጋጅነት ለአምስተኛ ጊዜ የተካሔደውን ሀገር አቀፍ የሽልማት ሥነ-ሥርዓት ተመልክተን አደነቅን፡፡ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት ዘርፍ የላቀ አስተዋፅኦ አበርክተዋል የተባሉት 268 የሚሆኑ በሳይንስና ሒሣብ፣ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት፣ በምርምርና ፈጠራ ውጤታማ የሆኑ መምህራን፣ ሠልጣኞችና አሠልጣኞች፣ ተመራማሪዎችና የፈጠራ ባለሙያዎች መሸለማቸው ተገቢና ይበል የሚያሠኝ ነው፡፡ ግና ለሀገሪቱ ልማት በየድርሻቸው የራሳቸውን አስተዋፅኦ ለማበርከት ደፋ ቀና የሚሉትን የማኅበራዊ ሳይንስ ተማሪዎች ፈፅሞ መዘንጋቱ እጅግ አሳዛኝ ነው፡፡ እንዲያውም የዚህችን ሀገር ነባራዊ ሁኔታ የተመለከትን እንደሆነ ባለብዙ ታሪክና የታላላቅ የጥበብ ሠዎች መፍለቂያ መሆኗ አይጠፋንም፡፡ ሀገሪቱም ከሣይንስ ይልቅ ከጥበብና ታሪክ ጋር ባላት የረጅም ጊዜ ዝምድና ነው የምትታወቀው፡፡

### የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር!

ታዲያ እስከዛሬ ድረስ ለአምስት ያህል ጊዜ ለሣይንስ፣ ለሒሳብ እና ቴክኖሎጂ ትምህርት ውጤታማ ተማሪዎችና የቴክኒክና ሙያ ሠልጣኝና አሠልጣኞች እንዲሁም ለፈጠራ ባለሙያዎች የተሠጠው ሽልማት የማህበረሠብ ሣይንስ ተማሪዎችና መምህራንን «የእንጀራ ልጅ» ማድረጉ ምን ያህል ተገቢ ነው? ተሸላሚዎቹ የእርሶን እጅ እየጨበጡ ሽልማት የተቀበሉበት የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን አዳራሽ የተሠየመው በኔልሰን ማንዴላ ስም አይደለም እንዴ? ከታላላቅ የዓለማችን ሠዎች አንዱ የሆኑት እኚህ የአፍሪካ እንቁ ደግሞ በማኅበረሠብ ሳይንስ ውስጥ የህግ ተማሪ እንደነበሩ ማን በነገረዎት?! የማኅበረሠብ ሣይንስም ትኩረት ተሠጥቶ ከተሠራበትና ተማሪና ምሁራኑ የማበረታቻ ሽልማት የሚያገኙ ከሆነ የህብረተሠቡን እሴት የሚጠብቁ፣ ለባህል ዕድገት የድርሻቸውን የሚያበረክቱ እንደነ እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ፣ ፕሮፌሠር ኃይሌ ገሪማ እና ክቡር ዶክተር ሐዲስ አለማየሁ ያሉ የሀገር ዋርካዎች ማፍራት ይቻላል፡፡ ከሣይንስና የሂሣብ ተማሪዎችና መምህራን ሌላ ስኬታማ ሴቶችንና አርሦ አደሮችን በየጊዜው እየመረጠ የሚሸልመው እጅዎ ለማኅበረሠብ ሣይንስ ተማሪዎችና ምሁራን ምነው አጠረ?

### የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር!

ሀገሪቱ ለሣይንስና ሒሳብ ትምህርቶች በቂ ትኩረት በመስጠት ከፍተኛ ብቃት ያላቸው ቴክኖሎጂስቶች፣ መሐንዲሶችና ሣይንቲስቶችን በብዛት የማፍራት ዓላማ እንዳላት ሲናገሩ አድምጠናል፡፡ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሠባ በመቶ ያህል የተማሪ ቅበላቸውን ለተፈጥሮ ሣይንስ ትምህርት እንዲያውሉ የትምህርት ፖሊሲዎም አስቀምጧል፡፡ ታዲያ ሠላሣ በመቶ ከሚሆኑት የማህበራዊ ሣይንስ ተማሪዎች መካከል ከፍተኛ ውጤት ያላቸውን መርጦ ሽልማት መስጠት በየምክንያቱ መሸለም ለለመደ መንግሥት ምን ይከብዳል? ነው ወይስ ለሀገሪቱ ዕድገት የሚያስፈልጉት መሐንዲሶች ብቻ ናቸው? ከመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች መካከል ሁለቱ የሣይንስና ቴክኖሎጂ፤ አስሩ ደግሞ የቴክኖሎጂ ተቋማት መሆናቸውን ተገንዝበ ለማህበረሠብ ሣይንስ ትምህርት የዚህን ግማሽ እንኳ ትኩረት አለመሠጠቱን የተመለከተ ሠው የሚመሩት መንግሥት የትምህርት ፍትሃዊነት ላይ ያለበትን ጉድለት በቀላሉ ይታዘባል፡፡ የተፈጥሮ ሣይንስና የሂሣብ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተማሪዎችና መምህራንን ብቻ መርጦ መሸለም ለማህበራዊ ሳይንስ ተማሪዎች የ‹አታስፈልጉኝም› መልዕክት ማስተላለፍ ሣይሆን ይቀራል?

### ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር!

ለአምስተኛ ጊዜ ለሣይንስ፣ ለሒሳብና ለቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተማሪዎችና መምህራን በተዘጋጀው የሽልማት መድረክ ላይ ቻይና እና ሌሎች የኤዥያ ሀገራት በዘርፉ ያመጡት ለውጥ ለዕድገት እንዳበቃቸው ተናግረው ነበር፡፡ ታዲያ ቻይና፣ ጃፓን እና ህንድ ተጠብቆ በቆየ ባህላቸውና የረጅም ጊዜ ታሪካቸው ለመታወቅ የቻሉት ለማህበረሠብ ሣይንስ ተገቢውን ትኩረት በመስጠታቸው አይደለምን?

### የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር!

ለነገሩ ድርጅትዎ ኢህአዴግ ለዓፄዎቹ መንግሥታትም ሆነ ለደርግ መንግሥት ያለውን የተንሸዋረረ እይታ ሠሞኑን ለመንግሥት ሠራተኞች በሠጠው ስልጠና ለመታዘብ ችለናል፡፡ ከዓፄዎቹም ሆነ ከደርግ መንግስት ለአብነት የሚጠቀስ አንዳች አዎንታዊ ጎን በስህተት እንኳ አላደመጥንም ነበር፡፡ ስለዚህ ታሪክን የመረዳቱ ክፍተት ከመንግስቶ የሚጀምር ይመስለናል፡፡ በቅርቡ ሊዘጋ እንደሆነ ሲነገርለት የሰነበተው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ትምህርት ክፍል ጉዳይም ከዚሁ መንግሥትዎ ለማህበረሠብ ሣይንስ ካለው የትኩረት ማነስ የመጣ ይመስለናል፡፡ ማህበራዊ ሳይንስ ጥሎ፤ የተፈጥሮ ሳይንስ አንጠልጥሎ መጓዙ ለሀገሪቱ ዕድገት የሚጠቅም አይመስለንምና ቢያስቡበት መልካም ነው፡፡



# ከአዲስ አበባ እስከ ዩክሬን

ይርጋለም ሃይሌ

ባለፈው ዕትም ከአዲስ አበባ እስከ ኢስታንቡል ያለውን ጉዞዬን አስቃኝቼዋለሁ፡፡ ተርኪሽ አየር መንገድ በጣም ድንቅ እና ምቾት ያለው እንደሆነና የኢትዮጵያ አየር መንገድም ብዙ መማር እንዳለበት ጠቅሻለሁ፡፡ አሁን ደግሞ ከኢስታንቡል ኪቭ ዩክሬን ያለውን ጉዞዬን በመከታተል አብራችሁኝ ትሆኑ ዘንድ በቁም ነገር እጠይቃችኋለሁ፡፡

ከኢስታንቡል ኪቭ ቦርይስፖል አየር ማረፍያ ጣቢያ ያለውን ጉዞዬን ለማድረግ ለአንድ ሰዓት ያህል እዚያው አየር ማረፊያ ውስጥ ማረፍ ግድ ይለኝ ነበርና የአየር ስአቱን በመከታተል ቆየሁ፡፡ ሰዓቱም እንደደረሰ ሰልፌን ያዝኩኝ፡፡ ስለ ሰልፍ ሲነሳ አንድ ነገር ትዝ አለኝ፡፡ እኛ ሀገር ያለው የሰልፍ አይነት፡፡ እኛ ለታክሲ ሰልፍ፣ ለዳቦ ሰልፍ ብቻ ለማንኛውም ወደ ጉዟችን እንመለስና፤ ከአዲስ አበባ ኢስታንቡል የነበረውን ጉዞዬን ታስታውሱ ከሆነ ብዙ ጥቁሮችን አይቻለሁ፡፡ እንዲያውም ሁለት ኢትዮጵያውያንን እንደተዋወኩኝ አጫውቼያችኋለሁ፡፡ በሚገርም ሁኔታ በአሁኑ ጉዞዬ ግን አንድም ጥቁር አላየሁም፡፡ ወደ አውሮፕላኑ የገባሁኝ ብቸኛው ጥቁር እኔ ነበርኩኝ፡፡ አልፈራሁም ያው ኢትዮጵያውያን የጀግንነት ስሜት አለብን አይደል፡፡

በተፈጥሮዬ ከሰው ጋር ለመግባባት ጊዜ አይፈጅብኝም፡፡ በመሆኑም ከአጠገቤ ያሉትን ነጮች ወድያው ተዋወቅኳቸው፡፡ ሁለቱም ዩክሬናውያን ነበሩ፡፡ ከየት እየመጣሁ እንደሆነና ዜግነቴን ጠየቁኝ፡፡ ‹‹I am Ethiopian››በማለት እኔም ጥያቄዬን አስከተልኩኝ ‹‹Do you know anything about Ethiopia?›› እናም ኢትዮጵያን የሚያውቁት በአትሌቲክስ እንደሆነ ነገሩኝ፡፡ እንደሚታወቀው አትሌቲክሳችን እያሽቆለቆለ የመጣበት ሁኔታ ነው ያለው ፡፡ታድያ ይህን ሀገራችንን ለዓለም ማህበረሰብ እያስተዋወቀ ያለው ማንነታችን ልንከባከበው እንዳለብን ለማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡ ታድያ እኔም በበኩሌ ዩክሬን ሼቭ ሽንኮ በሚባለው እግር ኳስ ተጫዋቿ እና በሁለቱ ክቺኮ ቦክሰኞች አማካይነት እንደውቃት ነገርኳቸው፡፡ እንዲህ እንዲህ እያልን አውሮፕላኑ ዩክሬን ኪቭ እያንጃበበ እንደሆነ አየሁኝ፡፡ ቶፕ ቪን ሳይ በጣም የምታምር ከተማ እንደሆነች አስተውያለሁ፡፡ አሁን ዩክሬን ኪቭ ቦይስፓ ኢንተርናሽናል ኤየርፖርት ደርሻለሁ፡፡

ከዚህ በፊት እንደገለፅኩት ወደ ዩክሬን የሄድኩት ዋናው አላማዬ ለ20ኛ ጊዜ በዩክሬን ሱሚ ስቴት ዩኒቨርሲቲ በሚደረገው ዓለማቀፍ የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ላይ በሚያተኩረው ሳይንሳዊ ኮንፈረንስ ላይ ለመሳተፍ ነበር፡፡ ኮንፈረንሱም እ.ኤ.አ ከግንቦት 6- ግንቦት 9 የተደረገ ነበር፡፡ ከአውሮፓ ሀገሮች መካከል ሰፊ ግዛት እና ትልቅ የቆዳ ስፋት ያላት ሀገር ዮክሬን ስትሆን በወቅቱ የተገነጠለችውን የክሬሚያን ግዛት ጨምሮ 29 የሚደርሱ ትላላቅ ስቴቶች አሏት፡፡

ዩክሬን ስድስት ሀገሮች በድንበር ይዋስኗታል፡፡ በስተሰሜን ቤላሩስ እና ፓላንድ በስተምእራብ ስሎቫኪያ፤ ሀንጋሪ እና መማእያ፣ በስተደቡብ ሞልዶቫ እና በስተምስራቅ ሙሉ ለሙሉ የራሽያ ፌዴሬሽን ታዋስናታለች፡፡ ሰፊ ድንበርም የምትዋሰነው በወቅቱ ጠበኛዋ ራሽያ ጋር ነው፡፡ ሀገሪቱን ከሰሜን እስከ ደቡብ በመሀል አቋርጦ የሚሄደው ወንዛቸው ካወቅቱ ፖለቲካ ጋርም ይያያዛል፡፡ ይህም ወንዝ ወደ ጥቁር ሐይቅ ይፈሳል፡፡

ታዲያ ይህ ወንዝ ነው ምዕራብ እና ምስራቅ ዩክሬንን ለይቶ ያለው፡፡ ከወንዙ በስተምስራቅ ያሉት ዋና ዋና ከተሞች ዩኔስክ፤ ሎሀንስክ፣ ድኔትሮጀትሮሽስክ፣ ክሪሚያ፣ ካርኮቭ እና ሱሚ ከተማ ሲሆኑ፡፡ አንድ አንድ እውቅ የፖለቲካ ተንታኞች እንደሚሉት ከሆነ እኚህን የምስራቅ ዩክሬን ከተሞች ነው ለመገንጠል ታርጌት የተደረገው፡፡

በርይስፓል ኢንተርናሽናል አየር መንገድ ደርሻለሁ፡፡ እዚያው እንዲቀበሉኝ ተመድባ በነበረችው ልጃገረድ አይኔን አማተርኩ፡፡ አንዲት መልከ መልካም ልጃገረድ መጥታ ‹‹Are you Yirgalem?›› አለችኝ ‹‹Yes I am Yirgalem from Ethiopia›› አልኳት Welcome to Ukraine I am Yulia thankrov በማለት እቅፍ አደረገችኝ ፈረንጆች a litfiahng እንደሚሉት ማለት ነው፡፡ Skype ላይ አውርተን ስለነበር ወዲያው ነው የለየኋት፡፡ እንግዲህ ኮንፈረንሱ የሚደረገው በስተምስራቅ ዩክሬን በምትገኘዋ ሱሚ ከተማ ነውና ምንም ሳናርፍ ኬቭ ከተማ ውስጥ ወደሚገኘው ባስ ስቴሽን አመራን፡ ከ Yulia ጋር ቀጥታ ወደ ሱሚ ስቴት ዩኒቨርሲቲ አመራን፡፡ በጉዟችን ላይ ስለ ኢትዮጵያ ምን እንደምታውቅ




ጠየቅኳት፡፡ ምንም እንደማታውቅ እና ኢትዮጵያን በእኔ ምክንያት ብቻ እንደምታውቃት ነገረችኝ፡፡ ስለ ኢትዮጵያ ብዙ ማውራት እንዳለብኝ ተረድቼ ከኢትዮጵያ ጂኦግራፊካል አቀማመጥ ጀመርኩ፡፡ በምስራቅዋ የአፍሪካ ቀንድ እንደምትገኝ፤ በአሳዛኝ ሁኔታ የባህር በር እንደሌላት፤ ኤርትራ፣ ኬንያ፣ ሱማሊያ እና ሁለቱ ሱዳኖች እንደሚያዋስኗት፤ ትላልቅ ወንዞች መገኛ እንደሆነች (የአባይን ወንዝ በመጥቀስ)፣ በአፍሪካ ትልቅ የሚባለውን (የህዳሴው ግድብ) እየገነባች መሆኑን፣ ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ያልተገዛች ብቸኛዋ አፍሪካዊት ሀገር መሆኗን ዋና ከተማችን አዲስ አበባ የሚል ትርጉም እንዳላትና የአፍሪካ መዲና መሆኗን፡፡ ድሮ ድሮ በአክሱም ዘመነ መንግስት ኢትዮጵያ የስልጣኔ ጫፍ ላይ እንደነበረች፡፡

ኢትዮጵያ የሰው ልጅ ዘር መገኛ እንደሆነችም ጭምር የህዝብ ቁጥሯም እስከ 90 ሚሊዮን እንደሚደርስ እና ከናይጀሪያ ቀጥሎ በአፍሪካ ሁለተኛ እንደሆነች፡፡ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትም ጥሩ እየሆነ መምጣቱን፡ ፡ ግብር የኢትዮጵያውያን የኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት እንደሆነ፡፡ በኢነርጂ በኩል ኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጫዎች እየገነባች መሆኑን፡፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከአፍሪካ ታዋቂና በአንደኛ ደረጃ እንደሚገኝ፡፡ በዩኔስኮም የተመዘገቡ እና በርከት ያሉ የቱሪስት መስህብ ቦታዎች እንዳሏት፡፡ እንዲህ እንዲህ እያወራኋት በዚሁ ከኪቭ ሱሚ ድረስ ያሉት ከተሞች፤ አስፓልቱን እየነበኘሁ ሄድኩኝ፡፡ አስፓልቱ በጣም ጥራት ያለ እና ልክ ከናዝሬት አዲስ አበባ እንዳለው አይነት አስፓልት ማለት ነው፡፡ ልክ ሱሚ ከተማ እንደደረስን ሌሎቹም የዝግጅቱ አስተባባሪዎች ተቀብለውኝ ወደ ማረፍያ ክፍሌ ወሰዱኝ፡፡ ስለ ሱሚ ከተማ ምን የተለየ ነገር አስተዋልክ ብትሉኝ እንደ ሉሚ እስቴት አረንጓዴ ከተማ አይቼ አላውቅም ነው የምላችሁ፡፡ በመሆኑም በጣም ነው የሚበርደው፡፡

ይቀጥላል....




# ከችሎት መልስ

## መንታፊዋ የቤት ሰራተኛ

በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለከተማ ወረዳ 7 ክልል ልዩ ቦታው አንፎ 75 ቤቶች አከባቢ ሰርካለም ብርሃን የተባለች ግለሰብ በወ/ሮ ፅጌሬዳ ዘርኡ በቤት ሰራተኝነት ተቀጥራ የቤቱ ሐላፊነትም ለተቀጣሪዋ ተሰጥቶ የሚጠበቅባትን ሐላፊነት እንዲሁም የተጣለባትን እምነት ጠብቃ በቤት ሰራተኝነት ሁሉ የተሰጣትን ስራ እንድታከናውን በቤቱ ተሹማ እየሰራች ነው፡፡

ቢሆንም ግን አንድ ቀን የቤትሰራተኛ የሆነችው ሰርካለም ብርሃን እንዲሁም ቀጣሪ አሰሪ ወ/ሮ ፅጌሬዳ ዘርኡ ከሳሽና ተከሳሽ ሆነው ፍርድ ቤት ተገናኝተዋል፡፡

ጉዳዩም እንደሚያስረዳው ተከሳሽ የሆነችው በቤት ሰራተኝነት ተቀጥራ ስትሰራ የነበረችው ሰርካለም ብርሃን በፈፀመችው የስርቆት ወንጀል ተከሳ ነበር ፍርድ ቤት የቆመችው፡፡

ተከሳሿ በተጠቀሰው ቦታ ሐምሌ 24 ቀን 2006 ዓ/ም በግምት ከጠዋቱ 1:20 ሰዓት ሲሆን ንብረትነቱ የቀጣሪ አሰሪዋ የ ወ/ሮ ፅጌሬዳ ዘርኡ ባለ 24 ካራት 63 ግራም የሚመዝኑ የተለያዩ ወርቆች ግምታቸው 60ሺህ ብር የሚሆን ፣በጥሬ ገንዘብ 20ሺህ ብር፣የተለያዩ አልባሳት አጠቃላይ ግምታቸው አራት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር፣እንዲሁም አንድ የውጭ 3ግራም የሚመዝን ብራስሌት ግምቱ 135 ብር የሚገመት ንብረት በሰራተኝነት ተቀጥራ ከምትሰራበት ቤት ውስጥ ቁም ሳጥን በመሳብ አውጥታ የወሰደች መሆኑን የተከሳሿ መዝገብ ቁጥር 396/07 በከባድ የስርቆት ወንጀል መከሰሷን ያስረዳል፡፡

ጉዳዩን የተከታተለው የቤቴል አከባቢ ፖሊስ ጣብያ ከፌዴራል ዐቃቤ ህግ ጋር በመሆን ወንጀሉን በጋራ መርምሮ ያጣራ ሲሆን በፍትህ ሚኒስቴር የኮልፌ ቀራንዮ ፍትህ ጽህፈት ቤት ዐቃቤ ህግ መዝገቡን መርምሮ በ3 የሰው ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃ አስደግፎ የወንጀሉን ክስ ያቀረበ ሲሆን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ኮልፌ ቀራንዮ2ኛ ምድብ ችሎት የቀረበውን ክስ እና ማስረጃ መርምሮ ተከሳሽ ፍርድ ቤት ቀርባ በቀረቡት ማስረጃዎች ጥፋተኛ ሆና በመገኘቷ በወንጀል ህግ አንቀጽ 669/2/ መሰረት በ 7 /ሰባት/ዓመት ከ8 ወር ቀላል እስራት እንድትቀጣ ሲል ነሐሴ 5 ቀን 2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት ብይን ሰጥቷል ሲል የፍትህ ሚኒስቴር ኮሙኒኬሽን ማስተባበሪያ ዘግቧል፡፡

# የሚሊዮኖችን ተስፋ ያስመለመው አዲሱ የባራክ ኦባማ ትዕዛዝ




የዩናይትድ ስቴትሱ ፕሬዚዳንት ባራክ አባማ ከሠሞኑ በአሜሪካ ውስጥ የመኖሪያ ፈቃድ ወረቀት ሣይኖራቸው በስደት ይኖሩ ለነበሩ 4.7 ሚሊየን ዜጎች ፈቃድ መስጠታቸው የዓለማችን ታላላቅ ሚዲያዎች አብይ መነጋገሪያ ሆኖ ሠንብቷል፡፡ ይህ የአባማ ዕቅድ በሚሊየን ለሚቆጠሩ በህገወጥ መንገድ የሚኖሩ ስደተኞች ለሥራ የማመልከት ዕድል የሚሠጥ ቢሆንም ከዚህ ዕድል ተጠቃሚ ያልሆኑ ሌሎች በሚሊየን የሚቆጠሩ ሰዎችም አሉ፡፡ የፕሬዚዳንቱ ዕቅድ የሪፐብሊካን ፓርቲ አባላትን በከፍተኛ ደረጃ ያስቆጣ ቢሆንም እርሣቸው ግን ውሳኔያቸው አዲስ ነገር አለመሆኑንና ከእርሣቸው በፊት የነበሩት የዲሞክራትም ሆኑ የሪፐብሊካን ፓርቲ ፕሬዚዳንቶች ያደረጉት የነበረ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ አብላጫውን የምክር ቤት ወንበር የያዙት የሪፐብሊካን ፓርቲ አባላት ‹‹ይህ የአባማ ውሣኔ ህገመንግሥቱን የጣሠና ከሥልጣናቸው በላይ የተደረገ ነው›› ሲሉ ተቃውሟቸውን ቢያሠሙም ‹‹የስደተኞችን ሁኔታ በተሻለ መንግስት ለመምራት ባሣለፍኩት ውሳኔ ላይ ጥያቄ ያላችሁ የምክር ቤት አባላት የተሻለ የምትሉትን ህግ ማውጣት ትችላላችሁ፡፡›› ሲሉ ምላሽ ሠጥተዋል፡፡

በሪፐብሊካኑ ፓርቲ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ወግ አጥባቂዎች ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በህገወጥ መንገድ ለሚገቡ ሥደተኞች የሚሠጠውን ወደ ዜግነት የሚያደርስ የህግ ማሻሻያ ይቃወማሉ፡፡ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ፅ/ቤት በበኩሉ በሀገሪቱ የሚታየውን የስደተኞች ችግር ለመቅረፍ ባራክ አባማ የወሠዱት እርምጃ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣናቸውንም በመጠቀም ያደረጉት መሆኑን ገልፆ ከዚህ ቀደም የነበሩት የሪፐብሊካን ፕሬዚዳንቶች ሮናልድ ሬገንና ጆርጅ ቡሽም ተመሳሳይ ውሳኔ አስተላልፈው እንደነበር አስታውሷል፡፡

ፕሬዚዳንቱ በቀጥታ ቴሌቪዥን ስርጭት በተላለፈ መልእክታቸው ባሣለፉት ውሣኔ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በህገ ወጥ መንገድ የሚኖሩት፤ ነገር ግን የሀገሪቱን ዜግነት ያገኙ ልጆች ያሏቸው 4.1 ሚሊየን ወላጆች ቢያንስ ለአምስት ዓመታት አሜሪካ ውስጥ የኖሩ ከሆነ ወደ ሀገራቸው ተይዘው እንዳይመለሱ ከለላና የሥራ ፈቃድ ለማግኘት እንዲያመለክቱ ጠይቀዋል፡፡ የፕሬዚዳንቱ ውሣኔ ስደተኞች የሚገጥማቸውን ችግር በመጠኑም ቢሆን የቀነሠ ቢሆንም በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ከሚኖሩት አሥራ አንድ ሚሊዮን ህገወጥ ስደተኞች ተጠቃሚ የሚያደርገው ከግማሽ በታች የሚሆኑትን ነው፡፡ ‹‹ይህ ለእናንተ የተደረገ ምህረት ሣይሆን ተጠያቂነትን የማስፈን ሥራ ነው›› ያሉት ፕሬዚዳንት አባማ ውሳኔው በሚሊየን የሚቆጠሩ ሰዎች ሥራ ማግኘት እንዲችሉ የሚረዳ ቢሆንም የአሜሪካ ዜጎች የሚያገኟቸውን ጥቅሞች የሚያስገኝ አለመሆኑን ተናግረዋል፡፡ ‹‹ወንጀለኞች ከሆናችሁ ትያዙና ወደ ሀገራችሁ ትመለሣላችሁ፤ ወደ ዩናየትድ ስቴትስ በህገወጥ መንገድ የመግባት ዕቅድ ካላችሁ ተይዛችሁ ወደ ሀገራችሁ የመመለስ ዕድላችሁ ሠፊ ነው›› ሲሉ አስጠንቅቀዋል፡፡

በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የመኖሪያ ፍቃድ ሣያገኙ የሚኖሩ ስደተኞች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በመጨመሩ አሣሣቢ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ከ1990 (እ.ኤ.አ) እስከ 2007 ባሉት ዓመታት ውስጥ ቁጥሩ ከሶስት ነጥብ አምስት ሚሊየን ወደ አስራ ሁለት ነጥብ ሁለት ሚሊየን አሻቅቦ የነበረ ሲሆን የተወሠኑት ስደተኞች ወደ ሜክሲኮ መግባታቸውን ተከትሎ የህገወጥ ስደተኞች ቁጥር ወደ አስራ አንድ ነጥብ ሶስት ዝቅ ብሏል፡፡ በአብዛኛው ወደ ሀገሪቱ የሚገቡት ስደተኞች ከሜክሲኮ የሚመጡ ናቸው፡፡ ከላቲን




በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ  አሥራ አንድ ሚሊዮን ህገወጥ ስደተኞች ይኖራሉ

አሜሪካና ከኤዥያ ወደ አሜሪካ የሚሄዱት ስደተኞች ቁጥርም ከፍተኛ  ነው፡፡ ችግሩ እጅግ አሣሣቢ የሆነባት ዩናይትድ ስቴትስ በ2012 (እ.ኤ.አ) 400,000 ስደተኞችን ይዛ ወደ ሀገራቸው መልሳለች፡፡ በ2013  (እ.ኤ.አ) ደግሞ 396,000 ህገወጥ ስደተኞችን በተመሣሣይ ሁኔታ ወደመጡባቸው ሀገራት ለመመለስ ተገድዳለች፡፡ የዩናይትድ ስቴትስ የሀገር ደህንነት መረጃ በመስከረም አጋማሽና በጥቅምት ወር 2012 (እ.ኤ.አ) ወላጆቻቸው አብረዋቸው የሌሉ 5 ሺህ ህፃናት መገኘታቸውን ነው የሚገልፀው፡፡

የስደተኞች አያያዝ ችግር ላይ መፍትሄ ማምጣት የተሣናቸው የዲሞክራትና የሪፐብሊካን ፓርቲ አባላት የስደተኝነት ህግ የማሻሻል፣ በዩናይትድ ስቴትስ የሚገኙ ስደተኞች ሁኔታ፣ የድንበር ደህንነት አጠባበቅና የትኞቹ ስደተኞች ወደ ሀገራቸው ይመለሱ በሚሉት ጉዳዮች ላይ የጋራ መግባባት ላይ አልደረሱም፡፡ ፕሬዚዳንት ኦባማ «የተሠበረ» በማለት ይገልጹት የነበረውን ይህንን የስደተኞች ጉዳይ ለማስተካከል የወሠዱት እርምጃ «ትልቅ» እንደሆነ ተነግሯል፡፡ የባራክ ኦባማ እርምጃ በዩናይትድ ስቴትስ ድንበሮች የሚፈጠሩ ህገወጥ ስደተኞችን ለመከላከል ወንጀለኞችን ወደ ሀገራቸው ለመመለስና የመኖሪያ ፈቃድ የሌላቸው ጥቂት ስደተኞች የመስራት ነፃነታቸው  ከፍተኛ እንዲሆን የሚያስችል ነው፡፡ የፕሬዚዳንቱ ዕቅድ በዩናይትድ ስቴትስና ሜክሲኮ ድንበር ተጨማሪ ግብዓቶች በማቅረብ በህገወጥ መንገድ ወደ ሀገሪቱ የሚገቡትን ስደተኞች በመያዝ ወደ ሜክሲኮ ለመመለስ እንዲሁም የስደተኞች ጉዳይ ላይ ውሣኔ የሚሰጥ የፍርድ ስርዓት ለመዘርጋት ያስችላል፡፡ ባራክ ኦባማ በዚህ ዕቅዳቸው የብሔራዊ ደህንነታቸው ስጋት የሚሆኑ የስደተኝነት ችግሮችን ለመፍታት፣ ወንጀለኞችን ለመቆጣጠርና የዩናይትድ ስቴትስን ድንበር በህገወጥ መንገድ የሚያቋርጡ የሌሎች ሀገራት ዜጎችን ከሀገሪቱ ለማስወጣት የሚረዱ ትዕዛዞችን ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች ያስተላልፋሉ፡፡

ባራክ ኦባማ ይህን ውሣኔ ተከትሎ በሠዎች ዝውውር ፖሊሲው ላይ ያመጧቸው ሌሎች ለውጦች መኖራቸውን የሚገልጹ መረጃዎች አሉ፡፡ ከለውጦቹ መካከልም የመጀመሪያው የማህበረሰቡን ደህንነት መጠበቅ ነው፡፡ በተቋቋሙት የማህበረሠብ ደህንነት ጠባቂ አካላት በየትኛውም የአሜሪካ እሥር ቤት የሚገቡ ሰዎች የእጅ አሻራ በሠዎች ዝውውር ላይ ለሚሠሩ ኃላፊዎች ተላልፎ ይሠጣል፡፡ ይህን መረጃ በመጠቀም የወንጀል ተግባር ላይ የተሠማሩ ስደተኞችን በቀላሉ ለመያዝ ይቻላል፡፡

የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት በሣይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በምህንድስና እና በሒሣብ የትምህርት ዘርፎች ለሁለት ዓመት ከመንፈቅ ሠልጥነው የሚመረቁ በርካታ ተማሪዎችን ይፈልጋል፡፡ በእነኒህ ሙያዎች የተመረቁ ተማሪዎች ለአስራ ሠባት ተጨማሪ ወራት በአሜሪካ ለመቆየት የማመልከት መብት አላቸው፡፡ በዚህ ፕሮግራም ውስጥ የታቀፉ ከ100,000 እስከ 200,000 የሚደርስ ቁጥር ያላቸው ስደተኞች ይገኛሉ፡፡ እንዲያውም ይህ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ከአስር ሺህ እስከ ሠላሣ ስድስት ሺህ የሚደርስ ቁጥር ያላቸው ባለሙያዎች ከተለያዩ የውጪ ሀገራት ለመቀበል ያስችላል፡፡ ስለዚህ የባራክ ኦባማ አዲስ ውሣኔ ለስደተኞች ፈቃድ በመስጠት ስደተኞች ተረጋግተው በሀገሪቱ እንዲሠሩ ያደርጋል፡፡

# ስወላጆች



## እናት ጡት ማጥባት

ለጨቅላ ህፃን ከእናት ጡት የተሻለ የተስተካከለ እደሌለ አያከረክርም እንዲውም ምትክ የለሽ ነው፡ የእናት ጡት ወተት ለህፃናት ተስማሚ በቀላሉ የሚሰለቀጥና የማይጎረብጥ ነው፡፡ እመጫቶች ከ4 እስከ 6 ወር ድረስ ህፃናት ልጆቻቸውን ለመጀመሪያው ሙሉ በሙሉ እንዲያጠቡ ይመከራል፡፡ በዚያ ላይ የእናት ጡት ፀረ- ተህዋስ ተፈጥሮ ስላለው ከበሽታም ይከላከላል፡፡ ይልቁንም የእናታቸውን ጡት የጠቡ ህፃናት የተሻለ የአእምሮ ብስለትን ገና በጨቅላነታቸው እንደሚታደል፤ በጥናት ተደርሶበታል፡፡

### ተጨማሪ ወተት መስጠት (የላም ወይም የዱቄት ወተት)

ህፃን እንደተወለደ ለመጀመሪያዎቹ 5 እና 6 ወራት ከእናት ጡት ሌላ ተጨማሪ ወተት በመሰረቱ አያስፈልገውም፡፡ ነገር ግን የህፃናት ሀኪሞች አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት የላም ወይም የዱቄት ወተት አክለው ሊሰጡት ይችላሉ። ተጨማሪው ወተት በኩባያ ወይም በሲኒ መቅረብ አለበት እንጂ በጡጦ አይመከርም፡፡ ጡጦ መጥባት ብክለትን ፣የአንጀት ህመምን እና ቅርሻ ሊያስከትል ይችላል፡፡

## ጠጣር ምግብ ማስለመድ

ጨቅላ ህጻናት ጠና እንዳሉ የወተት መጠን እየቀነሰ የዛኑ ያህል ወስፋታቸው እስከተቀበለና  ድረስ ለስለስ ያለ ጠጣር ምግብ መልመድ አለባቸው፡፡ ለህጻናት ቢያንስ ለመጀመሪያዎቹ 4 ወራት ሙሉ ለሙሉ የእናት ጡት አስፈላጊ እንዳለ ሆኖ ከዛም በተጨማሪ ወተትና ለስለስ ያሉ ጠጣር ምግቦች ያስፈልጋል፡፡ ይሁን እነጂ የእናት ጡት ማጥባቱ በትንሹ ለአንድ ዓመት ያህል መቀጠል አለበት

### ህፃናትን ጠጣር ምግብ ለማስለመድ የሚያግዝ የተግባር

ከፍራፍሬ ፣ከጥራጥሬና ከቅጠላ ቅጠል ፈሳሽ ምግብ ማዘጋጀትና መመገብ ይቻላል፡፡ ብዛቱን ሆነ ጥጣሬውን እነደ  ልጁ ዕድሜና ፍላጎት መጨመር ይቻለል፡፡ ጠጠር ያሉ ምግቦችን የበለጠ የምግብ ይዘት ያላቸውና ኃይል ሰጪ ስለሆኑ ቀስ በቀስ ጭማቂዎችንና ሾርባዎችን የመሳሰሉ ፈሳሽ ምግቦችን መተካት አለባቸው ፡፡ ልዩ ልዩ ምግቦች ግን አንዳንዱን ተራበትረ በየሁለት ሳምንቱ እየቀያየሩ ማቅረብ /መስጠት/ መመገብ ይገባል ፡፡

ጨቅላ ህፃናት  በአብላጫው ሙዝ  ስለሚወዱ ጠጣር ምግብን በሙዝ ማለማመድ ይቻላል፡፡ ቤት የተዘጋጀ አጥሚትና ገንፎ በወተትና በስኳር መብረዱን አረጋግጦ ለጨቅላ ሕፃን መስጠት ይጠቅማል፡፡ሩዝና ቅንጬም  ህፃኑ 6 ወር ከሞላው በኋላ ማብላት ይቻላል፡፡አታክልትንም በመቀቀል አብስሎ በተጫማሪ አካትቶ ማቅረብ ደህና ነው፡፡

-ማን ጤነኛ ህፃን ከ10 እስከ 12 ወራ ዕድሜው ያገኘውን መብላት ይኖርበታል፡፡ ከዚያም ጡት ማጥባን ዝግ ብሎ በ10 ወራ ውስጥ ማቋረጥ ተገቢ ነው፡፡

-እንድ ህፃን መቀመጥ እስከቻለ ድረስ በኩባያ ወይም በብርጭቆ ማጠጣትን መለማመድ ይችላል ፡፡ ዕድሜው እንድ አመት ለሞላ ህፃን ወተት ይሄን ያህል አስፈላጊ አይደለም መደበኛ ምግቡ እንደ አቅሙ ጠጠር ወይም ለስለስ ይበል እነጂ አዋቂ የሚበላውን ዓይነት መሆን አለበት፡፡

ምንጭ ፡- ሪም የህፃናት ሞግዚት ማሰልጠኛ ተቋም

# አንዳንድ ነገሮች

**‹ማሪያም ሳመችኝ›**

ይህን ቃል የምናውቀው በተለምዶ ሰውነታችን ላይ በሚወጣ ጥቁር ጠብታ መሰል ምልክት ምክንያቱን ስንጠየቅ ወይም ራሳችንን ስንጠይቅ ‹ማሪያም ስማኝ› ነው የሚለውንም ላሽ እንሰጣለን፡፡ የቆዳ ህክምና ባለሙያዎች ግን ይህ የሚፈጠረው እንዲህ ነው ይላሉ........

ይህ ጥቁር ነጥብ የመሰለ ምልክት በቆዳችን ላይ የሚፈጠረው ለሰውነታችን ከለር የሚሰጡን ንጥረ ነገሮችን (pigment) የያዙ ሴሎች ያለ ተገቢ ሁኔታ ሲሰራጩ የሚፈጠር ነው ይላሉ፡፡ አንድ ህጻን በተወለደ በጥቂት ሳምንት በኋላ ፊቱ ላይ ትንሽ እንጆሪ መሰል ቀለም ያለው ነጥብ ቢወጣበት ቤተሰቡ ብዙም አትክሮት አይሰጠውም ፡፡ይህ እንጆሪ መሰል ነጥብ ከስድስት ወር በኋላ እየደመቀና ቡናማ ከለር እየያዘ ይሄዳል፤ ከዛም ብዙ ጊዜ ልጁ አራት ወይም አምስት አመት ሲሞላው ይጠፋል፡፡

የተለያዩ አይነት የማሪያም ምልክቶች ሲኖሩ የተወሰኑት ቆይተው የሚጠፉ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ የማይጠፉ ናቸው፡፡ ከጊዜ ቆይታ በሃላ የሚፈጠሩት የማሪያም ምልክቶች ብዙውን ጊዜ ትንሹ የደም ቧንባ ያላግባብ ሲሰበሰብ ነው፡፡ ሁለተኛውና ለረጅም ጊዜ ወይም እስከመጨረሻው አብሮን የሚቆየው የማሪያም ምልክት ደግሞ መጠኑ ተለቅ ያለ ሲሆን ሜላኒን የተባሉ በሰውነታችን ውስጥ የሚገኝ ንጥረ ነገር አንድላይ በመከማቸቱ የሚፈጠር ነው፡፡

# ስፈገግታ

**‹አሯሩጪኝ !›**

አንዲት ወጣት የታመመ መዘመዷን ለመጠየቅ ወደ እብዶች ሆኪም ቤት ትሄዳለች፤ ወጣቷ የምትጠይቀውን ዘመዷን ፍለጋ በሆስፒታሉ ጊቢውስጥ ስትዟዟር ድንገት አንዲት የአዕምሮ በሽተኛ ትመጣባታለች፤ ወጣቷ የአዕምሮ በሽተኛዋ ሁኔታዋ ስላስፈራት በድንጋጤ ያለ የሌለ ኃይሏን ተጠቅማ መሮጥ ትጀምራለች ፡፡ የፈራችውም አልቀረ! የአዕምሮ በሽተኛዋ ተከትላ ታሯሩጧት ጀመር፤ ጊቢው ውስጥ በመሯሯጥ ብዙ ከቆዩ በኋላ ወጣቷ የመሮጥ ሀቅሟን ጨርሳ ትወድቃለች፤ የአዕምሮ በሽተኛዋም አጠገቧ ትደርስና ቆም ብላ ቁል ቁል እያየቻት «በይ ነይ ደግሞ አንቺ በተራሽ አሯሩጪኝ !» ብላት እርፍ!!!

**‹ስማቸው ተስፕፏል!›**

ሁለት የእንሰሳት ህክምና ተማሪዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድ የከብት እርባታ ጣቢያ ለልምምድ ይሄዳሉ፡፡ የመጀመሪያው ቀን ከብቶቹ መስክ ላይ ሣር ሲግጡ ከዋሉ በኋላ ወደ ማደሪያ ቤታቸው ሲገቡ ያያቸው አንደኛው ተማሪ......

‹አይገርምም !እያንዳንዷ ከብት ማደሪዋን በትክክል አውቃ መግባቷ!›ሲል ጓደኛውን ይጠይቀዋል?

ጓደኛው ነገሩን ቀለል አድርጎ ‹ምኑ ነው የሚገርመው ?እያንዳንዳቸው ማደሪያ ላይ ስማቸው ተለጥፎ የለም? ብሎት እርፍ!!!!!

# ቅኔ

- ምን ያሉ ቄስ ናቸው የማይጠብቁ ዕቃ
  ከቤተክሲያን ጓሮ ዕጣኒቱ ወድቃ፡፡
- መባህ ለምን ቀረ አይበሉኝ ቄስ ስዩም፣
  ሰጥቻለሁና መባ ከኔ አልቀረም፡፡
- ተናግሬ ነበር ሊመጣ ነው ብዬ
  አውቄ እንኳ አይደለ እንዲያው መላ ጥዬ፡፡
- በጣም ደስ ይለኛል በዓል ሲከበር ፣
  ተኮት ኩታ ሲሆን በሀገር ባህል፡፡
- ምን ይሻላት ይሆን ያቺ ቆንጆ ሴት፣
  በጣም የምትወደው በጓ እዳ አስገባት፡፡
- ምን ጊዜ ነግዳ ምን ጊዜ አገኘችው፣
  ከቤተክሲያን ጓሮ መሬት የገዛችው፡፡
- ዶሮም ያረዳችሁ ቆቅም የያዛችሁ
  እቤቴ ላኩልኝ ከንፉን እባካችሁ፡፡

# አፈምባና ቆቦ

| | |
|---|---|
| ቀልደኛ ገበሬ | - በሰኔ ይሞታል |
| | - አሸባሪ ተባለ |
| ውሃ በለዘብታ | - ድንጋይ ይፈነቅላል |
| | - መች ይዳረሳል |
| ወስፌ ሲለግም | - ቅቤ አይወጋም |
| | - ኔቶርክ ይጠፋል |
| ሲሞቱ ዘመድ | - ሲገዙ ገመድ አይታጣም |
| | - መግለጫ ይሰጣል |
| የኑቶሎ ቶሎ ቤት | - ግርግዳው ሰንበሌጥ |
| | - በስልጣና ይገነባል |

ቢፍቱ ባይሳ /ከገላን/

| | |
|---|---|
| የትም ፍጭው | - ዱቄቱን አምጭው |
| | - ስኳሩን ግን አምጭው |
| መራጭ | - ይወደወቃል ከምራጭ |
| | - ምርጫ ደረሰለት |
| አተርፍ ባይ | - አጉዳይ |
| | - ባክሲዮን ይበላል |
| የቸኮለች | - አፍሳ ለቀመች |
| | - ሰላማዊ ሠልፍ ጠራች |

አዳሙ ይጽና ክ/ኮተቤ/

# ጠቅሳሳ ዕውቀት

## ለካስ በላይ ኖሯል

አንድ ግለሰብ በቅሎ ጠፍታበት ሲፈልግ ሊያገኛት ስላልቻለ የአካባቢው ኗሪ ሕዝብ ተሰብስቦ ሌባውን እንዲያወጣለት ይጠይቃል፡፡ ሕዝቡ ተሰብስቦ ሌባውን እንዲያጋልጥ ይደረጋል፡፡ ከተሰበሰበው ሕዝብ መካከል በቅሎውን የሰረቀውን ሌባ የሚያውቁት ስለነበሩ «በላይ ነው» ብለው አወጡት፡፡ በመጨረሻም በቅሎው የተሰረቀበት ግለሰብ የሚከተለውን አለ ይባላል፡፡

በታችኛው መንገድ ስከታተለው
ለካስ «በላይ» ኖሯል ስቦት የሔደው
ተመስገን ስብሐት-ከባህር ዳር

# ምርጥ አባባሎች

‹ሰው በተፈጥሮው ፖለቲካዊ እንስሳ ነው፡፡ በልማድ ግን አውሬ›

/አርስቶትል/

‹ዕድል አንዳንዴ በአንዳንድ ሰዎች ከንፈር ላይ ጤዛ ትሰራለች ፡፡ አንዳንድ ሰዎች አጠገብ ደግሞ ተሽኮርምማ ታልፋለች፤አንዳንዶቹን ከተኙበት ገብታ አቅፋቸው ትገኛለች፡፡›

/ፍራንሲስ ባኮን/

‹ጎበዝ የምንለው አንድን ነገር ከተለመደው መንገድ በተለየ ሁኔታ መቀበል ችሎታ ያለውን ሰው ነው ፡፡›

/ዊሊያም ጀምስ/

‹በራሳችን ስህተት መሳቅ ህይወታችንን ያረዝማል፤ በሌሎች ስህተት መሳቅ ግን ያሳጥራል፡፡›

/ቶማስ ኤዲሰን/

‹ትክክለኛ ዕውቀት ወደ ውስጣችን እንደገባ ብቻውን ደስታ ይፈጥራል፡፡›

/ፍራንሲስ ባኮን/

‹ቃታው ላይ እጅችህ ካረፉ ለመተኮስ አታመንታ፡፡›

/አርተር ጀምስ ሳልፎር/

‹እንስሳት ምቹ ጓደኞች ናቸው፡፡ አይጠይቁም አይሄዱም፡፡›

/ጆርጅ ኢሊየት/

‹ቅዱስ ይበሉህ ፈላስፉ! ግን ሰው ሁን›

ለምትከራከሩኝ ሁሉ ክርስቶስ በርግጥ እንደኛ ‹ሰው›ነበርን ? ከሆነ ታዲያ ክርክሩን ትተን ለምን እንደሱ ለመሆን አንጣጣርም?

/ማቲው አርኖልድ/

# የትኛው ቬሎ ይስማማሻል?



የሠርግ ሥነ-ሥርዓት የተቃናና የደመቀ እንዲሆን አስቀድሞ መዘጋጀት ወሳኝ ነው፡፡ አስቀድሞ የታሰበበት ሠርግ የተሳካና ያማረ ለመሆኑ አያጠራጥርም፡፡ የሠርግ ነገር ሲታሰብ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ነገሮች አንዱ የሙሽሪት ቬሎ ነው፡፡ ሙሽሪት ቬሎዋ ከሠርጓ ስድስት ወር አስቀድማ መምረጥ ይኖርባታል፡፡ ከሠርጓ ሁለት ሳምንት በፊትም በእጇ ልታስገባ ይገባታል፡፡

ሙሽሪት ቬሎዋን ከመግዛቷ ወይም ከመከራየቷ በፊት የትኛው እንደሚስማማት እንደሚማርካት መወሰን ይገባታል፡፡ በየቬሎ ቤቱ በመሄድ በርካታ ምርጫዎች ልትመለከት ትችላለች፡፡ ምርጫዋን ከያዘች በኋላ ምን ማድረግ ይገባታል?

በመጀመሪያ የሠርጓ ሥነ-ሥርዓት በምን መልኩ እንደሚከናወን ልታወቅ ይገባል፡፡ ምክንያቱም የቬሎ መግዢያ ወይም መከራያ ዋጋ ውድ በመሆኑ ለፕሮግራሙ የሚስማማውን የቬሎ አይነት ልትወስን ይገባታል፡፡ ለምሳሌ የሠርግ ሥነ-ሥርዓቷ በቤተክርስቲያን የሚከናወን ከሆነ እጃቸው ጉርድና ግልጥ ቬሎዎች ተቀባይነት ላይኖራቸው ይችላል፡፡የሠርጓ ሥነ-ሥርዓት ቀለል ያለ እንዲሆን ከፈለገች የምትመርጠው የቬሎ አይነት የተለየ ይሆናል፡፡

የሠርጓ ዕለት በየትኛው ወር እንደሚከናወን ማወቁ አስቀድሞ ከግምት ውስጥ ሊገባ ይገባዋል፡፡ በአገራችን የሚያዝያ ወር የሠርግ ወቅት ቢሆንም የበልግ ዝናብ የሚኖርበት በመሆኑ ሙሽሪት ቅጥያና ተጎታች የሌለው ወይም ተጎታቹ የሚነቀል ቬሎ ልታደርግ ይገባታል፡፡ ይህም ቬሎዋ በጭቃ እንዳይበላሽ ይረዳታል፡፡ እንዲሁም ከጀርባቸው በጣም ክፍት የሆኑ ቬሎዎች በዝናብ ወቅት ለብርድ ያጋልጣሉ፡፡

ቬሎን በመምረጥ ሂደት ሌላው ወሳኝ ነገር የሙሽሪት የአካል ሁኔታ ነው፡፡ ርዝመት፣ እጥረት፣ ውፍረትና ቅጥነት ቬሎን ለመምረጥ ወሳኝነት አላቸው፡፡ ከሰውነት ጋር የሚሄድ ቬሎ ለሙሽሪት ድምቀትን ይሰጣል፡፡ የቬሎ አይነቶች ቅርፅ፣ ቡፍያለና ክብ ባለተጎታች በመባል ይታወቃሉ፡፡ ኤ ቅርፅ ያለው ቬሎ ለማንኛዋም ሴት የሚስማማ ነው፡፡ ቡፍና ክብ ያለው ሙሽሪት ጎላ ረዘም ብላ እንድትታይ ያደርጋታል፡፡

## ለአጭር ሴት

አጭር ሴት አንገቱ በጣም ክፍት ያልሆነ፣ ወገቡ ያወረደና አጭር እጅጌ ወይም ባካውት የሆኑ ቬሎዎች ይሰማሚታል፡፡ ተጎታች ያለው ቬሎ ለአጭር ሴት አይመከርም፡፡ እንዲሁም አጭር ሻሽ ልታደርግ ይገባታል፡፡ በጣም ቡፍ ያለ ቬሎዎች አጭር ሴትን ይበልጥ አጥራ አንድትታይ ሰስሚያደርጋት ምርጫዋ ባይሆኑ ይመረጣል፡፡ ረዘም ብለው ጠበብ ያሉ ቬሎዎች ለአጭር ሴት ተመራጭ ነው፡፡

## ለረጅም ሴት

ረጅም ሴት አጠር ብላ አንድትታይ ወገቡ ወረድ ያሉና ቡፍ ያሉ ቬሎ ልትመርጥ ይገባታል፡፡ ሰፊ ቬሎ ሙሽሪት ወደጎን ሰፉ ብላ እንድትታይ ስለሚያደርጋት ቁመቷን ይከተዋል፡፡ አንገቱ ከፍ ያለና ፒትልስ ቬሎዎች ለረጅም ሴት አይመከርም፡፡ ባካውትና ማንገቻ የሌላቸው ቬሎዎች ለረጅም ሴት ተመራጭ ናቸው፡፡ እጀሙሉ ቬሎዎችም እንዲሁ ለረጀም ሴት ተስማሚ ናቸው፡፡ ረዘም ያሉ ሻሾችም ለረጅም ሴት ይስማማል፡፡

## ለመካከለኛ ቁመትና ውፍረት

መካከለኛ ቁመትና ውፍረት ያላት ሙሽራ የትኛውም አይነት ቬሎ ይስማማታል፡፡ ፋሽን ሆኖ የመጣውን ቬሎ ብትለብስ ደምቃና አምራ ልትታይ ትችላለች፡፡ በቬሎ ምርጫዋ ላይ ምንም ተፅዕኖ አይኖርባትም፡፡

## ለወፍራም ሴት

ወፍራም ሴቶች በተለይ ጡታቸው በጣም ትልቅና አንገታቸው አጭር ከሆነ ግልጥና ባካውት ቬ ሎ ዎ ች ን ሊያደርጉ አይገባም፡፡ እንዲሁም ቡፍ ያሉ ቬሎዎች ወፍራም ሴት ይበልጥ ወፍራ እንድትታይ ያደርጋታል፡፡ ወፍራም ሴት በሳተን የተሰሩና ጠበቅ ያሉ ቬሎዎች ምርጫዋ ልታደርግ ይገባታል፡፡ የትከሻዋን ውፍረት ለመሸፈንም ትንሽ እጅጌ ያላቸው ቬሎዎች ብታደርግ ጥሩ ይሆናል፡፡ አንገቷ ወጣ ብሎ አንዲታይ አንገታቸው ገለጥ ያሉ ቬሎዎች ብትመርጥ መልካም ነው፡፡

## ቀጭን ሴት

እንደ መካከለኛ ቁመት ውፍረት ያላት ሴት ሁሉ ቀጭን ሴትን በርካታ የቬሎ ምርጫ አላት፡፡ እንደፓሪ ያሉና ጥብቅ ያሉ ቬሎዎች ቀጨን ሴትን የበለጠ ስለሚያከሷት ብዙም አይመረጡም፡፡ በቲውል የሚሰሩና ቡፍ የሚሉ ቬሎዎች ቀጭን ሴትን ውበት ያላብሷታል፡፡

እንግዲህ ሙሽሪት እነዚህን ሁሉ ነገሮች ከግምት ካስገባች በኋላ መሆን አለበት የቬሎ ምርጫዋ ማከናወን ያለባት፡፡ ከዚህ በኋላ የሠርጓ ዕለት አምራና ደምቃ ትታያለች፡፡



# ማንኮራፋት እና የጀርባ ሕመም



ማንኮራፋት የምንለው በምንተኛበት ጊዜ በመተንፈሻ አካላችን ላይ በሚፈጠሩ ለውጦች ምክንያት በሚመጣ ድምፅ ነው። ማንኮራፋት አብሮ የሚተኛን ሰው ከመረበሽ ባለፈ አንዳንድ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ የጤና እክሎች ምልክት ሊሆን ይችላል፡፡

− ለማንኮራፋት ተጋላጭነት የሚዳርጉ ሁኔታዎች

የሰውንት ክብደት መጨመር፡- በተፈጥሮ የሚኖር ጠባብ መተንፈሻ አየር የምናስገባበት አካል መጥበብ የምንስበው አየር ግፊት እንዲጨምር በማድረግ ድምፅን ይፈጥራል

አልኮል መጠጥ ማብዛት፡- የአልኮል መጠጥ የጉሮሮ ጡንቻዎችን በማፍታታት አየር በሚገባበት ወቅት ርግብግቢት በመፍጠር ድምፅ እንዲጨምር ያደርጋል

በአፍንጫ ላይ የሚከሰቱ ችግሮች፡- በአፍንጫ ላይ የሚኖሩ ተፈጥሮአዊ የአቀማመጥ ችግሮች የማንኮራፋት ዕድልን በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራሉ

- ማናኮራፋት የሚያስከትላቸው ችግሮች

ቀን ቀን የእንቅልፍ ስሜት መሰማት

ብስጭትና ንዴት

ለነገሮች ትኩረት ማጣት

ለደም ግፊትና ለልብ ሕመም ማጋለጥ

በእንቅልፍ እጦት ምክንያት ለሰው ሠራሽ አደጋዎች መጋለጥ

የትዳር አጋርን እንቅልፍ ማሳጣት ናቸው፡፡

- የሚያንኮራፉ ሰዎች

- በእንቅልፍ ጊዜ የሚረብሽ ድምፅ ያሰማሉ

- የቀን እንቅልፍ ሊያስቸግራቸው ይችላል

- የጉሮሮ መከርከር ይኖርባቸዋል

- ሰላም የሌለው እንቅልፍ ያስቸግራቸዋል

- በእንቅለፍ ጊዜ ትንታ እና ትንፋሽ ማጠር ያጠቃቸዋል

- የደረት መጨምደድና የደም ግፊት ሊኖራቸው ይችላል፡፡

- ማንኮራፋትን የምንከላከልባቸው መንገዶች

- አስተኛኘትዎን ያስተካክሉ

በጀርባዎ መተኛት ምክንያት እና ለስላሳ ላንቃዎን ወደ ጉሮሮ እንዲወርዱ ስለሚያደርግ በእንቅልፍ ጊዜ የመርገብገብ ድምፅን እንዳናሰማ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ በጎን መተኛት መፍትሔ ሊሆን ይችላል፡፡

- የሰውነት ክብደትዎን ይቀንሱ

የሰውነት ክብደት የሌላቸው ሰዎችም ቢሆኑ ያንኮራፋሉ፡፡ ነገር ግን ማንኮራፋቱ የመጣው የሰውንት ክብደት ከጨመረ በኋላ ከሆነ መንስዔው ሊሆን ስለሚችል ክብደትዎን ይቀንሱ፡፡

- የአልኮል መጠጥ አይውሰዱ

የአልኮል መጠጥ የምንወስድ ከሆነ በጉሮሮ አካባቢ የሚገኙ ጡንቻዎችን ስለምናፍታታ ማንኮራፋት እንጀምራለን፡፡ ከመተኛታችን በፊት ባለው ከ4 – 5 ሰዓት ጊዜ ውስጥ አልኮል መጠጥን መውሰድ ማናኮራፋትን ያባብሳል፡፡

- የእንቅልፍ ሰዓትዎን ያስተካክሉ

ለረጅም ሰዓታት ያለዕረፍት የሚሠሩ ከሆነ እና በመጨረሻ እጅግ በጣም እራስዎን ካዳከሙ በኋላ የሚተኙ ከሆነ የጉሮሮ ጡንቻዎች ባጣም ስለሚፈታቱ የማንኮራፋት ድምፅ ያሰማሉ፡፡

- አፍንጫዎን ከመደፈን ይከላከሉ

አፍንጫዎ በቅዝቃዜም ሆነ በአለርጂ ምክንያት ከተደፈነ የማንኮራፋት ዕድልን ስለሚጨምር ከመተኛትዎ በፊት በሙቅ ውሃ ገላን መታጠብ በተጨማሪ ውሃ በጨው በማድረግ አፍንጫን ማፅዳት፡፡ ይህ የአፍንጫን ቀዳዳዎች ስለሚከፍት ማንኮራፋትን ይከላከላል፡፡

- ትራስዎን የቀይሩ

በትራስዎ ውስጥ በዓይን የማይታዩ ብናኞች ተከማችተው ሊገኙ ስለሚችሉ መቀየር ተገቢ ነው፡፡

- ፈሳሽ በብዛት ይውሰዱ

ፈሳሽን በብዛት መውሰድ ከአፍንጫችን የሚመነጨውን ፈሳሽ ሰለሚያቀጥን ማነኮራፋት እንዳይኖር ይረዳል፡፡

## የጀርባ ሕመም

የጀርባ ሕመም እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን የኅብረተሰባችን ክፍል እያጠቃ የሚገኝ የሕመም ዓይነት ነው፡፡ በአብዛኛው ይህ ሕመም በዕድሜ የገፉ ሰዎች ላይ የተለመደ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ግን በወጣትነት የዕድሜ ክልል ባሉ ሰዎች ላይም እየተበራከተ ይገኛል፡፡

- የጀርባ ሕመም ለምን ይከሰታል?

የጀርባ ሕመም ከማንኛቸውም የሰው ጀርባን ከሚሰሩ የሰውንት ክፍሎች ሊነሳ ይችላል፡፡

እነዚህም፤

- የጀርባ ጡንቻዎች መሳሳብ (መሸማቀቅ)

- ከባድ ዕቃን ያለአግባብ ለማንሳት



መሞከር

- ድንገተኛ የሆነ ከፍተኛ እንቅስቃሴ
- የዲስክ መንሸራተት
- የመገጣጠሚያ ላይ ኢንፌክሽን
- የአጥንት መሳሳት
- የጀርባ ሕመም ከዕለት ተዕለት የኑሮ ሁኔታችን ጋር ይያያዛል፡፡
- ከባድ ዕቃን በመገፋት ወይንም በመጎተት
- ከባድ ዕቃን በመሸከም ወይም በማንሳት
- ለብዙ ሰዓት በመቆም
- ለብዙ ሰዓታት አጎንብሶ መቀመጥ
- ያለ ዕረፍት ለብዙ ሰዓታት መኪና ማሽከርከር
- የጀርባ ሕመምን እንዴት መከላከል ይቻላል?

- የአካል ብቃት እንቅስቃሴ፡- ኤሮቢክስ የሚባለውን የስፖርት ዓይነት መሥራት የሰውነታችንን አቅም ከመጨመር ባለፈ ክብደታችንን በመቀነስ የጀርባ ሕመም ይከላከላል፡፡

- ሲጋራ ማጤስን ማቆም፡- ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ ሲጋራን የሚያጤሱ ሰዎች በከፍተኛ ሁኔታ ለጀርባ ሕመም ተጋላጭ ናቸው፡፡

- የሰውንት ክብደት መቀነስ፡- የሰውነት ክብደታቸው የጨመረ ሰዎች የጀርባ ሕመም ይኖርባቸዋል፡፡

- የተስተካከለ አቀማመጥ፡- በምንቀመጥበት ጊዜ ጀርባችንን የሚደግፍ እና እጃችንን የምናሳርፍበት ቀጥ ያለ አቀማመጥ መያዝ፡፡

- የተስተካከለ አቋቋም፡- በምንቆምበት ጊዜ የሰውነት ክብደታችን በሁለቱም እግሮቻችን በእኩል መጠን እንዲያርፍ ማድርግ እና ቀጥ ብለን ሳንቆለመም መቆም፡፡

- ክብደት ያላቸውን ዕቃዎች በአግባቡ ማንሳት፡- ክብደት ያላቸውን በምናነሳበት ጊዜ ክብደቱን ከወገባችን/ከጀርባችን ይልቅ በእግሮቻችን ላይ እንዲያርፍ ማድርግ ተገቢ ነው፡ ፡ ዕቃዎችን በምናንቀሳቅስበት ጊዜ ከመጎተት ይልቅ መገፋትተመራጭ ነው፡፡

- ጫማ፡- የጀርባ ሕመም እንዳይሰማን የምንጫማቸው ጫማዎች ምቹ ሊሆኑ ይገባል፡፡

- መኪና በምንሽከረክርበት ወቅት ጀርባችንን መደገፍ፡፡ ለረጅም ሰዓት የምናሽከረክር ከሆነ በየማሃሉ ከመኪና በመውረድ ሰውነትን ማንሳሰቀስና ዕረፍት መውሰድ ተገቢ ነው፡፡

- የአልጋ ፍራሽ ምቾት፡- የምንተኛበት የአልጋ ፍራሽ ቀጥ ያለ መሆን አለበት፡፡

የጀርባ ሕመም ከባድ የሆኑ የጤና ችግሮች ምልክት ሊሆን ስለሚችል በቀላሉ ሊመለከቱት አይገባም፡፡በመሆኑም ከዚህ በታች የሚጠቀሱት ተጫማሪ ምልክቶች ካሉ ወደ ሕክምና ማዕከል በመሄድ መመርመር ያስፈልጋል፡፡እነዚህም፤

- በድንገተኛ የመኪና አደጋ ወይንም መውደቅን ተከትሎ የመጣ የጀርባ ሕመም
- ከወር በላይ የቆየ እና እየባሰ የመጣ የጀርባ ሕመም
- በሕመም ማስታገሻ እና ዕረፍት በመውሰድ ለውጥ የማያመጣ የጀርባ ሕመም
- ከወገብ በታች የመደንዘዝ ስሜት
- ደም የቀላቀለ ሽንት መኖር
- ከፍተኛ ትኩሳት መኖር እና ሆድ ሕመም መሰማት ናቸው፡፡

(በዶክተር ሆነሊያት ኤፍሬም ቱፈር)


# መልካም ጋብቻ HAPPY WEDDING

**ህዳር 7/2007 ዓ.ም**
**የጋብቻ ሥነ-ሥርዓታችሁን ስፈፀማችሁት**
**ለአቶ ኤፍሬም እነዳወቅ እና ወ/ሮ ሜላት አርጋው እንኳን ደስ አላችሁ!!!**
**አበባው ዳምጠውና የደጃች ውቤ ጓደኞችህ**






ቴሌቪዛ የተሠኘው የሜክሲኮ መገናኛ ብዙሃን በትልቅነቱ በላቲን አሜሪካ የመጀመሪያውን ደረጃ ያየዘ ነው፡፡ ይህ ታዋቂ የመገናኛ ብዙሃን ከሚያቀርባቸው የቴሌቪዥን ፊልሞች መካከል በእኛው ሀገር ብሔራዊ የቴሌቪዥን ጣቢያ በየሣምንቱ ቅዳሜ ምሽት እና ረቡዕ የሚተላለፈውና ከፍተኛ ተከታታዮች ያሉት ኩዊዳዶ ኮንኤል ኤንጅል የተሠኘው ፊልም አንዱ ነው፡፡ ፊልሙ  በኢትዮጵያውያን ተመልካቾቹ ዘንድ በአብዛኛው የሚታወቀው ማሪቾይ በተሠኘው የዋና ገፀ ባህርይዋ ስም ነው፡፡ የናታሊ ላርቲሌክስ የቀረፃ ሥራ የሆነው ኩዊዳ ዶ ኮን ኤል ኤንጅል ሜይት ፔሮኒ እና ዊሊያም ሌቪ በሚባሉ ተዋንያን የተወከሉ ሁለት ዋና ገፀባህርያት አሉት፡፡ ሌሎች ስድስት ገፀ ባህርያት ደግሞ ከዋና ገፀ ባህርያቱ በተቃራኒ ተሠልፈዋል፡፡ ፊልሙ በሜክሲኮው ቴሌቪዛ ከሰኔ 9 ቀን 2008 እ.ኤ.አ እስከ መጋቢት 6 ቀን 2009 እ.ኤ.አ የተላለፈ ሲሆን በዓለማቀፍ ደረጃ በሚሊየን የሚቆጠሩ ተመልካቾች ማፍራት ችሏል፤ በአሜሪካም እያንዳንዱ የፊልሙ ክፍል በየዕለቱ ወደ አምስት ሚሊየን የሚጠጋ ተመልካች በማግኘቱ ሪከርድ አስመዝግቧል፡፡

## የታሪኩ መዋቅር

የፊልሙ ሴራ የሚጀምረው ማሪያ ዲ ጂሴስ ወይም ማሪቾይ ከተባለችው ገፀባህሪ ውልደት ነው፡፡ ካቺ ሊያ ቬላርዴ የተባለች እናቷ ህፃን ልጇን  አባ አንሴልሞ ለተባሉ ቄስ በአደራ ትሰጣቸዋለች፡፡ እርሳቸውም ይህቺን ልጅ ወደ እጓለማታውያን ማሳደጊያ ወስደው ይሠጧታል፡፡ ማሪቾይ አስራ አራት ዓመት ሲሞላት ከህፃናት ማሳደጊያ ወጥታ በጎዳና እየኖረች በህይወት ለመቆየት የቻለችውን ጥረት ማድረግ ትጀምራለች፡፡ በርካታ ዓመታትን በጎዳና ታሣልፋለች፡፡ አንድ ቀን በአንድ የሠከረ ሠው የአስገድዶ መደፈር ጥቃት ይደርስባታል፡፡ እርሷ ከድህነቷ ባሻገር ድንገት ጥቃቱን የፈፀመባትን ሠው ማንነት ባለመለየቷ የህግ ያለህ ለማለት አልደፈረችም፡፡

ይልቁንም በዚህ ምክንያት በተደጋጋሚ ቅዠቶች ተሠቃየች፤ ወንድ የተባለ ፍጥረት ሁሉ አጥብቃ ጠላች፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለች ነው ካንዴላርያ የተባለች ልብስ አጣቢ ከጎዳና አንስታት ወደ ቤቷ በመውሰድ ማሪቾይን እንደ ልጇ መንከባከብ የጀመረችው፡፡

ማሪቾይ ወደ ካንዴላሪያ ቤት ከመጣች በኋላ እርሷን ለመርዳት ያልተለመዱ ነገሮች ትሠራ ነበር፡፡ አብዛኛውን የእረፍት ጊዜዋን የምታሣልፈው የተለየ ፀባይ ካላቸው ጓደኞቿ ጋር ነው፡፡ አንድ ምሽት የማሪቾይ ጓደኞች የመሠረቱት ቡድን በፖሊስ ቁጥጥር ስር ዋለ፡፡ ከቡድኑ አባላት ጋር ተይዛ የሄደችው ማሪቾይ ግን አንዳች ክስ ሣይቀርብባት ዶክተር ጁዋን ሚጉዌል ሳን ሮማን በተባለ የስነ አዕምሮ ባለሙያ ከእስር ተለቀቀች፡፡ በሌላ በኩል ዶክተር ጁዋን ሚጉዌል በጋሬጣ የተሞላ ትዳሩን ወደ መልካም ጎዳና ለመመለስ ቪቪያና ከተባለች ባለቤቱ ጋር ሚያሚ አካባቢ ጉዞ ያደርጋል፡፡ በጉዟቸው ላይ አውሮፕላኑ ተከስክሶ የዶክተሩ ሚስት እንደሞተች ይታመናል፡፡ እርሡ ግን ከተረፉት መካከል አንዱ መሆን ቻለ፡፡ ቪቪያና እንደታመነው ሳትሞት ቀርታ ህይወቷን በነፃነትና በቅንጦት መኖር ትቀጥላለች፡፡

ማሪቾይ ከቀናት በኋላ በታሠሩ አርቲስት ጓደኞቿ ምክንያት የተሰማትን ሀዘን ለመግለፅ ፓትሪቺዮ ቬላርዴ ወደተባለው ዳኛ በመሄድ የቤቱ መስታወት ላይ ድንጋይ ትወረውራለች፡፡ በኋላም ከጎረቤቶቿ ሠርቃ ወደ ወላጅ አልባ ህፃናቱ በወሠደችው ወተት ምክንያት ትያዛለች፡፡ በዚህ ጊዜ የቤቱ መስታወት በማሪቾይ የድንጋይ ናዳ ሲወርድበት የነበረው ዳኛ  ማሪቾይን ወደ እስር ቤት ያስገባታል፡፡ ነገር ግን የስነ አዕምሮ ባለሙያው ጁዋን ሚጉዌል እንደገና ይመጣና ማሪቾይ በምክር የሚመለስ ፀባይ እንዳላት በመግለፅ አስፈላጊውን እንክብካቤ እንደሚያደርግላት ተናግሮ ከእስር ያስፈታና ወደ ቤቱ ወስዶ ማይታ ከተባለች ልጁ፣ አነሊያ ከተባሉ የሚስቱ እናትና ሮቺዩ ከተባለች እህቱ ጋር ያስቀምጣታል፡፡

እንዲህ እንዲህ እያለ በተለይ በማሪቾይና በዋን ሚጉዌል ዛቢያ እየዞረ የሚቀጥለው ታሪክ ፊልሙን ይዞ ይጓዛል፡፡የፊልሙ ታሪክም እጅግ ተወዳጅ ነው፡፡ በውስጡ ፍቅርን፣ መተሣሠብን፣ ጥላቻን ሌሎችንም ሠውኛ ስሜቶች ይዞ ታሪኩ ሣይሠለች እንዲቀጥል በጥሩ ሴራ ተዋቅሯል፡፡ ዛሬም በፊልሙ ላይ ከሚተውኑት ዋነኛ ገፀ-ባህሪያት መካከል በአስቂኝ ፀባዮቿ የምትታወቀውን ላላ የተባለችውን ገፀ ባህሪ ወክላ የምትጫወተውን ኤቪታ ሙኖዝ የሕይወት ታሪክ በመጠኑ የሚያስቃኝ ፅሑፍ እንደሚከተው አቅርበናል፡፡ እኛም የዚህን ተወዳጅ ፊልም ገፀባህርያት የወከሉትን ተዋንያን የህይወት ታሪክ ማቅረብ ከጀመርን ሠነባብተናል፡፡ በዛሬው እትማችንም በፊልሙ ላይ  የተለያዩ ገፀባህርያትን ወክለው ከሚጫወቱት ተዋንያን መካከል የተወሰኑትን የህይወት ታሪክ ይዘን ቀርበናል፡፡

## ሮቺዮ ባንኬልስ ( ኢዛቤላ ሮያስ)



እ.ኤ.አ ሠኔ 22 ቀን 1958 ኑዌቮ ሊዮን በምትባለው የሜክሲኮ ከተማ ተወለደች፡፡ ይህቺ የፖፕ ሙዚቃ ድምጻዊና ተዋናይ በሜክሲኮና በላቲን አሜሪካ በሠራቻቸው የቴሌቪዥን ድራማዎች፣ የመድረክ ቴአትሮችና በርካታ ፊልሞች ከፍተኛ ታዋቂነት አትርፋለች፡፡ የትኛውንም አይነት ሙዚቃ መጫወት የሚችል ድምፅ ካላቸው ሜክሲኳውያን መካከል አንዷ መሆኗ የሚነገርላት ሮቺዮ ባንኬልስ ኦፔሬታ፣ ራንቼራ፣ ሮክ እና ባላድስ በተሠኙ የሙዚቃ ስልቶች ትዘፍናለች፡፡

ራፋኤል ባንኬልስ የተባለው አባቷ የኩባ ተወላጅ ሲሆን ተዋናይ እና ዳይሬክተር ነው፡፡ እናቷ ዲና ዴ ማርኮም በሙያዋ ተዋናይ ነበረች፡፡ ሲልቪያ ፒናል እና ሲልቪያ ፓስኬል የተባሉት እህቶቿም ተዋንያን ናቸው፡፡

እ.ኤ.አ በ1968 ጉቴሪቶዝ በተሠኘው በወላጅ አባቷ የተሠራ ፊልም ላይ ተጋባዥ ተዋናይ በመሆን ነበር ገና በአሥር ዓመቷ ወደ ፊልሙ ዓለም ማልዳ የመጣችው፡፡ ከዚህ በኋላ ሣውንድ ኦፍ ሚውዚክ፣ ግሬስ፣ ኤቪታ እና ጂሠስ ክራይስ ሱፐር ስታር የተባሉ ፊልሞች ላይ ለመሣተፍ ችላለች፡፡ በ1979 እ.ኤ.አ የሠራችው ሎስ ሪኮስ ታምቢየን ሎራን የተሠኘ ተከታታይ የሜክሲኳውያን ፊልም አለማቀፍ ተወዳጅነት ያገኘ ሲሆን ቢያንካ ቪዳል እና ላ ፊኸራ የተሠኙት የቴሌቪዥን ድራማዎችም የወቅት ተጠቃሽ ስራዎቿ ናቸው፡፡

እ.ኤ.አ በ1985 የሙዚቃው ዓለም ጉዞዋን አሀዱ ያለችበትን ሮቺዮ ባንኬልስ የተሠኘ የሙዚቃ አልበም አሣትማለች፡፡ በ1980ዎቹ መጨረሻና በ1990ዎቹ መጀመሪያ በሙዚቃ ሥራ ከቆየች በኋላ ለአሥር ዓመታት ያህል ራሷን ከጥበብ ህይወት አግልላ ነበር የቆየችው፡፡ ከዚያም

በ2006 ኮንታዶፖር አን ሡዌኖ በተባለ ሪያሊቲ ሾው ላይ ተሣትፋለች፡፡ ከአንድ ዓመት በኋላም ‹‹ናቺ ፓራቲ›› የተሠኘ አዲስ የሙዚቃ አልበም አሣትማለች፡፡ ፓሽን፣ ማማሚያ እና ኖቸስ ዲ ካባሬት የተሠኙት ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማዎችና ሾዎች የሮቺዮ አሻራ ያረፈባቸው ነበሩ፡፡ ይህን የሙዚቃ፣ የቴሌቪዥን ድራማዎችና የመድረክ ህይወቷን ከግምት በማስገባት ‹ፓሴዎ ዴላስ ሉሚናሪያስ› የተባለ የሜክሲኳውያን የጥበብ ባለውለታዎች አሻራ የሚቀመጥበት የክብር አደባባይ ላይ ስሟ ሠፍሯል፡፡ በሠራቻቸው የሙዚቃ አልበሞች፣ የሙዚቃ ቪዲዮዎች እና ፊልሞች ያገኘቻቸው በርካታ ሽልማቶችም አሉ፡፡

## የግል ህይወት

እ.ኤ.አ ከ2008-2009 በተላለፈውና ከፍተኛ ተወዳጅነት ባገኘው ኩዊዳዶ ኮን ኤል ኤንጅል በተሠኘ የሜክሲኳውያን ፊልም ላይ ኢዛቤላ ሮያስ የተባለችውን ተቀናቃኝ ገፀ ባህርይ ወክላ ተጫውታለች፡፡


ባንኬላስ ለሁለት ጊዜያት ያህል አግብታ የፈታች ሲሆን ከሁለቱም ትዳሮቿ ያፈራቻቸው አንድ ሴት እና አንድ ወንድ ልጆች አሏት፡፡

## አፍሪካ ዛባላ




የትውልድ ስሟ አፍሪካ ኢቮኔ ሌቹጋ ዛቫላ የሚባል ሲሆን የተወለደችው ነሐሴ 12/1985 (እ.ኤ.አ) የሜክሲኮ ዋና ከተማ በሆነችው ሜክሲኮ ሲቲ ውስጥ ነው፡፡ በሃያ አንድ ዓመት ዕድሜዋ ፔሬግሪና በተሠኘ ፊልም ላይ በመተወን ነው ወደ ጥበቡ ዓለም የገባችው፡፡ በ2006 ኮዲጎ ፖስታል የተባለ ፊልም ላይ የተሣተፈች ሲሆን በ2008 ቴሌኖቫ በሚባለው ግዙፍ የሜክሲኮ መገናኛ ብዙሀን በተሠራውና እጅግ ተወዳጅ በሆነው ኩዊዳዶ ኮን ኤል ኤንጅል የተሠኘ የቴሌቪዥን ተከታታይ ፊልም ላይ ኤልሣ ማልዶንዶ ሣን ሮማን የተባለች ገፀ ባህሪ በመወከል ተውናለች፡፡ ሎ ኤግዚስቶስ ፔሬዝ፣ ፓራ ቮልቨር አማር፣ አሞርቺዮ ኮራዞን እና ኮሮና ዲ ላግሪማስ የተሠኙት አራት ፊልሞች አፍሪካ ዛቫላ ከ2009 እስከ 2012 የሠራቻቸው ፊልሞች ናቸው፡፡

## አብርሐም ራሞስ




እ.ኤ.አ የካቲት 13 ቀን 1974 በሜክሲኮዋ ዋና ከተማ ሜክሲኮ ሲቲ የተወለደው አብርሐም ራሞስ በበርካታ የቴሌቪዥን ድራማዎችና የሜክሲኳውያን ተከታታይ ፊልሞች ላይ ተሣትፏል፡፡ እ.ኤ.አ ከ1995 ጀምሮ እስከ 2011 ድረስ የተለያዩ ተከታታይ ፊልሞችንና የቴሌቪዥን ድራማዎች የሠራ ሲሆን በእኛም ሀገር ከፍተኛ ተወዳጅነት ያተረፈውን ኩዊዳዶ ኮን ኤል ኤንጅል የተሠኘ ተከታታይ ፊልም ጨምሮ ፔሬግሪና፣ ሙጄር ቦኒታ፣ ዶስ ሆጋረስ፣ ሲንቲ እና ካሚላ የተሠኙት ፊልሞች ራሞስ ከተሣተፈባቸው ፊልሞች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ አብርሃም ራሞስ በኩዊዳዶ ኮን ኤል ኤንጅል ፊልም ላይ አድሪያን ጎንዛሌዝ የተባለውን ገፀባህርይ ወክሎ ተጫውቷል፡፡

## ሪካርዶ ብሉሜ



የፔሩ ዋና ከተማ በሆነችው ሊማ ውስጥ ነው ነሐሴ 16 ቀን 1933 (እ.ኤ.አ) የተወለደው፡፡ የቴአትር፣ የሲኒማ እና የቴሌቪዥን ድራማዎች ተዋናይ የሆነው ይህ እውቅ ባለሙያ በበርካታ የሜክሲኮ ፊልሞች ላይ የተወነና የተለያዩ ሽልማቶችም ለማግኘት የቻለ የጥበብ ሠው ነው፡፡ የስፔን ዋና ከተማ በሆነችው ማድሪድ ውስጥ የድራማ ሥነ ጥበብን ከተማረ በኋላ ወደ ፔሩ በመመለስ የካቶሊክ ዩኒቨርሲቲ የቴአትር ተቋምን በመመስረትና በመምራት ታዋቂ ተዋንያንና ዳይሬክተሮችን ለማፍራት ችሏል፡፡

በርካታ ቴአትሮችን በማዘጋጀትና በመተወን የሚታወቀው ሪካርዶ ብሉሜ በ1996 የሠራው ማሪያ የተሠኘ ተከታታይ ድራማ ከስኬታማ ሥራዎቹ አንዱ ነው፡፡ በርካታ ፊልሞች ላይም እንዲሁ አሻራውን አሣርፏል፡፡ በተለይ ኩዊዳዶ ኮን ኤል ኤንጅል የተሠኘው ዝነኛ የሜክሲኳውያን ተከታታይ ፊልም ላይ ፓትሪሺዮ ቬላርዴ የተባለውን ገፀ ባህሪ በመወከል መጫወቱ በእውቅናው ላይ ሌላ እውቅና ያተረፈለት ሲሆን በሥራዎቹም ታላላቅ ሽልማቶች ለማግኘት በቅቷል፡፡

## ቪክቶር ኖሬጋ




የትውልድ ስሙ ቪክቶር ኤንሪክ ኖሬጋ ሄርናንዴዝ የሚባል ሲሆን እ.ኤ.አ ሐምሌ 10 ቀን 1972 ነው የሜክሲኮ ዋና ከተማ በሆነችው ሜክሲኮ ሲቲ የተወለደው፡፡ የጥበብ ዓለም ጉዞውን በሞዴልነት ሙያ የጀመረው ኖጋ በህዝብ ግንኙነት ሙያ የመጀመርያ ዲግሪ አለው፡፡ እ.ኤ.አ ከ1989 እስከ 1998 ድረስ በቆየው ጋሪባልዲ የተሠኘ የሙዚቃ ቡድን ውስጥም ከስምንቱ አባላት መካከል አንዱ ነበር፡፡ የቡድኑ አባላት በ1999 በድጋሚ ተገናኝተው በሠሩት የሙዚቃ ሲዲ ላይ ተሣትፏል፡፡

# የጎዳናው ወግ

**መ**ንገድ ያደርሳል፤ መንገድ ይመልሳል ይሉት ወግ፤ መንገድ ማድረሱንም መመለሱንም የተቸገርንበት ጊዜ ሳይ መድረሳችንን ስመለከት፤ መንገድ ሳያደርስ አድክሞ፤ ሳይመልስ አዝግሞ፤ አናውዞና ተስፋን ነጥቆ፤ የብሶት አደባባይነቱን በማን አለብኝነቱ መያያዙ ለወጋችን መነሻ፤ ለቁም ነገራችን ማዋዛ ሲሆን ቢያስገድደን፤ ይህንን ወግ ሳቀብላችሁ በመንገድ ዳር እገኛለሁ...

(ክፍል 20 )

ሀገሬ የኔ ተስፋ(ከሳፍቶ)

## ‘መሠረታችንን ማን ይሆን የቀማን!?’

### አንዳንድ ነገሮች....ብዙ ይደንቀኛል !!!!!!

መቼም በአሁኑ ጊዜ ስለመሰረት፤ስለደረጃ፤ስለማንነትና ስለምንገነባው ህያውነት መናገር ለአንዳንዶቹ አላዋቂ ያስብል ይሆናል፡፡ ሃሳቡን ማንሳትም ያለፈውን እንደመናፈቅ የሚያስቡም አይታጡም፡፡ያለፈን መናፈቅ ሳይሆን ያለፈን መልካም ነገር ማስቀጠልን መሻት፤መሰረትን ሳይለቁ ፤ደረጃን፤ቀለምን፤ማንነትን፤ልዩነትን፤ተወዳጅነትን፤ብርታትን፤ተመራጭነትን ማሻገር መቻልን መመኘት አልያም መሻትን ነው ማንሳት የተፈለገው፡፡ይህን ፍላጎት የሚሞግቱ ሳይሆን በጭራሹ እንዲነሳ የማይፈልጉ ሰዎችን ማንነት ስንመለከት መሰረት የሚባለውን ወይም መለያ ቀለም የሆነውን የመጉላትና ለየት ብሎ መታዬትን የማይፈልጉ ሁሉም ነገር በድብልቅልቁ ዓለም ተጀብሎ እንዲጎርፉ የሚፈልጉ እንደሚሆኑ ይታመናል፡፡ለጊዜው የሰዎችን ማንነትና ፍላጎት ለጊዜው ገታ ላድርገውና የመሰረታችንን ስር እንድንፈልግ ወይም እንደሚያስፈልገን የተሰማኝን ስሜት በትንሹም ቢሆን ጫሪ ሃሳብ ወርወር ላድርግና መሰረታችንን ማን እንደነጠቀን አብረን እንድንፈልግ የጎዳና ላይ አምዴ ትጋብዛችሁአለች፡፡

በዘመነ ቴክኖሎጂ፤ ዓለም በከፍተኛ ጥድፊያ በሚሮጥበት ዘመን ፤መሰረት፤ስርዓት፤ማንነት (ብራንድ)፤ ቀለም የሚሉት ጉዳይ የገበያ ድርሻቸው ዝቅ ያለ የሚመስላቸው፤ከነፈሰው ጋር አብረው መንፈስን፤በተገኘው ማዕበል ውስጥ አብሮ መጋለብን ትክክለኛ እሳቤ አድርገው የሚያስቡ አይጠፉም፡፡መቼም የቱንም ያህል የገበያ የበላይነትን ለመውሰድ በሚደረግ ግልቢያም ቢሆን መለያ ቀለምን፤ማንነትን በማጉላት ጥራትን ከብዛት ጋር በማምረት የገበያ ድርሻን የማስፋት ካልሆነ በቀር እንደጎርፍ በመጉረፍ የበላይ መሆን እንደማይቻል፤ተመራጭ መሆንም እንደማይቻል ማመን ይገባል፡፡ዓለም አቀፍ ዝናና ስም፤ቀለም ያላቸው ምርቶችን ከዕለት መገልገያ እስከ ሳይንሳዊ ግኝቶች ድረስ ጥራትን ጠብቆ፤መሰረትን ሳይለቁ፤ማንነትን እያጎሉ ይሄዳሉ እንጂ ማንነታቸውን እያፈረሱ እንደማይጓዙ ከ50፤ከ100 እና ከ200 ዓመት በላይ ስማቸውን ተክለው የሚንቀሳቀሱ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎችን ለአንድ አፍታ መመልከት ይጠይቃል፡፡

ወደ አገራችን ስንመለስም አካባቢያችንን በአንክሮ፤ነገሮችን በትኩረት ስንመለከት የመሰረታችንን መጥፋት የሚጠቁመን በርካታ ማሳያ ጉዳዮች ያሉ ይመስለኛል፡፡ከእነዚህ ማሳያዎች መካከል የተወሰኑ ነጥቦችን በማንሳት ሃሳቡን አፍታተን እንመልከተው፡፡

### ትምህርት ቤቶቻችን

በቅድሚያ መሰረት ወደምንጥልባቸው ትምህርት ቤቶቻችን ጎራ እንበል፡፡በእድሜአችን እና ከእኛ ቀደም ባሉ የእድሜ ባለጸጎች ይነገረን በነበረ መረጃ ፤ የተለዩ ክብርና ደረጃ የነበራቸው ትምህርት ቤቶች በመዲናችንም ሆነ በአገራችን ነበሩ፡፡ወደነዚህ መሰረታቸው ያማረና ደረጃ ያላቸው ትምህርት ቤቶቹ ለመግባት ከየክፍለ ሃገሩ የሚመጡ ጎበዝ ተማሪዎች የመግቢያ ፈተና ከመፈተን አንስቶ ፈተናውን በማለፍ ወደ ትምህርት ቤቱ የመግባት፤በትምህርት ቤቱ ውስጥ ራስን ለማቆየት ጎበዝ ተማሪ መሆን ብቻውን በቂ አልነበረም፡፡ የበለጠ ራስን በእውቀት፤በፈጠራ፤በንቁ ተሳታፊነትና የመሪነት ሚና መጫዎት፤በስነምግባር እንዲሁም በልዩ የእውቅና ማማ ላይ መውጣት ይጠይቅ ነበር፡፡መምህራኑም ሆነ አስተዳደሩም ትምህርት ቤታቸውን በእውቀት ልቀት ከፍ ለማድረግ እጅግ የሚተጉ፤የማይዘናጉ እንደነበሩ ይነገራል፡፡ተማሪውም በዚህ ትምህርት ቤት በመማሩና በማለፉ ፤”በዚህ ትምህርት ቤት ነው የተማርኩት” ብሎ ኮራ ብሎ ሲናገር፤መምህራኑም “በዚህ ትምህርት ቤት ነው ያስተማርኩት” በሚል ልዩ ኩራት ይሰማቸው ነበር፡፡ይሄንኑ ዝናና ክብር ትምህርት ቤቱ ይዞ ዘመናትን እንዲሻገር የሚተካኩት መምህራንም ሆነ አስተዳደሩ በቅብብሎሽ ትውልድን እያነጹ የሚቀጥሉ ነበሩ፡፡ ይሄ እድገት በመደበኛው ትምህርት ቤት እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ብቻ ሳይሆን ከዚያም ሲሻገር በዩኒቨርስቲ ደረጃ ያለውም ለስሙ፤ለዝናው፤ለማንነቱ የሚጨነቅ የተለዩ ቀለም ያለው ደረጃው ከፍ ያለ ዩኒቨርስቲም ነበረን፡፡

ይሄው ስም አይጠሬ ዩኒቨርስቲ በአፍሪካ ደረጃ ስሙ የገነነ፤በዓለም ደረጃም ካሉ ዩኒቨርስቲዎች ተፎካካሪና አንቱ የተባለ ፤መሰረቱ የተመሰከረለት ትምህርት ቤት ነበረን፡፡ከአፍሪካ ከእነ ማካራሬ፤አክራ፤ካይሮ የመሳሰሉ ዝነኛ ዩኒቨርስቲዎች ጋር ስሙ ከፍ ያለ ቦታ ነበረው፡፡ በእኛ ዩኒቨርስቲ ለመማር ከአፍሪካ አገሮች፤ከአውሮፓና አሜሪካ ሳይቀር የሚመጡ ነበሩ፡፡በስኮላር ሺፕም ይሁን ራሳቸው ወጪያቸውን በመቻል ለመማር በዚህ ስመ ገናና እና ከፍ ባለ ደረጃ ባለው ዩኒቨርስቲ ለመማር ብዙ ርቀት መጓዝን ይጠይቅም ነበር፡፡ከመጀመሪያው ዓመት አንስቶ የገና ማዕበልን ማለፍ ከፍተኛ እውቀትንና ጥረትን ፤ጎበዝ መሆንን ያስገድድም ነበር፡፡ የዩኒቨርስቲው ደረጃ ከፍ ያለነውና የዚህን ከፍታ ለመወጣት ትጋትን ጠያቂ ነበርና ነው ፡፡በዩኒቨርስቲው የሚሰጠው ትምህርትና ምርምር ደረጃው ከፍ ያለ እንዲሆን የሚተጉ መምህራንና የዩኒቨርስቲው አመማራሮችም ነበሩት፡፡ደረጃው እንዳይወርድ የሚተጉ፤ለስሙ የሚመጥን ትምህርትና ተማሪ እንዲኖረው የሚጥሩ ነበሩት፡፡

### የጦር አካዳሚዎቻችን

የጦር አካዳሚዎቻችንም ላቅ ያለ መሰረት የነበራቸው እንደነበሩ ይነገራል፡፡ለአብነት ያህል የሀረር አካዳሚ እየተባለ የሚጠራውን ስመ ገናና የጦር ትምህርት ቤት ስንመለከት እንኳን ወደ ትምህርት ቤቱ ይገቡ የነበሩት ተማሪዎች ቢኤ ዲግሪ እና ማስተርስ ዲግሪ የነበራቸው እንደነበረ ይታወቃል፡፡ከመደበኛው ዩኒቨርስቲ ዲግሪያቸውን ይዘው ወታደራዊ ሳይንሱን ለመማር የሚገቡበት ትምህርት ቤት ነበረን፡፡በሀረር ጦር አካዳሚ የዚህ ዙር ምሩቅ ነኝ ማለት ምንያህል ደረጃው ከፍያለ እንደነበረ፤ከዚያ የወጣ ምሩቅ ስለሆነ ለዚህ ቦታና ማዕረግ ይመጥናል ሲባል በሙሉ እምነት የሚመሰከርለት እንደነበረ ይነገራል፡፡

በዚያ ትምህርት ቤት የተማሩ ተማሪዎች በወታደራዊ ሳይንሱ እውቀታቸው አንቱ የተባሉ፤በስነ ምግባራቸው የተመሰገኑ፤አገር ወዳድና ህዝብን የሚያገለግሉ እንደነበሩ ያለፉ ታሪኮቻቸውን ማንበብ፤በህይወት ያሉትን ደግሞ ከአንደበታቸው ለማድመጥ እንድንችል ህያው ምስክሮቻችን ናቸው፡፡እነዚህን

ነባርና ዘመናዊ ትምህርት ቤቶቻችንን፤ ዩኒቨርስቲዎቻችንን፤ የጦር አካዳሚዎቻችንን መሰረት ማን ይሆን ያፈረሰብን ? ዛሬ ላይ ሆነን የምንኮራበት፤የምንመካበት የትምህርትና የምርምር ጥራቱ፤የትምህርት ቤቱ ዲሲፒሊኑ፤ከትምህርት ዓለም ሲመረቁ በሙያቸው አንቱ ተብለው ተለይተው በዚህ ትምህርት ቤት የተመረቁ ናቸው እኮ የሚባልለት ትምህርት ቤት እንዳይኖረን ያደረገን ማን ይሆን? ይህንን ማንነት በማጥፋቱስ ያተረፈው ትርፍ ምን ይሆን ? የፖለቲካ ስርዓቱ ቢቀያየር እንኳን ከዘመን ወደዘመን ከነጥራታቸው፤ከራሳቸው ቀለምና ከእውቀት ልቀት ደረጃቸው ሳይወርዱ እንዲሸጋገሩ ማድረግ ለምን ይሆን ያልቻልነው? በሌላው ዓለም እንደምንሰማው ከ300 እና 400 ዓመት በላይ እድሜ ያላቸው ዩኒቨርስቲዎች ትውልድ ቢቀያየር፤የፖለቲካ ስርዓቱ ቢለዋወጥ መሰረታቸውን ሳይለቁ፤የሚያገለግሉት አገርንና ህዝብን በመሆኑ፤የማንነት ቀለማቸውን ሳያደበዝዙ፤በጥራታቸው አንቱታውን እንደያዙ ዘመናትን ሲሸጋገሩ እናያለን፡፡ ለምሳሌ በምዕራቡ ዓለም በዩኒቨርስቲ ደረጃ አንቱ የተባሉ ሁሌም የሚጠሩ እ ንደሀርቫርድ፤ሳምፎርድ፤በርክሌይ፤ካምብሪጅ፤አክስፎ ርድ አይነቶች ዩኒቨርስቲዎች ዛሬም ድረስ ከነዝናቸው መሰረታቸውን ሳይለቁ በትምህርትና ምርምር የልቀት ማዕከላት ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡

የጦር አካዳሚዎቻቸውንም ስንመለከት እንደ ዩናይትድ ስቴትስ ሚሊተሪ አካዳሚ፤ዩናይትድ ስቴት ኔቫል አካዳሚ፤ሮያል ፎርስ ኮሌጅ ክራን ዌል የመሳሰሉትን ማንሳት ይቻላል፡፡እነዚህ ሁሉ ዘመን ተሻጋሪ ተቋማትን ባላቸው ደረጃ ላይ የበለጠ እየተጠናከሩ እንዲሄዱ እንጂ ያላቸውን መሰረት እንዲያጡ አይደረግም፡፡ማንም ያቋቁማቸው፤በየትኛውም ዘመን ይመስረቱ ዋናው ዓላማቸው አገርንና ህዝብን ለማገልገል እስከተመሰቱ ድረስ እነርሱን የማፍረስ ወይም የማድከም አልያም የማባዛት ስራ አይሰራም፡፡ ይህም በመሆኑ ዘመን ተሻጋሪ የእውቀት፤የምርምርና የአማራር ማዕከላት መፍለቂያ ሆነው አገራትን እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡እኛስ የት ላይ ይሆን ያለነው? ይሄ ጥያቄ ነው ሊያሳስበን የሚገባው፡፡

እስኪ ያለፍንባቸውን ትምህርት ቤቶች፤ዩኒቨርስቲዎች፤የጦር አካዳሚዎች ዞር ብለን እናስታውስ፤እውነት ከነዝናቸው፤ከነክብራቸው ይገኙ ይሆን? ለመሆኑ ይህንን መሰረታችንን ማን ይሆን የነቀነቀብን ? ሁሌም ነባሩን አስጠልቶ እኛ ያልጀመርነው አያምርም በሚል ስሌት ከአዲስ እንድንጀምር የሚያደርገን ፤ለትውልድ የሚሸጋገር ተቋም በጥራት እንዳንመሰርት የሚያደርገን የአስተሳሰባችን ጉድለት የት ላይ ይሆን?

## የሃይማኖት ተቋማት

የመሰረታችን ውል ከጊዜ ወደጊዜ እየለቀቀ ከሄዱባቸው ተቋማት መካከል የሃይማኖት ድርጅቶችም(ድርጅቶች ስል ሰማያዊነታቸው እየተዘነጋ ምድራዊነታቸው ቢጎላብኝ፤የገቢ ሰብሳቢ ድርጅት ይመስል ከምዝገባ ጀምሮ ከሁለት ሺህ በላይ እድሜ ያላት ቤ/ክ ሳትቀር እንደሱቅ ወይም ድርጅት የስራ ፈቃድ ለማግኘት በመመዝገባቸው ጭምር ነው) ያላነሰ ይገኙበታል፡፡ ሁሉም በየቤተ እምነቱ የነበረውን መሰረቱን፤ስርዓቱን እየለቀቀ፤የእይታናየይምሰልአይነትእየሆኑለመምጣታቸው ጠጋ ብሎ በመመልከት ማረጋገጥ የሚቻል ይመስለኛል፡፡ለአብነት ያህል የኦርቶዶክስ ተዋህዶን ቤተክርስቲያንን ብንመለከት እንኳን የቱን ያህል መሰረቷን እየለቀቀች መምጣቷ እንመለከታለን፡፡ከቤተክርስቲያኗ መሪዎች ንግግር አንስቶ፤ቋንቋቸውን፤አለባበሳቸው፤የሚይዙት መኪናና መኖሪያ ቤታቸው፤በእለት ከእለት የሚጠቀሙበት ቁሳቁሳቸው እየተለወጠ መሄዱን እንመለከታለን፡፡የህንጻ ግንባታና የንግድ እንቅስቃሴውን፤ መንፈሳዊ ልቀቱ፤ መዝሙሩ፤ ስብከቱ፤ አገልግሎቱ (የመስቀል፤የጥምቀቱ ሳይቀር ትርኢቱ በየጊዜው መሰረቱ እየለቀቀ የታይታ እና በዩኔስኮ የመመዝገብ ጥድፊያ እንጂ መንፈሳዊ አገልግሎቱ ሰማያዊነቱ እየተዘነጋ የቱሪስት መስህብ እየመሰለ መጥቷል) ሁሉ የቀደመውን መሰረት ብቻ ይዞ እየተጓዘ ነው ለማለት አይቻልም፡፡

በእስልምናውም ቢሆን በተመሳሳይ መልኩ መሰረቱን የቆየውን እየዘነጋ በስሜትና በወጣቱ ትውልድ እየተገፋ የሚሄድ አዳዲስ ጉዳዮችንና አስተሳሰቦችን የምንመለከትበት እየመሰለ ይታያል፡፡አብሮ የመኖር ዋጋን እየተጋፋ፤በንግዱ ላይ እምነትን እየለዩ እየሰራ መሆኑን የሚያሳዩ ምልክቶች መታየታቸው፤የስብከቱ፤የመንዙማውና ሌላውም መንፈሳዊ አገልግሎቱ ከጊዜ ወደጊዜ እየተቀየረ መሆኑን እንመለከታለን፡፡በአለባበስ እንኳን ብንመለከት የሴቶቻችን ሁኔታ ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ከህጻናት አንስቶ እስከ እናቶች ድረስ የመቀየር ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ይሄ ቀደም ሲል ያልነበረ በቅርቡ እየተለወጠ የመጣ ይመስላል፡፡

ወደ ፕሮቴስታንት ሃይማኖትም ስንመለከት በተመሳሳይ መሰረቱን እየለቀቀ ለመሄዱ ብዙ ማሳያዎችን ማንሳት ይቻላል፡፡አዳዲስ ህንጻ ላይ አዳዲስ የቸርች ስሞችን በመሰየም በየመንደሩ እንደሰደድ በማስፋፋትና በመክፈት አገልግሎት እንሰጣለን የሚሉ፤ነባሮቹን ቸርቾች የት እንዳሉ የሚያስረሱ፤በየአዳራሹ እና በየአደባባዩ የኮንፍራንሶች ብዛት፤የመዝሙሩ ቅንብር ከዘመናዊ ሙዚቃ መለየት እስኪያስቸግር ድረስ የልዩነት መስመሩ የጠፋበት፤የፓስተሩ ወይም የቸርቿ መስራችና ባለቤት በሃብት ማማ ላይ ሆኖ በሃብት ላይ ሃብት የማከማቸት ሂደቱ፤ባለሃብቶችንና ዝነኞችን እንዲሁም ፓለቲከኞችን በማደንና በማሳመን ተከታይ በማድረግ በሌላኛው ህዝብ ላይ የመማረኪያና የማጥመጃ ስልት አድርጎ የመጠቀሙ፤የስብከቱ፤ሌላም ሌላው ከጊዜ ወደጊዜ ግራ የሚያጋባና መሰረቱን የሳተ የአዳዲስ ክስተቶች ማዕከል እየመሰለ ነው፡፡

ቀደምት የሃይማኖት መሰረቶቻችንን ማን ይሆን የወሰደብን ? የሃይማኖት ተቋማቱን የእምነት ተቋምነትስ ምን ይሆን የነጠቀን? የሃማኖት መሪዎቻችንን መንፈሳዊውን ዓለም ዘንግተው በስጋዊ የሃብትና የፖለቲካ ተገዢ እንዲሆኑ ያደረገ፤አማኙ በእነርሱ ላይ እምነቱን እንዲያጣና አርአያ እንዳይሆኑን ያሳጣን ማን ይሆን? የሚሉትን በእርጋታ እንድንፈትሻቸው ያስፈልጉናል፡፡

## መስሪያ ቤቶቻችን

የመሰረት መናጋት በዚህ ብቻ አይደለም ያጋጠመነን፡፡በመንግስት መስሪያ ቤቶች፤ በሲቪል መስረያቤቶቻችን፤በመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም ሆነ በግል የስራ ቦታዎችም ያለው የዚያኑ ያህል ተናግቶብናል፡፡ቀደም ሲል የዚህ መስሪያ ቤት ሰራተኛ ነኝ ከሚለው ሰራተኛ አንስቶ፤”አቶ እከሌ እኮ በዚህ መስሪያ ቤት በዚህ የሃላፊነት ቦታ ላይ ለዚህን ያህል ዓመታት መስሪያ ቤታቸውንና አገራቸውን በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል “ሲባል የሚሰጠው ኩራት ልዩ ነበር፡፡ለአብነት አንዳንድ መስሪያ ቤቶችን ብናነሳ እንኳ አቶ እንቶኔ የአየር መንገድ ሰራተኛ ነው፤የባንክ ሰራተኛ ነው፤የሜድሮክ ሰራተኛ ነው ፤ሙገር ነው የሚሰራው፤አውራ ጎዳና ነው የሚሰራው፤በዩኤን እኮ ነው የሚሰራው፤ኤንጂኦ ነው የምትሰራው የመሳሰሉ አበባሎች የተለመዱ ነበሩ፡፡የመስሪያ ቤቱ ክብር፤የስራ ጸባይና ዝና፤የክፍያ ዝና፤የስርዓት ዝና ተጠቃሽ ናቸው፡፡መስሪያ ቤቶችን እንኳ ስንመለከት ፤ከመስሪያቤቱየአጥርግቢማማርአንስቶየጥበቃዎች አለባበስ ከአቋም ጋር ፤አፈታተሽ፤የሪሴፕሽኒስቶች መረጃ አቀባበል፤የቢሮዎች ንጽህና የእንግዳ መቀመጫ፤የሰራተኛው አለባበስ ፤በጉዳዩ ላይ ያለው እውቀት፤ፈገግታው፤የጉዳይአስተነጋገዱ፤ለደንበኛው የሚሰጠው ጊዜና ውይይት፤የቀጠሮ አሰጣጡ፤የችግር አፈታቱ፤ፍጥነቱ፤ውሳኔው ደግማችሁ ተመለሱ ተመለሱ የሚያስብሉ እንደነበረ ይታወቃል፡፡

ዛሬ ስልጣኔና እውቀት፤ቴክኖሎጂ ባደገበት ዘመን የቆየውን መሰረት ነው ያልነውን ነጥቆ በምትኩ ደካማና እርካታ የማይሰጥ አገልግሎት ሰጪ እንድንሆን መሰረታችንን ማን ይሆን የነጠቀን? በባለሙያ ፋንታ ባለሙያ ያልሆነን በጸሀያና በእሳት እየፈለግን ሰግስገን ስራና ሰራተኛ ሰኔና ሰኞ ሲሆንብን፤እውቀት አልባ ሰራተኞችን፤አመራር አልባ አመራሮችን መድበን ስምና ተግባር ለየቅል ቢሆንብን ይደንቀን ይሆን ? በየብዙሃን መገናኛው የመልካም አስተዳደር ችግርን ለመፍታት እያልን የቱንም ያህል ብንለፈልፍ እየነቀልን የጣልነው መሰረት፤ቀለም፤ ማንነት፤ጥራት፤ብቃትን ልንመልሰው የምንችል አይደለም ፡፡ በየመስሪያ ቤቱ የቢሮክራቲኮች መብዛት፤የሙሰኞች መርመስመስ፤የአቅመ ቢሶች መሰባሰብ፤የስራ ጥራትና ቅልጥፍና ገደል ሲገቡ፤መሰረታችን የነጠከን ከወዴትን ነህ ብለን ብንጮህ ይፈረድብን ይሆን?

# ዕድለ ቢሶቹ የዓለማችን ሠዎች

መጥፎ ቀን ሲያጋጥማችሁና በእድላችሁ ማማረር ስትጀምሩ (የ40 ቀን እድላችሁን ስትረግሙ) ቀም ብላችሁ ስለ አንድ ነገር አስቡ፡፡ ከእናንተ በባሰ ሁኔታ እድል የጠመመባቸው በርካታ ሠዎች አሉ፡፡ ከስራ ስለተባረራችሁ፣ ከፍቅር ጓደኛችሁ ጋር ስለተጣላችሁ፣ የቤት ኪራይ ዋጋ ስለተጨመረባችሁ፣ ከባድ ራስ ምታት ስለያዛችሁ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ጉዳይ ተበሳጭታችሁ የተወለዳችሁበትን ቀን ከመርገማችሁ በፊት ተከታዮቹን ሰዎች ተዋወቋቸው፡፡ በዚህች ምድር ላይ በነሱ ልክ እድለ ቢስ ሰው የለም፡፡

ፍስሐ ጌትነት

## ዴዴ ኮስዋራ

ኢንዶኔዥያዊ ነው፡፡ ሲወለድ እንደማንኛውም ሠው ሙሉ አካል ያለውና ጤነኛ ሠው ነበር፡፡ ነገር ግን የ10 ዓመት ልጅ እያለ አስገራሚ ነገር በህይወቱ ውስጥ ተፈጠረ፡፡ በኢንዶኔዥያ ጫካዎች ውስጥ ሲመላለስ ከዕለታት ባንዱ ቀን ድንገት ወድቆ ጉልበቱ ላይ ትንሽ ቁስል ወጣበት፡፡ ከዓመታት በኋላ ቁስሉ ላይ ያልተጠበቀ ነገር ብቅ አለ፡፡ አረንጓዴ የዛፍ ቅርንጫፍ፡፡ በየጊዜው በተለያዩ የሠውነት ክፍሎቹ ላይ የሚበቅሉት ቅርንጫፎቹ እየበዙ ሄደው የዴዴ ኮስዋራ ማንነት ከሠው ወደ ዛፍ ተቀየረ፡፡ በአካባቢው ነዋሪዎች መዝገብ ላይ ከዛፎች ተርታ ተመደበ፡፡ የትዳር አጋሩ ጥላው ጠፋች፡፡ ቤተሰቦቹ ራቁት፡፡



በኢንዶኔዥያጃቫኑሮውንየመሠረተው ኮስዋራ ከገባበት ችግር ለመውጣት የሃገሩ ዶክተሮች እገዛ ቢያደርጉለትም አልተሳካም፡፡ ዶክተሮቹ በኤሌክትሪክ ማሽን የዛፎቹን ቅርንጫፎች እየቆረጡ ለማስወገድ ቢሞክሩም ተመልሰው ያድጋሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ኮስዋራ ዛፍነቱን አምኖ ሰውነቱን ረስቶ እንደ ጥንታዊ ቦታ በቱሪስቶች እየተጎበኘ ኑሮውን ይገፋል፡፡ የህክምና ባለሙያዎች እንደሚሉት የዚህ ዓይነት ችግር የሚያጋጥማቸው ሰዎች የሉም፡፡ ብቸኛው ሰው ዴዴ ኮስዋራ ነው፡፡ ችግሩ የሚወጣው ፓፒሎማ በተባለ ቫይረስ አማካኝነት ነው ይላሉ፡፡


## ሜሪ ጆይ የልማት ማህበር

የእርስዎ ማንኛውም ድጋፍ (በገንዘብ፣ በቁሳቁስ፣ በአልባሳት…) የህፃናት ድጋፍ(ስፖንሰር ሺፕ) ለአንድ ህፃን 300 ብር በወር፣ የአረጋውያን ድጋፍ (ስፖንሰር ሺፕ) ለአንድ አረጋዊ 300 ብር በወር፣ የድርጅቱ አባል መሆን (ፕላቲኒየም፣ ወርቅ፣ የብር…) ቀጣዩን ትውልድ በመንከባከብና በማስተማር እንዲሁም አረጋዊያን ቀሪ ዘመናቸውን በደስታ ያሳልፉ ዘንድ እያንዳንዳችን ሃላፊነታችንን እንወጣ! በጋራ በምንደግፋቸው ህፃናትና አረጋዊያን ህይወት ላይ ለውጥ እናምጣ!

ማህበሩ አድራሻ:- መገናኛ ከዲያስፖራ አደባባይ ወደ ቶፕ ቪው (የካ ተራራ ት/ቤት) መውጫ 50 ሜትር ገባ ብሎ

ለበለጠ መረጃ ስልክ 0118-96-63-21/22/23 ሞባይል 0911 20 85 18


## ኮስቴስ ሚትሶታኪስ





ሰዴቶ ስፔን ውስጥ የምትገኝ ትንሽ መንደር ናት፡፡ እ.ኤ.አ በ2012 በዚህች መንደር ውስጥ ይኖሩ የነበሩት 71 አባወራዎች ብቻ ነበሩ፡፡ ከነዚህ ሰዎች መካከል አንዱ ኮስቴስ ሚትሶታኪስ ይባላል፡፡ ግሪካዊው ኮስቲስ ወደዚህች መንደር የመጣው የሚወዳትን ሴት ለማግኘት ሲል ነበር፡፡

ግሪካዊው የፊልም ባለሙያ ኮስቴስ በ2012 ከመንደሯ ነዋሪዎች አንድ ጥያቄ ቀርቦለት ነበር፡፡ 950 ሚሊዮን ዶላር በሚያሸልመው የገና ልዩ ሎቶ ሎተሪ እጣ እንዲሳተፍ፡፡ ነዋሪዎቹ ቤት ለመስራት ባቋቋሙት ማህበር ስም ሎተሪውን ለመቁረጥ ሲነሱ ኮስቴስ ግን አሻፈረኝ አለ፡፡ በሚገርም ሁኔታ እጣው ሲወጣ በስፔን ታሪክ በጣም ከፍተኛ የሆነውን የገንዘብ ሽልማት የሚያስገኘውን ሎተሪ ያሸነፉት የሰዴቶ መንደር ነዋሪዎች ነበሩ፡፡ ከመንደሩ ነዋሪዎች የገንዘቡ ተካፋይ ያልሆነው ብቸኛው ሰው ኮስቴስ ነበር፡፡

## ኤሪክ ኖሬ



ክፉ ነገር አያጣውም፡፡ የአሜሪካ ፍሎሪዳ ነዋሪ የሆነው ኤሪክ ኖሬ ያልሆነው ነገር የለም፡፡ እ.ኤ.አ ሐምሌ 29 ቀን 2013 ባሃማስ ውስጥ በሚገኝ ውቅያኖስ አሳ ሲያጠምድ ያልታሰበ ነገር ገጠመው፡፡ እግሩ በሻርክ ጥርስ ተያዘ፡፡ በቦታው የነበረው የሚስቱ አባት ወደ ውሃው ዘሎ በመግባት በከፍተኛ ትግል ከሻርኩ ባያድነው ኖሮ ህይወቱ ለማለፍ ተቃርባ ነበር፡፡ በንክሻው ምክንያት በርካታ ደም ከሠውነቱ የፈሰሰው ኤሪክ በሃኪሞች እገዛ ከሞት ተረፈ፡፡

ከዚያ አደጋ በኋላ ታዲያ ኤሪክ ለጋዜጠኞች አንድ እውነት ነገራቸው፡፡ ‹‹ህይወቴ ሁሌም ለትላልቅ አደጋዎች የተጋለጠ ነው›› አላቸው፡፡ እሱ እንደሚለው ከዚያ በፊት በመብረቅ ደጋግሞ ተመቷል፡፡ እንዲሁም በአደጋኛ መርዘኛ እባብ ተነድፎ ከሞት ለጥቂት ተርፏል፡፡

## ሜላኒ ማርቲኔዝ

በአሜሪካ ሉዚያና ውስጥ ትኖራለች፡፡ የለየላት እድለ ቢስ ናት፡፡ ባለፉት 50 ዓመታት ውስጥ በሄሪኬን (ዝናብ በቀላቀለ አውሎ ነፋስ) ሳቢያ 5 ጊዜ መኖሪያ ቤቷ ፈርሷል፡፡ ሜላኒ ማርቲኔዝ መጀመሪያ ሰለባ የሆነችው እ.ኤ.አ በ1965 ነበር፡፡ ቤትሲ በተባለው ሄሪኬን ቤቷን አጣች፡፡ በ1985 ጆዋንና በ1998 ጆርጅ እንዲሁም በ2005 ካትሪና የተባሉ ዝናብ አዘል አውሎ ነፋሶች ቤት አልባ አደረጓት፡፡

ይህ ታሪኳ በመገናኛ ብዙሐን ከተዘገበ በኋላ ሰዎች 20 ሺ ዶላር ሠብስበው ለ4ኛ ጊዜ ቤቷ በፈረሠ ወቅት አዲስ ቤት ገነቡላት፡፡ የሚያሳዝነው ግን አዲሱ ቤቷም 2012 ላይ በተከሰተው አይዛክ የተባለ ሄሪኬን ሰበብ ፈረሠ፡፡ ይህ ሁሉ እየሆነ ግን እድለ ቢሷ ሜላኒ አካባቢውን ለቃ ለመሄድ አትፈልግም፡፡ አሁንም አዲስ ቤት ገንብታ እዚያው ሉዚያና ውስጥ ትኖራለች፡፡ ‹‹የተወለድኩት እዚህ ነው፤ የምኖረውም እዚህ ነው፡፡ ሉዚያና ቤቴ ነች›› በማለት ትናገራለች፡፡

## ኤልዛቤት ሆጅ



በሷ ላይ የሆነው በማንም ላይ ሆኖ አያውቅም፡፡ አንድ ቀን አሜሪካዊቷ አን ኤልዛቤት ሆጅ በመኖሪያ ቤቷ ሳለች ከየት እንደ መጣ ያልታወቀ ነገር ጣሪያ በስቶ ገብቶ እግሯ ላይ ወደቀ፡፡ ራሷን ሳተች፡፡ ኤልዛቤት ሆጅ ወደ ህክምና ተወስዳ ህይወቷ ቢተርፍም ሁለቱም እግሯቿ ግን ተቆርጠው ነበር፡፡

ለእግሮቿ መቆረጥ ምክንያት የሆነውና የቤቷን ጣሪያ በስቶ የገባው ነገር ከጠፈር ተምዘግዞ የመጣ አለት ነበር፡፡ ይህ ከእሷ ውጭ በማንም ላይ ደርሶ አያውቅም፡፡ በዚህም ሳቢያ እድለ ቢሷ ተብላ ትጠራለች፡፡ የሷን እግር የቆረጠው አለት በአሁኑ ወቅት አላባማ በሚገኘው የተፈጥሯዊ ታሪክ ሙዚየም ውስጥ ይገኛል፡፡



# የግጥም ገበታ

ወንዱ ልጅ ያቅራራ! ይፎክር!
ያስመስክር!
ጠላት መግቢያ ይጣ! ይሸበር
ይደንብር!
ወንዱ ደሙ ይፍላ! ይቆጣ
ይገንፍል-ሥሩ እስኪገተር
በነፃነት ፍቅር ለራሱ ባለው
ክንዱን እያነሳ አሻፈረኝ ብሎ
ጥቃትን ይጋት
ሕያው ኢትዮጵያ ትለምልም
በኅብረት!
አረሙ ይነቀል!
ይቅር ስጋት ፍርሃት

**ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም**

## ለአንዲት ቅጽበት ብቻ

እስቲ የማነው ጉልበት
የሰው የአማልክት
ሊሰጠኝ የሚችል የደቂቃ እረፍት?
ከእውነት - ፍቅር - ውበት እማወጋበት?
ለአንዲት ውብ ሙዚቃ ሀሳቤን ሰውቼ
ለአንዲት መልካም ቅኔ ባርነት ገብቼ
ህሊናዬን ፣ቀልቤን ፣አካሌን ሰጥቼ፣
ለአንዲት ቅጽበት ብቻ!
ያዕምሮ መርከብ ማእበል አምልጣ
የሕይወት ስንክሳር አምርራ ፈርጥጣ
በዕፁብ - ውበት ቅኝት እጅግ ተመስጣ
ሌላው ሌላው ነገር ባፍንጫዬ ይውጣ!

**ደበበ ሰይፉ**
**/ስራስ የተፃፈ ደብዳቤ/**

## ጌሾ ወቀጣ

ዘነዘና እንጨት
ሙቀጫም እንጨት
ጌሾ በነነ በመበሳጨት
ሲነረት ሀቁን ገና አሁን ዋጠው
የራስ ወገን ነው የሚያስወቅጠው፡፡

**ተስፋዬ ድረስ ከ/ምርገማን/**

## ለጾመኞች

ምላስን የሚያህል ቢላ
ባፉ ይዞ እየዞረ
ጾዋሚ ነኝ ይላል ሰው
ሰው ወገኛው ፍጡር
ሰው በልቶ እየኖረ፡፡
እንዳለጌታ ከበደ ከ
ይገርማል
ፉንጋ ያልኩት ፊቴ ቆንጆ እያስባለ፣
አጭሩን ቁመቴን መለሎ እያስባለ
ኮስታራ ፊቶችን ደስተኛ አድርጎ፣
የኔን ተቆርቋሪ እንደ አሽን ካፈላ
ሰው አሎድም እኔ ከገንዘቤ ሌላ፡፡

**ሰላማዊት ተስፋዬ ከ/ዝና/**

# በተስፋ የተሞላ ህይወት ለመኖር



Life hack.org በተባለ ድረገፅ ላይ ‹ተስፋ የማድረግ ህይወት› በሚል ርዕስ የቀረበ ፅሁፍ አለ፡፡ ይህ ፅሁፍ ‹በተስፋ የተሞላ ህይወት ማለት ሁሉም ነገርና ሁሉም ሠው ዋጋ እንዳለው ማወቅ ነው› ይላል፡፡ ይህም ለራሳችን ዋጋ ከመስጠት ይጀምራል፡፡ ራሳችንን መንከባከብ የምንችለውም ዋጋችንን በተረዳን ጊዜ ነው፡፡ የምንሠራው ስራም ለራሳችን ለምንሠጠው ዋጋ የራሱ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ሰዎች እኛን የሚንከባከቡበት መንገድና እኛም ሠዎችን የምንይዝበት አግባብ በህይወታችን ለሚኖረን ተስፈኝነት ከፍተኛ ዋጋ አለው - እንደ ፅሁፉ ገለፃ፡፡ እናም ለራሳችን ተገቢውን ክብር መስጠት፣ ጤናችንን በሚገባ መጠበቅ፣ የሚገጥሙንን ጫናዎች መቀነስ፣ ሠዎችን ይቅር ማለት፣ አሉታዊ ሀሣቦችን ማስወገድና ሌሎች ሠዎችን መርዳት በተስፋ የተሞላ ህይወት እንዲኖረን ይረዱናል ይላል life hack.org ድረገፅ ላይ ተስፋ የማድረግ ህይወት በሚልረ ርዕስ የቀረበ ፅሁፍ፡፡

Ehow.com በተሠኘው ድረገፅ ደግሞ እነኚህን ነገሮች ብትለማመዱ ህይወታችሁ በተስፋ የተሞላና ጤናማ ይሆናል የሚል መረጃ ሠፍሯል፡፡ እንመልከታቸው፤

1. መሠጠት (commitment)፡- ተስፋ እንዲሁ በሠዎች ልብና አዕምሮ ውስጥ በድንገት የሚበቅል አይደለም፡፡ የዕለት ተዕለት ጥረትን፣ መሠጠትን፤ ትኩረትና የተግባርና ጠንካራ የሥራ ሰው መሆን ይጠይቃል፡፡ በነኚህ ልምዶች ያለፈ ሠው የሥራውን ፍሬ መመልከት ስለሚችል ነገ የሚደርስበትንም ቦታ ከአሁኑበዓይነ ህሊናው መመልከት ይችላል፡፡ ስለዚህም በቀላሉ በሚታይ ተስፋ መኖር ይችላል፡፡

2. ተስፋ መቁረጥን ፈፅሞ አለማሠብ፡- እውነት ነው ህይወት የተመኘነውንና የጠበቅነውን ሁሉ አትሠጠንም፡፡ አንዳንድ ጊዜ እጅግ ደክመንና ሃላፊነታችንን በሚገባተወጥተን እንኳን ነገሮች አይሣኩልንም፡፡ስለዚህ በቀላሉ ተስፋ መቁረጥ የለብንም፡፡ ለነገሩ ሰው ተስፈኛየሚሆነውም በብዙ መሠናክሎች ማለፍ ሲችል ነው፡፡

3. ማስታወሻ (Diary)፡- የየዕለት ውሎ ማስታወሻ (Diary) አችን ላይ በቀን ውስጥ ያደረግናቸውን አምስት መልካም ነገሮች መፃፍ የለመድን እንደሆነም ድካምና ጥንካሬያችንን በቀላሉ መለየት እንችላለን፡፡ የሠራናቸው መልካም ነገሮችም የበለጠ ተስፈኝነት ኖሮን እንድንቀጥል ያደርጉናል፡፡

4. መንፈሳዊ መሆን፡- የብዙ ሀይማኖቶች መሠረታዊ ጥያቄ ‹‹ለምን ተፈጠርኩ? በምድር ላይ የመኖሬ ዓላማስ ምንድን ነው?›› የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነው፡፡ ይህንን ጥያቄ ለራሳችን ስናቀርብ ለአንድ ታላቅ ዋጋ ላለው ምክንያት እንደተፈጠርን ይገባናል፡፡በዚህም ምክንያት ሣይሆን አይቀርም አብዛኛውን ጊዜ መንፈሣዊ ሠዎች በነገሮች ሁሉ ጠንካራ ሆነውና ተስፋ ኖሯቸው የሚታዩት ፡፡

5. ተስፋ ከሚያደርጉ ሠዎች ጋር መሠባሠብ፡- አስተሣሠቦችይጋባሉ፡፡ ‹ተመሳሳይ ክንፍ ያላቸው ወፎች አንድ ላይ ይበርራሉ› ይባላል፡፡ ተስፋ ከሚያደርጉ ሠዎች ጋር አብዝቶ መገናኘትም እኛም በተስፋ የተሞላን እንድንሆን ይረዳናል፡፡

## ከሰሞኑ




### ‹‹ወደ ሀገር ቤት›› የተሠኘው ፊልም ተመረቀ

**ማን፡-** በአቤል ፊልም ፕሮዳክሽን
**ምን፡-** ወደ ሀገር ቤት ፊልም
**የት፡-** ሀርመኒ ቴል
**መቼ፡-** ህዳር 13 ቀን 2007 ዓ.ም

በደራሲና ዳይሬክተር ሱራፌል ኪዳኔ ተሠርቶ በአቤል ፊልም ፕሮዳክሽን የቀረበው ወደ ሀገር ቤት የተሠኘ ፊልም ህዳር 13 ቀን 2007 ዓ.ም በሀርመኒ ሆቴል ተመርቋል፡፡

ፊልሙ የፍቅር ኮሜዲ ይዘት ያለው ሲሆን በስደት ወደ ውጭ ሀገር ሄዶ ለችግር ከመጋለጥ በሀገር ሠርቶ መለወጥ እንደሚቻል የሚያስገነዝብ ሲሆን ፍቅርና ጓደኝነት ያላቸውን ኃያልነትም ያሣያል፡፡ ካሣሁን ፍስሀ (ማንዴላ)፣ እንግዳሰው ሀብቴ/ቴዲ/፣ ማርታ አሠፋ፣ መኮንን ላዕከ እና አስቴር አለማየሁ ከፊልሙ ተዋንያን መካከል የተወሠኑት ናቸው፡፡ በፕሮዲውሠርና ኤዲተር አቤል አለማየሁ በተዘጋጀው በዚህ የፊልም ምርቃት ላይ በክብር እንግድነት ዶ/ር ኤልያስ አህመድ እና አርቲስት ዝናብዘሀ ፀጋዬ ለተዋንያኑ የምስክር ወረቀት ሠጥተዋል፡፡

**ጌርጌሴኖን የአዕምሮ ሕሙማን መርጃ ማህበር**

ለደሃ ቸርነት የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል
በጎነቱንም መልሶ ይከፍለዋል፡፡ ምሳሌ 19፡17
መልካም ማድረግን ለሌሎች ማካፈልን አትርሱ
ማህበሩ የጀመረውን መልካም ራዕይ የሚያከናውንበትን
ቦታ ከመንግስት ወይም ከለጋሽ ግለሰቦች ጠይቆ ማግኘት፡፡

ማህበሩ አድራሻ
ቁስቋም 17 ቁጥር ባስ ማዞሪያ ከፍ ብሎ ውሃ ክፍሉ ጎን
0118 70 39 27 አቶ መስስ አየለ 0912-18-88-76
0922-82-12-35 ፓስታ 31209 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Email:gergesenon@gmil.com

# አፍቅሮተ ‹‹ታላቅ›› ነት

አዲስ አበባ ውስጥ ከሚተላለፉ የኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያዎች በአንዱ የሠማሁት ነገር አስደንቆኛል፡ ፡ ጋዜጠኛው ስቱዲዮ የጋበዘውን አንድ ድምፃዊ ሲያስተዋውቅ «ታላቁ እንግዳችን» በማለት ተናገረ፡፡ ይህ ጋዜጠኛ ከዚህ ቀደም ከአሁኑ ድምፃዊ በልምድም ሆነ በችሎታ የሚበልጡ ድምፃውያንን እንግዳ ማድረጉን ስለማውቅ ይህ ድምፃዊ ከሌሎቹ ተለይቶ «ታላቅ እንግዳ» የሆነበት ምክንያት አልገባኝም፡፡ ለነገሩ በዚህች ታላቅነቷ ታሪክ ሆኖ በቀረ ሀገር ዛሬ ማንም እየተነሣ ሁሉንም ነገር «ታላቅ» ለማድረግ ሲሞክር እየተመለከትን አይደል?

ሐይማኖታዊ ማስታወቂያዎችን የምትመለከቱ ከሆነ «ታላቅ መንፈሳዊ ጉባዔ» እና «ታላቅ የወንጌል ኮንፈረንስ» የሚሉ መልዕክቶች በየቦታው ተለጥፈው ታያላችሁ፡፡ ወደ ጥበቡ ጎራም ስትዘልቁ ይሄ ነው የሚባል የሙዚቃ ታሪክ የሌላቸው ድምፃውያንን ሠብስበው «ታላቅ የሙዚቃ ኮንሠርት» የሚል ማስታወቂያ የሚያስነግሩ ነጋዴዎችን መልእክት ትመለከታላችሁ፡፡ «ታላቅ የመፅሓፍት አውደ ርዕይ» የሚሉ ማስታወቂያዎችን ሠምታችሁስ አታውቁም? «ታላቅ ቴአትር» የሚል የቴአትር ተመልካቹ ጥሪም አድምጠናል፡፡

ወደ ንግዱ ጎራ ስትሄዱ ደግሞ በየሱቁ ተለጥፈው የሚጠብቋችሁ «ታላቅ የዋጋ ቅናሽ» የሚሉ መልዕክቶች አሉ፡፡ የዋጋ ቅናሹ «ታላቅ» የተባለው ነጋዴው ለደንበኞቹ ምን ያህል ገንዘብ ቀንሶ ይሆን የሚል ጥያቄ ስታነሡ ግን ነገሩ ‹ውስጡ ገለባ› ይሆንባችኋል፡፡ ከመሸጫ ዋጋው ላይ ሃያ ብርም የቀነሰ፤ ሰማንያ ብርም የቀነሠ ነጋዴ፤ እኩል «ታላቅ ቅናሽ» የሚል ማስታወቂያ ሲያስነግሩ «ለምን?» ብሎ የሚጠይቃቸው የለም፡፡

በቅርቡ ደግሞ ወደ አዳማ ከተማ ሄጄ በአንድ የባንክ ቅርንጫፍ ላይ «ታላቋ አዳማ ቅርንጫፍ» የሚል ፅሁፍ መመልከቴ አስገርሞኛል፡፡ አዳማ ታላቅ የሆነችው ከየትኞቹ ከተሞች ጋር በምን መስፈርት ተወዳድራ ይሆን? ለመሆኑ እንደ ታላቋ አዳማ ሁሉ ታናሽ የምንላት አዳማ ትኖር ይሆን? መቼም ታላቅ ካለ የታናሽ መኖር ግድ ነው፡፡

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትራችን አቶ መለስ ዜናዊም ህልፈታቸውን ተከትሎ «ታላቅ» የሚል ክብር ተሠጥቷቸው «ታላቁ መሪ» ተብለዋል፡፡ ሠውየው «ታላቅ» የተባሉት ከእነማን ጋር ተወዳድረው ነው? መቼም ማስረጃ ጠቅላይ ሚንስትርን ከሚኒስትሮች ጋር አወዳድሮ ታላቅ ማለት ተገቢ አይመስለም፡ ፡ ነገርየው የራሱ መስፈርት ከሌለው እኔም የቀድሞውን ፕሬዚዳንት መንግሥቱ ኃይለማርም «ታላቁ መሪ» ብዬ ብጠራቸው ተሣሣትክ የሚለኝ ማነው? አዎና! ቢያንስ በእድሜ እንኳን የአቶ መለስ ታላቅ ናቸው፡፡



## ከኢቦላ ነፃ ስለሆነችው ሀገር

ሰሞኑን የአፍሪካ ሀገራትን እያስጨነቀ ስላለው የኢቦላ በሽታ ሀገራት ዜጎቻቸውን ከዚህ ቀሳፊ በሽታ ለመከላከል ላይ ታች እያሉ ነው፡፡ አንዳንድ ሀገራት የኢቦላ በሽታ ተጠቂ ወደ ሆኑ የምዕራብ አፍሪካ ሀገራት የአየር በረራ ላለማድረግ ሲወስኑ የበረራ መጠናቸውን በግማሽ የቀነሱም አሉ፡፡ ሀገራችም ምንም እንኳ የበሽታው ስጋት ያለባት ብትሆንም የአየር በረራዋንም ሆ ዜጎቿን ወደ ምዕራብ አፍሪካ ከመላክ አልተቆጠበችም፡፡

እንደውም ሰሞኑን 201 የጤና ባለሙያዎች ወደ ላይቤሪያ፤ ሴራሊንዮንና ጊኒ ‹ካሄድን › በማለታቸው ወደ እዛው የሚሳፈሩበትን ትኬት መንግስት ቆርጦ እንደሰጣቸው ሰሞኑን በየዜና ማሰራጫው ተዘግቧል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን በአፍሪካ የኢቦላ በሽታ የማያሰጋት ሀገር ስለመኖሯ አንድ ጓደኛዬ ስልክ ደውሎ ይፋ አድርጎልኛል፡፡ ለመሆኑ በአፍሪካ ውስጥ እያለች ነገር ግን የኢቦላ በሽታ የማያሰጋት ሀገር የትኛዋ እንደሆነች በመፈለግ ላይ እያለሁ ባለበት ጊዜ ጓደኛዬ ደውሎ ሀገሪቱን አወቅሃት ወይ? አለኝ፡፡ እንዳላወኳት ስነግረው ‹ሰሞኑን በ37 ቀናት ብቻ ከስድስት ሺህ በላይ ስደተኞቿ ወደ ኢትዮጵያ ያስገባች ሀገር ስለመኖሯ በዜና አልሰማህም እንዴ?› አለኝ፡፡ እንዳልሰማሁ ስገልፅለት ምን ቢለኝ ጥሩ ነው? ‹ኤርትራ ናት› አለኝ፡፡ እንዴት? ስለው ‹ሰየህ ከኤርትራ የሚወጣ እንጂ ወደ ኤርትራ የሚገባ ሰው ስለሌለ በሽታው አያሰጋትም› አለኝ፡፡

## ከፌስቡክ ማህደር



" ከጋብቻ በፊት "
ወንዱ :- ይሄንን ቀን በጉጉት ስጠብቅ ነበር
ሴቷ :- ትቼህ እንድሄድ ትፈቅድልኛለህ ?
ወንዱ :- በፍፁም
ሴቷ :- ትወደኛለህ ?
ወንዱ :- አዎን
ሴቷ :- በላዬ ላይ ከሌላ ሴት ጋር ታመነዝራለህ ?
ወንዱ :- በፍፁም አላደረገውም
ሴቷ :- ትስመኛለህ ?
ወንዱ :- ባገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ
ሴቷ :- ትመታኛለህ ?
ወንዱ :- ምን በወጣኝ
ሴቷ :- ልመንህ ?
ወንዱ :- Yes
ሴቷ :- የኔ ፍቅር
" ከጋብቻ በኋላ ከታች ወደ ላይ አንብቡት "

በፍስሃ ጌትነት


# ጋሬት ቤል

## ‹‹ልጅ እያለሁ ሳድግ ሄሊኮፍተር የምሆን ይመስለኝ ነበር››




እስካሁን በዓለም እግር ኳስ ታሪክ የሱን ያህል ከፍተኛ ገንዘብ ወጥቶበት ከአንድ ክለብ ወደ ሌላ ክለብ የተዘዋወረ የለም፡፡ የ25 ዓመቱ ዌልሳዊ የክንፍ ተጫዋች ጋሬት ቤል ቶተንሃምን ለቆ ሪያል ማድሪድን የተቀላቀለበት የዝውውር ዋጋ 85 ሚሊዮን ፓውንድ ነበር፡፡ እ.ኤ.አ በ2013 ክረምት ላይ ሳንቲያጎ በርናባው የደረሠው ቤል በመጀመሪያው ዓመት  ከአዲሱ ክለቡ ጋር የቻምፒዮንስ ሊግና የንጉሱ ዋንጫን ማንሳት ችሏል፡፡ ሪያል ማድሪድ በውድድር ዓመቱ ላስመዘገበው ውጤት የተጫዋቹ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነበር፡፡ በተለይ በቻምፒዮንስ ሊግ ፍጻሜ አትሌቲኮ ማድሪድን 3ለ1 በረቱበት ጨዋታ ያስቆጠራት ጎል ሪያል ማድሪዶች ለ10ኛ ጊዜ አህጉራዊውን ዋንጫ ያነሱ ዘንድ በር ከፍታለች፡፡

ጋሬት ቤል ጎል ያስቆጠረው ጨዋታው በአትሌቲኮ ማድሪክ 1ለ0 አሸናፊነት ሊጠናቀቅ የሰከንዶች ሽርፍራፊ በቀሩበት ወቅት ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ የስፖርት መገናኛ ብዙሐን ሪያል ማድሪድን ለቆ ማንቼስተር




ዩናይትድን አልያም ቼልሲን በመጪው ክረምት በከፍተኛ የዝውውር ዋጋ ሊቀላቀል እንደሚችል የሚጠቁሙ ዘገባዎች እያወጡ ይገኛሉ፡፡ ዜናው እውን ከሆነ ጋሬት ቤል ዳግም የዓለም የተጫዋቾች ዝውውር ዋጋ ሪከርድን ይሰብራል፡፡

## ልጅነት

ሙሉ ስሙ ጋሬት ፍራንክ ቤል ይባላል፡፡ የተወለደው እ.ኤ.አ ሐምሌ 16 ቀን 1989 በዌልሷ ካሪድፍ ከተማ ነበር፡፡ የማንቼስተር ዩናይትድ ተጫዋች የነበረውን ሪያን ጊግስን እያደነቀ ያደገው ጋሬት ቤል በልጅነቱ በበርካታ የስፖርት አይነቶች ይሳተፍ ነበር፡፡ እግር ኳስ የመጀመሪያ ምርጫው ቢሆንም አትሌቲክስ፣ ራግቢና ሆኪ ከሚያዘወትራቸው ሌሎች ስፖርቶች መካከል ይገኙበታል፡፡ የ14 ዓመት ታዳጊ ሆኖ 100 ሜትር ሩጫን በ11.4 ሰከንድ መጨረስ ችሎ ነበር፡፡

‹‹በልጅነቴ ሳድግ ሄሊኮፍተር የምሆን ይመስለኝ ነበር›› የሚለው ጋሬት ቤል ከመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት አንስቶ በተለይ በስፖርት መምህራኖቹ

ይደረግለት የነበረው እገዛና ክትትል ዛሬ ለደረሠበት ደረጃ መሠረት እንደሆነ ይናገራል፡፡ በተለይ ሞሪስ የተባለ አስተማሪው በቤል የእግር ኳስ ህይወት ውስጥ መሠረት የጣለ ሰው ነው፡፡ ችሎታውን ማሳደግ የሚችልበትን መንገድ ከማሳየት በተጨማሪ ክትትልና ድጋፍ ያደርግለት ነበር፡፡

ሁለቱንም እግሮቹን የመጠቀምና ለቡድን አጋሮቹ ቶሎ ኳስ የማቀበል ብሎም ጨዋታን የማንበብ ክህሎቱ እንዲያድግ አስተማሪው በየጊዜው ይረዳው ነበር፡፡

«ጋሬት ቤል ያሰበውን ለማሳካትና ከግብ ለማድረስ ጥረት የሚያደርግ ታታሪ ልጅ ነበር፡፡ ካስተማርኳቸው ልጆች ሁሉ በጣም የምደሰትበትና ራስ ወዳድ ያልሆነ ሠው ነው» በማለት አስተማሪው ሞሪስ ባንድ ወቅት ስለተጫዋቹ ስብዕና አስተያየቱን ሰጥቶ ነበር፡፡

## ሳውዛምፕተን

የእንግሊዙ ክለብ ሳውዛምፕተን የጋሬት ቤል ምንጭ ነው፡፡ ወጣት የእግር ኳስ ከዋክብትን እያፈራ የሚገኘው ሳውዛምፕተን እንግሊዝ ውስጥና ከእንግሊዝ ውጭ የእግር ኳስ አካዳሚዎች አሉት፡፡ ጋሬት ቤል የሳውዛምፕተን አካዳሚን የተቀላቀለው ገና በ9 ዓመቱ ነበር፡፡ በ16 ዓመቱ ደግሞ ለክለቡ የመጀመሪያ ጨዋታውን አደረገ፡፡ በትንሽ እድሜው ክለቡን ወክሎ በመጫወት ከቴው ዋልኮት በመቀጠል ሁለተኛው ተጫዋች ነው፡፡ አሁን ለአርሰናል የሚጫወት ዋልኮት ከሳውዝሃምፕተን አካዳሚ የተገኘ ሲሆን ለቀድሞ ክለቡ የመጀመሪያ ጨዋታውን ያደረገው 16 ዓመት ከ132 ቀን ሆኖ ነበር፡፡ ከጋሬት ቤል በ43 ቀናት ያንሳል፡፡

ዌልሳዊው የክንፍ ተጫዋች የአደገበትን ክለብ ያገለገለው ግን ለአንድ ዓመት ብቻ ነበር፡፡ በዚያ ቆይታው 45 ጊዜ ተሰልፎ የተጫወተ ሲሆን 5 ጎሎችንም አስቆጥሯል፡፡ ከነዚህ መካል 3ቱ የቅጣት ምት ጎሎች ናቸው፡፡ በዚህም ሳቢያ በሳውዛምፕተን ክለብ ውስጥ ጋሬት ቤል የቅጣት ምት ስፔሻሊስት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

## ቶተንሃም

ጋሬት ቤል በሳውዛምፕተን እያለ ያሳየው ድንቅ እንቅስቃሴ ገና በ16 ዓመቱ በተለያዩ ክለቦች እይታ ውስጥ እንዲገባ አድርጎት ነበር፡፡ በተለይ የሰሜን ለንደኑ ክለብ ቶተንሃም የተጫዋቹን ፊርማ ለማግኘት ተደጋጋሚ ጥያቄዎችን ያቀርብ ነበር፡፡ በዚህም መሠረት ቤል በ7 ሚሊዮን ፓውንድ የዝውውር ዋጋ እ.ኤ.አ 2007 ላይ ቶተንሃምን ተቀላቀለ፡፡ ለለንደኑ ክለብ የመጀመሪያ ጎሉን ያስቆጥረው ለሁለተኛ ጊዜ በተሰለፈበትና ቶተንሃም ከፉልሃም ጋር 3ለ3 በተለያየበት ጨዋታ ነበር፡፡ በወቅቱ ያስቆጠራት ድንቅ ጎል ደጋፊዎቹን ያስፈነጠዘች ነበረች፡፡ ይሁንና ቶተንሃም ከ2007-2009 ድረስ ጥሩ የሚባል ውጤት ማስመዝገብ ተስኖት ነበር፡፡ እነዚያ ዓመታት ለዌልሳዊው ጋሬት ቤልም ጭምር እንደመጥፎ ጊዜያት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ጉልበቱ ላይ ባጋጠመው ጉዳት ሳቢያ ለረዥም ጊዜ ከሜዳ ርቆ ነበር፡፡

ከጉዳት ከተመለሰ በኋላም ቢሆን በተለይ ካሜሮናዊው አሶአ ኢኮቶ በድንቅ አቋም ላይ ስለነበር አሰልጣኝ ሃሪ ሬድናፕ ተጠባባቂ ወንበር እንዲያሞቅ ፈርደውበት ነበር፡፡ በቋሚ ተሰላፊነት ወደ ሜዳ




ለመግባት የኢኮቶን መጎዳት ለመጠበቅ ተገደደ፡፡ ጋሬት ቤል የመጀመሪያ ተመራጭ ከሆነ በኋላ ቶተንሃም ተደጋጋሚ ውጤት አስመዘገበ፡፡ የለንደን ተቀናቃኞቹን ማለትም ፉልሃም፣ አርሰናልና ቼልሲን በተከታታይ በኤፍ ኤ ካፕና በፕሪምየር ሊጉ ሲያሸንፍ ቤል ጎሎችን በማስቆጠር ጭምር ወሳኝነቱን አሳየ፡፡ በዚህም መሠረት ክለቡ ጋሬት ቤልን አዲስ የአራት ዓመታት ኮንትራት አስፈረመው፡፡ ይህ የፊርማ ውል ክለቡ በቻምፒዮንስ ሊግ የሚያስትፈውን ውጤት እንዲያገኝ ላስቻለበት ውለታ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

በቶተንሃም ክለብ ውስጥ የጋሬት ቤል ወርቃማ ጊዜ የሚባለው እ.ኤ.አ 2012/13 የውድድር አመት ነው፡፡ በዚያ የውድድር ዓመት የእንግሊዝ ፕሪምየርሊግ የአመቱ ምርጥ ተጫዋችና ምርጥ ወጣት ተጫዋች እንዲሁም የዓመቱ የእግር ኳስ ፀሀፊዎች ሽልማትን ወስዷል፡፡ ከክርስቲያኖ ሮናልዶ በኋላ ሶስቱን ሽልማቶች በአንድ አመት ማግኘት የቻለ ሁለተኛው ተጫዋች ሆኗል፡፡

## ሪያል ማድሪድ

ቤል ሪያል ማድሪድን ሲቀላቀል መጀመሪያ ላይ የዝውውር ዋጋው ሚስጥር የተደረገ ቢሆንም በኋላ ግን የእንግሊዝ መገናኛ ብዙሃን ይፋ አደረጉት፡፡ ዌልሳዊው የአለም የእግር ኳስ ተጫዋቾችን የዝውውር ዋጋ ሰበረ፡፡ ማድሪድ ክርስቲያኖ ሮናልዶን ከማንቼስተር ዩናይትድ ያስኮበለለበት ዋጋ 80 ሚልዮን ፓውንድ ነበር፡፡ የጋሬት ቤል የዝውውር ዋጋ በ5 ሚሊዮን ፓውንድ ከፍ ያለ በመሆኑ የወቅቱ ሪከርድ በሱ ስም ተመዝግቧል፡፡

ቤል ሪያል ማድሪድን ከተቀላቀለ በኋላ የመጀመሪያዎቹን ወራት በጉዳት አሳልፏል፡፡ ወደ ሜዳ ከተመለሰ በኋላም ቢሆን በሚጠበቅበት ደረጃ ቡድኑን እያገለገለ አይደለም በሚል ትችቶችን ሲያስተናግድ ነበር፡፡

ድንቅ ብቃቱን በማሳየት የትችት አፎችን ማዘጋት የጀመረው ሪያል ማድሪድ ሲቪያን 7 ለ 3 ባሸነፈበት ጨዋታ ላይ ለጎል የሚሆኑ 2 ኳሶችን አመቻችቶ ካቀበለ በኋላ ነው፡፡ ሪያል ማድሪድ ሪያል ቫሌካኖን 4ለ0 ባሸነፈበት ጨዋታ ደግሞ ለክለቡ የመጀመሪያ ሃትሪኩን ሠራ፡፡

ቤል በንጉሡ ዋንጫና በቻምፒዮንስ ሊግ የፍጻሜ ጨዋታ ላይ ወሳኝ ጎሎችን በማስቆጠር ክለቡን ውጤታማ አድርጓል፡፡ ባጠቃላይ በመጀመሪያ አመት የሪያል ማድሪድ ቆይታው 22 ኳሶችን መረብ ላይ ሲያሳርፍ 16 የሚሆኑትን ደግሞ ለጎል አመቻችቶ ሰጥቷል፡፡

## የአጨዋወት ስታይል

ጋሬት ቤል እግር ኳስን ሲጀምር የግራ ተከላካይ ነበር፡፡ የክንፍ ተጫዋች ያደረጉት የቶተንሃም አሰልጣኝ የነበሩት ሃሪ ሬድናፕ ናቸው፡፡ በፈጣን እንቅስቃሴው የሚታወቀው ጋሬት ቤል ለተቃራኒ ተጫዋቾች አስቸጋሪ ከሚባሉ የአለማችን ምርጥ የግራ ክንፍ ተጫዋቾች አንደኛው ነው፡፡ የሱን እንቅስቃሴ ለማስቆም ከሁለት በላይ ተጫዋቾች የግድ ያስፈልጋሉ፡፡ ጋሬት ቤል እጅግ በጣም ፈጣን ተጫዋች ከመሆኑም በተጨማሪ ለቡድን አጋሮቹ በሚያቀብላቸው የተስተካከሉ ኳሶች፣ በምርጥ እግር ተጫዋችነቱና በአካላዊ ብቃቱ ይደነቃል፡፡ የኳስ ቁጥጥሩና ከቅጣት ምት የሚያስቆጥራቸው ጎሎቹ እንዲሁም ከፍፁም ቅጣት ምት ክልል ውጭ ወደግብ አክርሮ በመምታት የሚሞክራቸው ኳሶች የእሱ አጨዋወት መገለጫዎች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

## የግል ህይወት

ቤል ማድሪድ ከተማ ውስጥ ከፍቅረኛው ኤማ ሪስ ጆንስ ጋር ይኖራል፡፡ ሁለቱ የፍቅር አጋሮች የሚተዋወቁት ገና በተማሪነት ዘመናቸው ሲሆን ያኔ ቤል የ13 ዓመት ታዳጊ ነበር፡፡ አይናፋር የሆነችው ኤማ ራሷን ከመገናኛ ብዙሐን ደብቃ አመታትን ቆይታለች፡፡ ስለዚች ሴት መወራት የጀመረው ጋሬት ቤል ሪያል ማድሪን ከተቀላቀለ በኋላ ነበር፡፡

ጥንዶቹ አልባ የተባለች ሴት ልጅ አለቻቸው፡፡፡ ቤል ፊርማውን ለሪያል ማድሪድ ባኖረበት ወቅት በስፍራው ፍቅረኛውና ልጁ ተገኝተው ነበር፡፡

# ሃናና ሃበሻ ፐራንክ ...

ከገጽ 6 የዞረ

ወደ ደንበል የሚወስደውን መንገድ በፍጥነት ነድታ አዲስ እየተሰራ ያለው አደባባይ ጋር ስትደርስ በአይሬ ግራና ቀኝ ፖሊሶችን ፍሊጋ አማተረች፡፡

በወቅቱ በአካባቢው ላይ የትራፊክ ፖሊሶችና ሌሎች የፌደራል ፖሊስ የፀጥታ ሠራተኞች ነበሩ፡፡ ሚስት አደባባዩን እንደተሻገረች ላፓራዚያን ካፌ ፊት ለፊት ከመድረሷ በፊት ከኋላ የሚከተላት የባሏ መኪና ሲጋልብ አጠገቧ ይደርሳል፡፡ አመጣጡ ያላማራት ሚስት መኪናዋን ካርቱም ሬስቶራንት ፊት ለፊት ባለበት ሁኔታ አቁማ በመውረድ ወደ ፀጥታ ሠራተኞች ለመሮጥ በመወሰን መኪናዋን ታቆማለች፡፡

የአደጋ መከላከያ ቀበቶዋን በፍጥነት ፈትታ ልትወርድ ስትል ግን መኪናው በበሯ አጠገብ ሲጢጥ ብሎ በማቆም አሽከርካሪው ወደ እሷ መጣ፡፡ በሯ በመኪናው መዘጋቱን የተመለከተችው ሚስት በሌላኛው የፊት በር በፍጥነት ወጥታ ለማምለጥ ጥረት እያደረገች ሳለ ረዥም ክላሺንኮቭ ጠመንጃውን እያቀባበለ ወደ እሷ የተጠጋው አሽከርካሪ በቀጥታ በመተኮስ በ18 ጥይት የሁለት ልጆቹን እናት ባለችበት ጣላት፡፡ ከተኮሳቸው ጥይቶች መሀከል ወላጅ እናቷን ሶስት ጥይት አግኝቷቸዋል፡፡ ሁኔታውን በስፍራው ሆነው ሲከታተሉ የነበሩ የአይን እማኞች እንደገለፁት ከሆነ ያለምንም ንግግር ይህንን አስከፊ ድርጊት የፈፀመው ሰው በቀረው ጥይት ራሱን ለማጥፋት ወደርሱ ለመተኮስ ቢሞክርም ጠመንጃው ጥይቱን ጨርሶ ስለነበር መሞት አልቻለም፡፡ ይህ ከሁለት እስከ ሶስት ደቂቃ የፈጀውን ትዕይንት ለማስቆም ጊዜ ያጡት በአካባቢው የነበሩት የፀጥታ ሠራተኞች የድርጊቱን ፈፃሚ ዋና ተዋናይ በቁጥጥር ስር አድርገው ተጎጂዎቹን ወደ ሆስፒታል ለመውሰድ ወዲያ ወዲህ ቢሉም ሚስት ወ/ሮ ፍሬህይወት ታደሠ ሰውነቷ ላይ ባረፉት 18 ጥይቶች ሳቢያ እስከወዲያኛው ያሸለበችው እዚያው መኪና ውስጥ ነበር(ቁም ነገር መፅሔት 6ኛ ዓመት ቁጥር 62፤ መጋቢት 1999ዓ.ም)፡፡ ፍሬህይውት ታደሰ ባለትዳርና የሁለት ልጆች እናት ነበረች፡፡ ከባለለቤቷ ወንድወሰን ይልማ ጋር የተዋወቀችው ቦሌ ብራስ ሆስፒታል አካባቢ ባለ አንድ መ/ቤት ሊፍት ውስጥ በአጋጣሚ ሲሆን ብዙም ሳይቆዩ በከተማችን ለየት ባለ ባህላዊ ጋብቻ ነበር የተጋቡት፡፡ ወንድወሰን የሁለት ልጆቹን እናት በዚህ ሁኔታ ከገደለ በኋላ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውሏል፡፡ለሰሚ ግራ የሆነው ይህ ጭካኔ የተሞላበት ዜና እንደተሰማ አሁንም በመገናኛ ብዙሃኑ ላይ እንደወጣ ተመሳሳይ ድምጾች ወጡ፡፡ ‹ሊሰቀል ይገባል! › ተባለ፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት ከአንድ ዓመት ከሶስት ወራት በኋላ የዕድሜ ልክ እስራት ፈርዶበት ወደ ማረሚያ ቤት ተላከ፡፡

*******

## የቤተል ታሪክ

የ25 ዓመቷ ቤተል ሀዲስ ሀምሌ 3 ቀን 2003 ዓ.ም ከዲላ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን የመጀመሪያ ዲግሪዋን የተቀበለች ወጣት ናት፡፡ ከልጅነቷ ጀምሮ ለትምህርቷ ያላትን ፍቅርና ትጋት የሚያውቁት ቤተሰቦቿ ዲግሪዋን ይዛ ወደ ምትኖርበት ወደ ምዕራብ ወለጋ መንዲዳ ስትመጣ በደስታ ነበር የተቀበሏት፡፡ በአካባቢው ልጃገረዶች እንደ አርአያ መታየት የጀመረችው ቤተል በተማረችው ትምህርት ራሷን ለመቻልና ሀገሯን ለማገልገል ወደ ሥራ ፍሊጋ የተሰማራችው በማግስቱ ነበር፤ አዲስ አበባ መጥታ ሥራ ለማግኘት ቁርጥ ሀሳብ ላይ የደረሰችው ቤተል አዲስ ዓመትን ከቤተሰቦቿ ጋር አሳልፋ ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ጀመረች፡፡

መስከረም 4 ቀን 2004 ዓ.ም ማለዳ ወደ አዲስ አበባ ታላቅ እህቷ ለምለም ሀዲስ ጋር ለመሄድ በማሰብ በዋዜማው ልብሶቿን ስታጣጥብ በትዳር አብረን ካልኖርን እያለ የሚያስቸግራት ግለሰብ ቤቷ ድረስ በመምጣት «ወደ አዲስ አበባ መሄድ ብሎ ነገር የለም» በማለት ዝቶባት ይሄዳል፡፡ ማታ በጠዋት ለመነሳት በጊዜ ወደ አልጋዋ ላይ የወጣችው ቤተል ከምሽቱ 3 ሰዓት ተኩል ገደማ ከእንቅልፏ የሚቀሰቅሳት ሰው መምጣቱና በር ላይ መቆሙ ይነገራታል፡፡ አይናን እያሻሸች ወደ ደጅ ብቅ ያለችው ቤተል የጋብቻ ጥያቄውን በሀይል እንድትቀበል የሚጎተጉታት ሰው መሆኑን ብትረዳም ከደቂቃዎች በኋላ በእጁ የያዘውን ጀሪካን ሙሉ ሰልፈሪክ አሲድ መላ ሰውነቷ ላይ ይደፋብኛል ብላ አላሰበችም፡፡

******

## የትእግስት ታሪክ

የ3 ልጆች እናት የሆነችው ወ/ሮ ትእግስት መኮንን ከባለቤቷ ከአቶ ምናለ አቻሞ ጋር እንደ ማንኛውም ባልና ሚስት ተደጋጋሚ የቤት ውስጥ ፀብ ነበረባቸው፡፡ ሚያዝያ 30 ቀን 2003 ዓ.ም ግን ቤሰቦቿን ለመጠየቅ ወደ ቤታቸው ካመራችበት በስልክ ወደ ቤቷ እንድትመለስ ትጠራለች፡፡ አባት ሁሌም ቤት ውስጥ ሲመጣ ልጆቹን የማስቸገር ልማድ እንዳለው የምታውቀው ወ/ሮ ትእግስት ባሏ ወደ ቤት መምጣቱን ስትሰማ ልጆቿን እንዳይረብሽባት በሚል ወደ ቤቷ ትመለሳለች፡፡ ወትሮም የተለመደ የባልና ሚስት ፀብ ይኖራል ብላ የገመተችው ወ/ሮ ትእግስት ቤቷ ስትገባ የጠበቃት የባሏ ዱላ ነበር፡፡ ትእግስት ራሷን የመከላከል አቅሟን ካዳከመና ምንም ማድረግ እንደማትችል ካረጋገጠ በኋላ መላ ሰውነቷ ላይ አሲድ ደፍቶ ይሰወራል፡፡ በጉዳቱ መላ ሰውነቷ የተቃጠለባት ወ/ሮ ትዕግስት ለህክምና ወደ የካቲት 12 ሆስፒታል ብትወሰድም ጉዳቱ ከባድ ስለነበር ከቀናት የሕክምና እርዳታ በኋላ ሰኔ 1 ቀን 2003 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች፡፡

******

## የጊዜሽ ወርቅ ታሪክ

ወ/ሮ ጊዜሽወርቅ ዓለሙ ከአቶ ጌቱ ቶሎሳ ጋር ወዳጅ ዘመድ በተገኘበት ተጋብተው ሲኖሩ ስድስት ልጆችን ወልደዋል፡፡ ግልፍተኛ ስሜት የሚታይበት አቶ ጌቱ ሁለተኛ ልጃቸውን ከእኔ እንዳልወለድሽው «በራዕይ ታይቶኛል በሚል ከባለቤቱ ጋር ነጋ ጠባ ጠብ ውስጥ ይገባል፡፡ የምታደርገው ነገር የጠፋት ወ/ሮ ጊዜሽወርቅ የዘር ማንነት ምርመራ (DNA) ልጃቸው እንዲመረመር ተደርጎ ልጃቸው እንደሆነ በህክምና ባለሙያ ይረጋገጣል፡፡

ነገር ግን ታይቶኛል ያለው ራዕይ ከቀድሞው እውነታ በቀር ሌላ ነገር እንዳይቀበል አድርጎታልና ፈፅሞ DNA





ምርመራውን መቀበል አልቻለም፡፡ ሰኔ 2 ቀን 2003 ዓ.ም አድብቶ ከሥራ ወደ ቤት ይመለሳል፡፡ የቤት ሰራተኛቸውን ወደ ሱቅ እቃ ገዝታ እንድትመጣ ከላካት በኋላ የ6 ልጆች አባት ያደረገችውን ሚስቱን በጥይት ደብድቦ በመግደል እጁን ለፖሊስ ይሰጣል፡፡ ፖሊስም ምርመራውን አጠናቆ ለአቃቤ ህግ አቅርቦ መዝገቡ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤት የ13 ዓመት ፅኑ እስራት ፈረደበት፡፡

*****

## የእመቤት ታሪክ

አቶ ከበደ ተሰማና ወ/ሮ እመቤት ጌታቸው ከሚያዚያ 1999 ዓ.ም ጀምሮ በትዳር ሲኖሩ እንደ ማንኛውም ባልና ሚስት ጊዜያዊ ግጭት በመሀከላቸው መፈጠሩ አልቀረም፡፡ መጋቢት 12 ቀን 2003 ዓ.ም በመሀከላቸው የተፈጠረው አለመግባባት ግን ከሀይለ ቃል አልፎ ወደ ላዱላ አመራ፡፡ ባል አቶ ከበደ ለዓመታት አብረው የኖረች ባለቤቱን ጭንቅላቷን በዱላ ደጋግሞ በመምታት የቀን ጎዶሎ እንዲሉ ፓራላይዝድ እንድትሆን አድርጓታል፡፡ አቶ ከበደ በሚስቱ ላይ ባደረሰው ከባድ የአካል ጉዳትን የተመለከተው ፍ/ቤት በአቶ ከበደ ላይ የወሰነው የ4 ዓመት ከ6 ወር እስራት ብቻ ነው፡፡

*****

## የሳራ ታሪክ

የሐረር ከተማ ነዋሪ ሣራ መሀመድ በንግድ ሥራ የምትተዳደር የ24 ዓመት ወጣት ናት፡፡ ሣራ ከተጠርጣሪ ባለቤቷ አቶ አብዱልናስር ዑመር ጋር ቀለበት አስራ በአንድ ጎጆ ውስጥ በጋራ መኖር ከመጀመራቸው በፊት ተጠርጣሪ ሌላ ሚስት ነበረችው፡፡ ከዚህችው ማለቱም 3 ልጆች የወለደ ሲሆን ሳራ ጋር ሆኖ ተቆራጭ ያደርግላቸዋል፡፡ ከአዲስ አበባ ሐረር የሚሰራ ሚኒባስ ታክሲ ያለው ግለሰቡ ቀኑን የሚያሳልፈው መኪናውን ለሹፌር ሰጥቶ ቤት ውስጥ ነው፡፡

ሣራ መስከረም 3 ቀን 2004 ዓ.ም ከንግድ ስራዋ ላይ የምትጥለው እቁብ ደርሷት ስለነበር ለቀድሞ ባለቤቱና ለልጆቹ የ5 ሺህ ብር ልብሶች ገዝታ እንድትሰጥለት ይጠይቃታል፡፡ እሷም ገዝታ ሰጥታለች፤ ምን ያደርጋል ልብስ የገዛችበትን ብር ነገ ዛሬ እሰጥሻለሁ እያለ ካቆያት በኋላ መስከረም 6 ቀን 2004 ግን ቀደም ብሎ እቤት ተዘጋጅቶ በመጠበቅ ከሥራ ቶሎ ብላ እንድትወጣ በስልክ ይጠራታል፡፡ ሀገር አማን ነው ብላ ሥራዋን ቶሎ ጨርሳ ወደ ቤቷ የገባችው ሣራ ቀደም ሲል ግዥ ባላት ልብስና በገንዘቡ ዙሪያ ይጨቃጨቃሉ፡፡ ሁኔታው አላምር ያላት ሣራ ከሳሎን ወደ መኝታ ቤት ገብታ ስልክ ለታናሽ ወንድሟ ደውላ «የድረስልኝ» መልእክቷን ታስተላልፋች፡፡ ይህንን የሰማው ተጠርጣሪው አስቀድሞ ባዘጋጀው ሽጉጥ ሁለቴ አከታትሎ ደረቷን፤ ሁለት ጊዜ ደግሞ ጡቷን ከዚያም በሁለት ጥይት እጆቿን በመምታት ገድሎ ቤት ውስጥ ያስቀመጠችውን የእቁብ ብር ይዞ ይሰወራል፡፡ ተጠርጣሪ በወቅቱ ኮንትራት ታክሲ ተከራይቶ ወደ አዋሳ ከተማ መሄዱ የታወቀ ሲሆን እስካሁን ድረስ በሀረር ፖሊሶች እጅ እንዳልገባ ታውቋል፡፡

*****

## የዮዲት ታሪክ

ወ/ሮ ዮዲት አሰፋ ከተጠርጣሪ ባለቤቷ የፌደራል ፖሊስ ባልደረባ ኮማንደር ግርማ ሞገስ ጋር ትዳር የመሰረተችው በ1995 ዓ.ም ነው፡፡ በትዳራቸውም አንድ ሴት ልጅ ያፈሩ ሲሆን ነጋ ጠባ ጠብ ያልተለየው ትዳር በመሆኑ ገና በተጋቡ በስድስት ወራቸው ይጣሉ ነበር፡፡ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአካውንቲንግ ድግሪ ያገኘችው ዮዲት በትዳሯ ውስጥ ሁሌም ያለው ጭቅጭቅና አለመግባባት ሲያይል ቤቷን ትታ ከ4 ዓመት በፊት አባቷ ቤት ተቀምጣ ነበር፡፡ ጉዳዩ በሽማግሌዎች ተይዞ እንዲለያዩ ቢወሰንም በእሱ ጠያቂነት ታርቀው በአንድ ቤት መኖር ጀምረው ነበር፡፡ ደግሞ ፍቅራቸው ብዙም ሳይዘልቅ ወዲያው ተጣልተው በፍ/ቤት ፍቺ ይፈፅማሉ፡፡ በፍቺው መሠረት ለልጃቸው ተቆራጭ እያደረገ ዮዲት ማሳደግ ብትጀምርም በተደጋጋሚ እየመጣ ልጁን ልውሰደው እያለ ማስፈራራቱ አልቀረም፡፡ ዛቻና ማስፈራራቱ ደግሞ መንግስት ለደህንነት ብሎ ባስታጠቀው መሳሪያ የታጀበ ሲሆን በተደጋጋሚ ያደረገውን ዛቻ «ለህይወቴ ያሰጋኛል» በማለት ዮዲት ለፖሊስ በማሳወቋ በፖሊስ ይያዛል፡፡ ብዙም ሳይቆይ ግን በ1000 ብር ቅጣት ይለቀቃል፡፡ በዚህ ቂም የያዘው ተጠርጣሪው ሰኔ 18 ቀን 2003 ዓ.ም ሱማሌ ተራ ከሚገኘው የአባቷ ቤት የዘጠኝ ዓመት ልጇን ወደ ት/ቤት ለማድረስና በዚያው ወደ መ/ቤቷ ለመሄድ የወጣችውን ዮዲትን መከታተል ይጀምራል፡፡ ልጇን ት/ቤት ልካ ወደ መ/ቤቷ ለመሄድ ተክለሃይማኖት አደባባይ ጋር ታክሲ ቆማ ስትጠብቅ ተጠርጣሪው በያዘው የመንግስት መሳሪያ ተኩሶ ጭንቅላቷን በመምታት ገሏታል፡፡ ተጠርጣሪ ተይዞ ፍርድ ቤት የቀረበ ሲሆን ለጥቅምት 23 ቀን 2004 ዓ.ም ተቀጥሯል፡፡

## የሃናስ ታሪክ

ሃና ላላንጉ የ16 ዓመት ወጣትና የኢን ኢንተርናሽናል ት/ቤት ተማሪ ነች፡፡ ባለፈው ዓመት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ሆና ት/ቤቱን የተቀላቀለችው ሃና ዘንድሮ የ10ኛ ክፍል ትምህርቷን መከታተል ከጀመረች ገና አንድ ወር እንዳልሞላት ቤተሰቦቿ ይገልፃሉ፡፡ በሃና ላይ የደረሰውን ጥቃት መንስኤ በተለመከተ ሁለት አይነት መግለጫዎች ሲነገሩ ከርሟል፡፡ አንዳንዶች ‹ሃና የተደፈረችው ሺሻ ቤት ነው › ሲሉ ሌሎች ደግሞ በታክሲ በሀይል ታፍና ተወስዳ ነው ይላሉ፡፡

መስከረም 21 ቀን 2007 ዓ.ም በተለመደው አኳኋን ወደ ት/ቤት ያመራችው ሃና እስከ ቀኑ 9 ሰዓት ተኩል ድረስ እንደማንኛውም ተማሪ ትምህርቷን ስትከታተል ቆይታ ነው ወደቤቷ ለመሄድ የወጣችው፡፡ አየር ጤና አካባቢ ከሚገኘው ትምህርት ቤቷ ወደ ጦር ኃይሎች ለመጓዝ ታክሲ የተሳፈረችው ሃና ከፊት ለፊቷ መጥቶ የቆመው ሚኒባስ ታክስ ሾፌሩን ጨምሮ አምስት ሰዎችን ያሳፈረ ነበር፡፡ በታክሲ ውስጥ ስለተሳፈሩት ሰዎችም ምንም ግንዛቤ ያልነበራት ሃና መውረጃዋ ጦር ኃይሎች ጋር ስትደርስ ግን ‹ወራጅ አለ› ስትል የተሰጣት ምላሽ ጩቤ በማውጣት ማስፈራራት ነበር፡፡ በታክሲ ውስጥ የተሳፈሩት አምስት ጎረምሶች ሃናን አስፈራርተው ወደ አንደኛው ተሳፋሪ መኖሪያ ቤት በመውሰድ ለተከታታይ አምስት ቀናት እየተፈራረቁ እንደደፈሯት ነው ሪፖርተር ጋዜጣ የፖሊስ ሪፖርት ጠቅሶ የዘገበው፡፡

በዕለቱ ወደ ቤት በተለመደው ሰዓት ያለመምጣቷን የተረዱት ቤተሰቦቿ ጉዳዩን ያውቃሉ ወደተባሉ ጓደኞቿ ሄዱ፡፡ ማንም እናውቃለን ያለ አልነበረም፡፡ ጉዳዩን ለፖሊስ ካሳወቁ በኋላ ፖሊስ ትምህርት ቤቷ ድረስ በመሄድ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል የተባሉ ሶስት ተማሪዎችን የፍርድ ቤት ማዘዣ በማውጣት ወደ ጣቢያ በመውሰድ ምርምራ አደረገ፡፡በዚህ መሀል ልክ በአስራ አንደኛው ቀን ሃና ጦር ኃይሎች ሙሉ ወንጌል ቤተክርሲቲያን አካባቢ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባት ተጥላ መገኘቷን አባቷ አቶ ላላንጎ ይነገራሉ፡፡ቤተሰቦቿም ልጃቸውን ከወደቀችበት አንስተው መጀመሪያ ወደ አለርት ከዚያም ወደ ዘውዲቱ ሆስፒታል በመውሰድ ህክምና እንድታገኝ፡፡

ሃና በቤት ውስጥ ታግታ ያ ሁሉ ግፍ ሲፈፀምባት ከደፋሪዎቹ በአንዱ ስልክ ለጓደኛዋ ደውላ ስለነበር ጓደኛዋ የሞባይል ስልክ ቁጥሩን ለፖሊስ በመስጠት የመጀመሪያ ተጠርጣሪና ግብረ አበሮቹ የሚኒ ባስ ሾፌሩን ጨምሮ በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ሃና በህክምና ላይ እያለችም ፖሊስ ተጠርጣሪዎችን ሆስፒታል ድረስ በመውሰድ ከሌሎች ተጠርጣሪዎች መሀል አድርጎ በማሳየት እንድትለያቸው መደረጉን አባቷ አቶ ላላንጎ አየይሶ ለቁም ነገር መፅሔት በሰጡት ቃለ ምልልስ ገልፀዋል፡፡ ሃና የደረሰባት ጉዳት ግን ከባድ ስለነበር በ18ኛው ቀን ላይ ከዚህ ዓለም በሞት ትለያለች፡፡ ሀና ጥቃቱ ከተፈፀመባት በኃላ ቤተሰቦቿ በየሆስፒታሉ ቢንከራተቱም ህክምና ያገኘችው ከአራት ቀናት በኋላ መሆኑ ለሞቷ መፋጠን አስተዋፅኦ እንደነበረው አቶ ላላንጎ ተናግረዋል(ቃለ ምልልሱን በገፅ 8 ላይ ይመልከቱ)፡፡ መንግስት አጥፊዎችን ህግ ፊት ለማቅረብ ሃላፊነት እንዳለበት ሁሉ የህክምና ተቋሞቻችንን የአገልግሎት አሰጣጥ ሊፈትሽ እንደሚገባ ሁኔታው ያመለክታል፡፡

አሁንም ጉዳዩ ወደ መገናኛ ብዙሃን ሲወጣ ድርጊቱን ለማውገዝ የዘገየ የለም፡፡ በማህበራዊ ድረ ገጾች ላይ የዚህን ድርጊት ፈፃሚዎች እንደተለመደው ‹አውሬዎች› መባሉ አልቀረም፡፡ በተለመደው ሁኔታም በራስ ሆቴል ሃናን መነሻ ያደረገ አንድ የምክክር ስብሰባ ባለፈው ሰኞ ተካሂዷል፡፡ በማህበራዊ ድረ ገጾች ላይም በተለይም ህዳር 13 ቀን 2007 ዓ.ም ሃና የምትታሰብት ቀን እንዲሆንና ‹ፍትሕ ለሃና› በሚል መርህ የፀረ ሴት ልጅ ጥቃት ዘመቻ በአንዳንድ ተቆርቋሪዎች አስተባባሪነት ተካሂዷል፡፡

በሃና ላይ ያንን የመሰለ ግፍ የፈፀሙት ተጠርጣሪዎች ከሳምንት በፊት ፍርድ ቤት በቀረቡበት ወቅትም ቁጥሩ ቀላል የማይባል ሰው በፍርድ ቤቱ ደጃፍ ተገኝቶ ቁጣውን በወጣቶቹ ላይ ገልፆአል፡፡ፖሊስ ምርምራዬን አላጠናቀቅሁም በማለቱም ተጨማሪ የ10 ቀናት የጊዜ ቀጠሮ ተሰጥቶታል፡፡

ከቀደሙት ጥቃቶችና ከልምዳችን ተነስተን ነገሩን ስንፈትሽ የሃና ጉዳይም ከቀናት በኋላ ይረሳና መደበኛው ህይወት ይቀጥላል፡፡ የሴት ልጅ ጥቃት ጉዳይ በመገናኛ ብዘሃንም ሆነ በማህበራዊ ድረ ገጾች

ላይ ትኩረት ተሠጥቶት የሚዘገበው ጥቃቶች ሲደርሱ ነው፡፡ ከእንደዚህ አይነት ዘግናኝ ጥቃቶች በኋላ ለድርጊቱ መፈፀም መነሻ ሊሆኑ ይችላሉ ስለሚባሉ ስነ ልቦናዊም ሆነ ማህበራዊ ችግሮች መድረክ ተከፍቶ ወጣቶች ከእንደዚህ አይነት የሀይል ተግባራት ራሳቸውን እንዴት ገትተው በውይይትና በንግግር መፍታት እንደሚችሉ ውይይት አይደረግም፡፡

በተለይም አብዛኛዎቹ ጥቃቶች የሚፈፀሙት በፍቅር ግንኙነትና በትዳር ውስጥ መሆኑን ስንመለከት በዚህ ዙሪያ ሰፊ የቤት ስራ ይጠብቀናል፡፡ እንደ መንግስትም እንደማህበረሰብም በፍቅር ግንኙነት መሀል የሚኖሩ አለመግባባቶች እንዴት እንደሚፈቱ ወይም እንዴት መፈታት እንዳለባቸው በማህበረሰብ ሳይንስና በሥነ ልቦና ባለሙያዎች የታገዘ ተደጋጋሚ የውይይት መድረክ እንደሚያስፈልግ ቁም ነገር መፅሔት በተደጋጋሚ አሳስባለች፡፡ በተለይም የፍቅር ግንኙነት የሚጠነሰሰውና የሚያድገው ከትምህርት ቤት ጀምሮ በመሆኑ ተማሪዎች ከዕድሜ እኩዮቻቸውና ከከንፈር ወዳጆቻቸው ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት እንዴት ሰላማዊና ጤናማ መሆን እንዳለበት ስልጠና መሰጠት እንዳለበት እናምናለን፡፡

## የሴቶች ማህበራት ሚና

የሃና ጉዳይ ሰሞኑን መነጋገሪያ ከሆነ በኋላ በየማህበራዊ ድረ ገፆችም ሆነ በመገናኛ ብዙሃን ላይ የሚደመጠው ነገር በድርጊቱ ፈፃሚዎች ላይ መወሰድ ስላለበት የፍርድ ሂደት ነው፡፡ መንግስት አጥፊዎችን የሚቀጣበት የተፃፈ ህግ ያለው በመሆኑ ከፍርድ በፊት አስተያየት መስጠት ጣልቃ እንደመግባት ሊያስቆጥር ይችላል፡፡ ነገር ግን የዚህ አይነት አስከፊ ጥቃቶች ዳግመኛ በሴት እህቶቻችን፤ልጆቻችንና እናቶቻችን ላይ እንዳይደገም ሰፊና መሰረታዊ ሊባል የሚችል ትምህርት መስጠት መጀመር አለብን፡፡

የኢትጵያ አየር መንገድ የበረራ አስተናጋጅ የነበረችው የአበራሽ ጥቃት አደባባይ በወጣበት ወቅት በሸራተን አዲስ ሆቴል በሴቶች ማህበራት ቅንጅት አንድ ህዝባዊ ስብሰባ ተካሂዶ ነበር፡፡ በዚያ ስበሰባ ላይ የአቋም መግለጫ ወጥቶ የነበረ ሲሆን በዛ የአቋም መግለጫ ላይ ‹መንግስት ለሴት የጥቃት ሰብሰባዎች ፈንድ እንዲያቋቁምና እንዲረዱ ሊደረግ ይገባል› የሚል ለቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ጥያቄ ቀርቧል፡፡

ቁም ነገር መፅሄት በወቅቱ ይህንን ሀሳብ ኮንናለች፡፡ የሴቶች ጥቃት ቋሚና በየጊዜው የሚከሰት እንደሆነ በማሰብ ፈንድ ይቋቋም ማለት የጥቃቱን ቀጣይነት አምኖ እንደመቀበል ይቆጠራል፡፡ የሴቶች ጥቃት በትምህርትና በግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች የሚቀየር መሆኑን መርሳት ተገቢ አይደለም፡፡ መንግስት ለተጠቂ ሴቶች እንዲመድብ የሚጠየቀውን ፈንድ ለግንዛቤ ማስጨበጫ ቢውል በቀጣይነት የሴት ተጠቂዎች ቁጥር አይኖርም ወይም በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል፡፡ይህ ሃሳብ ዓመታትን ቆጥሮ ባለፈው ሰኞ በራስ ሆቴል ለሃና በተዘጋጀው ፕሮግራም ላይ ድጋሚ የአቋም መግለጫ ሆኖ ወጥቷል፡፡ ጥያቄውንም ለጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ እንደሚላክም ተጠቁሟል፡፡አቶ ኃ/ማርያም ጥያቄውን ከአቶ መለስ በተለየ መንገድ ይመለከቱታል ወይ የሚለውን ጥያቄ ወደ ጎን ትተን የሴቶች ማህበራት አሁንም በአስተሳሰብ ለውጥ ላይ አተኩረው መስራታቸውን እንደዋነኛ ግብ አድርገው ሊወስዱት እንደሚገባ የዘነጉት ይመስላልና ሁኔታውን ከዚህ አንፃር መመልከት ያስፈልጋል እንላለን፡፡

## የመገናኛ ብዙሃን ሚና

መገናኛ ብዙሃን ቋሚና ተከታታይ ስራን በሴቶች ና በወንዶች የፍቅር ግንኙነት ዙሪያ ከመስራት ይልቅ ጥቃት በደረሰ ጊዜ ለአየር ሰዓት መሙያ ብቻ የሚጠቀሙበት እየሆነ መጥቷል፡፡ ሰሞኑን ከሃና የሃይል ጥቃት ጋር በተያያዘም የታየው ነገር ተመሳሳይ ነው፡፡የሃና አባት አቶ ላላንጎም አንዳንድ መገናኛ ብዙሃን በልጃችን ሞት የደረሰብን ሀዘን ገና ሳያጠግግ እኛ ያላልነውን ነገር ለህዝብ እያስተላለፉ ሌላ መከራ ውስጥ ከተውናል ሲሉ ቅሬታቸውን ገልፀዋል፡፡

የሴት ልጅ ጥቃት የአንድ ወቅት ዜና ከመሆን ባለፈ መልኩ መሰረታዊ ችግሩ ላይ ያተኮሩ ፕሮግራሞች ሲቀርቡ አይታይም፡፡ ከዚህ አንፃር ለአውሮፓ እግር ኳስ ከተመደበው አየር ጊዜ ሲሶውን እንኳ በመመደብ ስለ ጤናማ የፍቅር ግንኙነት፤ ስለ ጤናማ ቤተሰብ ምስረታ፤ አለመግባባትን በፍቅረኞች መሀል እንዴት መፍታት እንደሚቻል ወዘተ ማቅረብ የነገውን ትውልድ መታደግ እንደሆነ ለመጠቆም እንወዳለን፡፡

ህብረተሰቡም በየአካባቢው የሚመለከተውን የሴት ልጅ ጥቃት በምን ያገባኛል ስሜት ሳይመለከት በጋራና በተናጠል መዋጋት አለበት፡፡ ዛሬ መንገድ ላይ አንዲት ሴትን ሲጎትት የምንመለከተው ጎረምሳን አይተን እንዳለየ ፊታችንን ካዞርን ነገ የምትጎተተው የራሳችን ልጅ ወይም እህት እንደሆነች መዘንጋት አይገባም፡፡ ሃናን እየጎተቱ ወደ ቤት ሲያስገቧትና እየተፈራረቁ ሲደፍሯት አይተው እንዳላየ የሆኑ ጎረቤቶች ስለመኖራቸው አባቷ አቶ ላላንጎ እንባ እየተናነቃቸው የተናገሩትን መዘንጋት አይገባም፡፡ ይህ እስካልተጀመረ ጊዜ ድረስ ግን ሌላ ሄርሜላ፤ ሌላ ካሚላት፤ ሌላ አበራሽ፤ሌላ ፍሬህይወትና ሌላ ሃናን ማጣታችን አይቀርም...

# ያረጋል...

ከገፅ 11 የዞረ ...

ላይ እና የፅሁፍ መልዕክትም ላይ የተመልካቹ ምላሽ በጣም የሚገርም ነው፡፡ ለዚህም ነው ጥሩ ፕሮግራም ስለሆነ ኢቲቪ እየደገመው ያለው፡፡ በጣም የሚገርመው ግን ኢቲቭ3 ላይ አንድ ዓመት ሙሉ ሲተላለፍ በራሴ ብቻ ነበር ወጪው የሚሸፈነው፡፡ ምንም ስፖንሠር አልነበረውም፤ ምንአልባት ሁለት ሦስት ማስታወቂያ ገብቶ ሊሆን ይችላል፤ በስፖንሠር ደረጃ አይታሠብም፡፡ አንዳንዴ የእኛም የስፖንሠርሺፕና የማስታወቂያ ባህሪያችን እከክልኝ ልከክልህ አይነት ነው፡፡ ወደ ኢቢኤስም ስንመጣ እንደዚያው፡፡ እና በኪሣራ የምንሠራው ሥራ ነው፤ ግን እንደ ሚዲያ ደግሞ ብዙ ተመልካች ሲኖረውና ማህበራዊ ኃላፊነቴን እየተወጣሁ ነው ብለህ ስታስብ ኩራት ይሠማሀል፡፡

**ቁም ነገር፡-አንዳንድ ጊዜ ማህበረሠቡን የሚያስቆጡ የሀና አይነት አደጋዎች ሲፈጠሩ አብዛኛው ሠው ሚዲያውን ወደ መውቀስ ይመጣል፡፡ይህስ ምን ያህል የሚያስማማ ነው ?**

*ያረጋል፡-* ምን መሠለህ፤ ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ ነውበቃ፡፡ምንምጥያቄየለውም፡፡ነገሮችከመፈጠራቸው በፊት ነው ግንዛቤ ማስጨበጥ ላይ መሰራት ያለበት፡፡ ለምሳሌ የካሜራ ትኩረት የሚለው ፕሮግራማችንን እኔ ነኝ ያለ የሚመለከተው አካል በቋሚነት በጀት መድቦ ግንዛቤ ለመፍጠር ሊጠቀምበት የሚገባ ፕሮግራም ነበር፡፡ ያለውን ጉልበት ልነግርህ አልችልም፡፡ ከገጠር ሁሉ እየተደወለ ‹ይሄ እኮ ነው የማህበረሠባችን ባህሪይ› ይባላል፡፡ ሚዲያውማ እንዲያውም በሌለው አቅም ማድረግ የሚገባውን ነገር እያደረገ ነው፡፡ ለሥብሠባና ዓመታዊ በጀት መዝጊያ ምናምን ተብሎ'ኮ ወደ ሀዋሳ፤ ወደ ባህርዳር ተሂዶ አዳራሽ ላይ መዓት ብር ይወጣል፡፡ ከዚህ ገንዘብ ላይ አንዷን ነገር ስፖንሠር የማድረግ፤ የማበረታታት ነገር መኖር አለበት፡፡ ግን ከቁጥጥር ውጪ ሆኖ እንዲህ አይነት ጉዳት ሲፈጠር ሚዲያው ላይ መጠቆም ተለምዷል፡፡ አሁን የሀናን ጉዳይ ካሜራ ይዘን ብንቀርፀው እናገኝ የነበረው ነገር ተመሣሣይ ነው፡፡ ሠዉም አየት አድርጎ ማለፉ አይቀርም ነበር፡፡

**ቁም ነገር፡- ኮንታክት መልቲሚዲያ የሚያዘጋጀው ፕሮግራም በተገቢ መንገድ ማህበረሠቡ ላይ የአስተሣሠብ ለውጥ አምጥቷል ብለህ ታምናለህ?**

*ያረጋል፡-* በእርግጠኝነት፡፡ በፕሮግራማችን ላይ አላፊ አግዳሚው ትክክለኛ ባህሪውን የሚያይበት ስለሆነ በእነርሡ እንደገና በሚሊየን የሚቆጠሩ ሰዎች ራሳቸውን ስለሚያዩ ጥሩ ነገር ሠርተናል ብዬ አስባለሁ፡፡ በፌዴራል ፖሊስ ደረጃ ፕሮግራማችን ስብሰባ ላይ የተነሳበት አጋጣሚ እንዳለ ጓደኛዬ ነግሮኛል፡፡ ‹እንዲህ አይነት ፕሮግራም አይታችኋል? የእኛ ማህበረሠብ እንዲህ አይነት ነው፡፡ ሴት ልጅ እንዲህ ስትሆን፤ መንገድ ላይ የመንግስት ንብረት ሲቆረጥ ከስንት አንዱ ነው ወደ ህግ መሄድ አለበት የሚለው› ተብሎ ተነስቷል፡፡ ሚዲያው ዕውቀቱ አለው፤ ማሠራጫው አለው፤ በገንዘብ ግን መደገፍ አለበት፡፡ ከእኛ ፕሮግራም አንፃር እንደ አዲስ የኢትዮጵያ ፕራንክ ሾው አመላካች ነገር አሣይተናል፡፡ ግን ከዚህ የበለጠ ሊሠራበት እንደሚችል እናምናለን፡፡

**ቁም ነገር፡- አመሠግናለሁ**

# ሙሉ...

ከገጽ 36 የዞረ

**ቁም ነገር፡- ከሀሳብና ቁስ የቱ ይቀድማል?**

ሙሉ፡- ይሄ እንግዲህ የዶሮዋና የእንቁላሉ አይነት ታሪክ ነው፡፡ ዶሮዋ ናት ወይስ እንቁላሉ ነው የሚቀድመው እንደማለት ነው ፡፡ አሁን አንቺ ምግብ መብላት ስታስቢ ሃሳብ ነው፡፡ ጠረቤዜዛ ኖሮኝ ምግቡን እዚህ ላይ አስቀምጬ ብበላ ብትይ ይህም ሀሳብ ነው፡፡ ከዛ በሃላ ነው ወደ ተግባር የሚለወጠው፡፡ እንደገናደግሞ ተግባሩን በማየት ወደሃሳብ ይለወጣል፤ ይህም ጠረቤዜዛው ስላጠረ ባስረዝመው ማለት ይመጣል ማለት ነው፡፡ ይሄ መፍጠርና እንደገና የፈጠሩትን ማሻሻል ይባላል፡፡ ነገር ግን እንደኔ የዶሮዋ አይነት ታሪክ ይሁን እንጂ ሀሳብ ነው የሚቀድመው፡፡ ገንዘብ ፣ ሀብት ሁሉንም ብገል መጀመሪያ ሃሳብ ማሰብ ያስፈልጋል፤ ገንዘብም ፣ንግድም ፣ፖለቲካም ሁሉም ከሀሳብ ነው የተፈጠሩት፡፡

**ቁም ነገር፡- ከፍተኛ ወጪ አውጥተሽ የገዛሽው ነገር ምንድን ነው?**

ሙሉ፡- እኔንጃ!! መጽሀፍ ወይም መኪናም ሊሆን ይችላል!! ግን በፊት ወርቅ ገዝቼ ነበር፤ እንግዲህ እሱ ያኔ ከፍተኛው ነው፡፡ 30 ሺህ ብር ነው የገዛሁት፡፡ እሱንም አንዲት ሴት ቤት ለመስራት መሬት ወስዳ በእዳ ተቸግራ ንብረቷን ሊወስዱባት ሲሉ፤ መጥታ ገንዘብ ስትጠይቀኝ በወቅቱ ገንዘብ ስላልነበረኝ በጣም በርካሽ ዋጋ ሸጬ ሰጠሁዋት፡፡ ሌላው አንዳንድ ጊዜ አውጥቼ ልገዛ እችላለሁ፤ ግን እኔ ይሄ ትልቅ ወጪ ነው ብዬ አላስታውሰውም፡፡

**ቁም ነገር፡- 8100 A ላይ ስንት ጊዜ ላክሽ?**

ሙሉ፡- እኔንጃ አላውቅም!! አስቤው ሳይሆን የምልከው ድንገት መልዕክቱ ሲደርሰኝ በዛው እልካለሁ፡፡ ወይም አንድ ጊዜ ቦንዱን እገዛ እንደሆን አላውቅም፡፡ ግን መኪና ለመሸለም ብሎ መላኩ ጥሩ ነው፡፡

**ቁም ነገር፡- በሴሎች ስራዎች መወጠርሽ ከኪነጥቡ አያርቅሽም?**

ሙሉ፡- አላራቀኝም! ቴአትሮችን አንዳንዴ ሲመቸኝ እከታተላለሁ፡፡ መጽሐፍ ሲመረቅ እሄዳለሁ፡፡ የራሴን መጽሐፍ ፣ ግጥሞች ፣ የፊልም እስክሪፕቶች የፃፍኳቸው አሉ፤ በእናቴም ህመም ምክንያት ለእሷ ጤና ቅድሚያ መስጠት ስላለብኝ ዘገየ እንጂ የሰራኋቸው ስራዎች አሉ፡ ፡ አንዳንዴም ውጥረት አለ፤ እኔ ከሌላው ሰው ተለይቼ 72 ሰዓት የተሰጠኝ የሚመስለው አለ፡፡ ለምሳሌ በአንድ ቀን ውስጥ 20 የግብዣ ደብዳቤ ይደርሰኛል፡፡ 20ውም ጋር መድረስ አስቸጋሪ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ጠዋት ጥቁር በጥቁር ለብሼ አልቅሼ ቀብሬ ከሰዓት በኋላ ደግሞ ነጭ የምለብስበት ጊዜ አለ፡፡ አልቃሽና ዘፋኝ ሆኜ እውላለሁ፡፡ በዚህ የተነሳ ዘገየ እንጂ ከኪነጥበቡም አልራቅኩም፡፡

**ቁም ነገር፡- በጣም ብዙ መድረኮች ላይ ትታያለሽ፤ ጊዜ ተርፎሽ ነው? ወይስ ጠሪ አክባሪ ነው በማለት ነው የምትሄጂው?**

ሙሉ፡- አንደኛው ጠሪ አክባሪ ነው፡፡ ሁለተኛው ብዙ ጊዜ ሴቶች ናቸው ፕሮጀክቱን የሚሰሩት፡፡ አነስተኛና ጥቃቅን ሄጄ እኔ ድጋፍ ካላደረኩኝ ሁሉም ትልቅ ነኝ እያለ አይገኝላቸውም፡፡ ትልቅነት ደግሞ ዝቅ ብሎ ትንንሾች ጋር መገኘትና ትሁት መሆን ነው፡፡ አሁን እኔ አንዳንድ ጊዜ የቀበሌ ሴቶች፤ አካል ጉዳተኞች ፣ ትንንሽ ህፃናትም ሲጠሩኝ እሄዳለሁ፡፡ ትመጣለች ብለው ስለማይጠብቁ ሲደነግጡ እመለከታለሁ፡፡ ሁልጊዜ ሸራተንና ሂልተን ብቻ ትልልቅ ቦታዎች እንገኝ የምንል ከሆነ እንደኔ ይህ በሽታ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ትልቅ ነኝ ብሎ ራስን መቆለል ጤነኛ አመለካከት አይደለም፤ እንደውም ታዋቂ ስንሆን የበለጠ ትሁት መሆንና ዝቅ ብለን የሰዎችን ሁኔታ ማዳመጥ ያስፈልጋል፡፡

**ቁም ነገር፡- እነዚህ ምግቦች ከምን ይዘጋጃሉ፤ ቡርሳሜ ፣ ጥህሎ ፣ እልበት?**

ሙሉ፡- ቡርሳሜ ያልሸኝንና ሁለተኛውንም አላውቀውም፡፡ እልበት ግን ከባቄላ ወይ ከአተር ሊሆን ይችላል፤ በደምብ ጸድቶ ይፈጫል፤ ሰናፍጭ፤ የሱፍ ውሃ፣ ነጭ ሽንኩርት ተጨምሮበት ይዘጋጃል፡፡

**ቁም ነገር፡- በሕይወትሽ ትልቅ ትርጉም የምትሰጭው ነገር ምንድን ነው?**

ሙሉ፡- በሕይወቴ ትልቁ ትርጉም የምሰጠው ነገር ለሰዎች ኖሮ ማለፍን እና እውነትን መከተል ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች ለራሳቸው ብቻ ይኖራሉ፤ እኔ ግን ለሰዎች መኖርና የአንድን ሰው ህይወት ማትረፍ በራሱ ትልቅ ዋጋ አለው ብዬ አስባለሁ፡፡ እውነትን መከተል ደግሞ ህመም አለው፤ ሊጎዳ ይችላል፤ ከውሸት በላይም የሚያስገድልበት አጋጣሚ አለ፤ ነገር ግን ሁልጊዜ ለእውነት ዋጋ እሰጣለሁ፡፡ ምክንያቱም የፈለገ ቢጎዳ ውስጤ ደስ ይለዋል፤ ማንም ሰው ባይረዳኝ እንኳን እውነት ከራስ ጋር ሲሆን ደስ ይላል፡፡ ስለዚህ ለእውነትና ለሰው ልጆች ዋጋ እሰጣለሁ፡፡

**ቁም ነገር፡- ብዙ ሰዎች ስብሰባ ይጠላሉ ስምን ይመስልሻል?**

ሙሉ፡- አዎ! ስብሰባ ብዙ ሰዎች እንደሚጠሉት ሁሉ እኔም እጠላለሁ፡ ፡ የሚጠላባት ምክንያቱ፤ አንደኛ ሰዓት አይከበርም ፣ ሁለተኛ ከአጀንዳው ውጪ የሚቃዣው ይበዛል፡፡ አንዳንዴ ከዘፍጥረት ጀምሮ አብዮቱ ፍንዳታ ላይ ይገባል፤ ትክክለኛ ነጥብ ላይ ተወርቶ በሰዓት አያልቅም፡፡ እኔ ድሮ ስብሰባ አልሄድም ነበር፡፡ አንድ ጊዜ ግን አንድ ምሁር «እናንተ ተማርን የምትሉ ሰዎች ወገኖቻችሁን ለመርዳት ፈቃደኛ አይደላችሁም፡ ፡» ይላል፡፡ ለምን ብዬ ስጠይቀው? «በደርግ ጊዜ መንግስት ምሁሮችን ስብሰባ ቢጠራቸው እምቢ ብለው ቀርተው፤ ያልተማሩ ሰዎች ከቀበሌ፤ ከሰፈርም ተሰብስበው ሄደው የቀበሌ ሊቀመንበር አስተዳደር በመሆን ነው ምሁሩን የፈጁት፡፡ ያኔ የተማሩ ሰዎች ቀበሌ ውስጥ ቢኖሩ ኖሮ ነገሩን አብራርተው ስንት ነገር ያድኑ ነበር፡፡ ካድሬውም፣ አብዮት ጠባቂውም መሀይም ነበር፡፡ አሁንም እናንተ ሄዳችሁ ሀሳብ እንኳን ማስቀየር ባትችሉ አስተያየት መስጠት ትችላላችሁ፤ ቢያንስ አዳምጣችሁ ወደፊት ምን እንደሚመጣ ብታውቁ ጥሩ ነው» ብሎ ተናገረ፡፡ ከዚያ በኋላ እኔ ጊዜ ባይኖረኝ እንኳን ተሟሙቼም ቢሆን ስብሰባ ላይ እገኛለሁ፡፡

**ቁም ነገር ፡- በወጣትነሽ ስንት ጊዜ ፍቅር ይዞሻል?**

ሙሉ፡- ምን አልባት ሁለት ጊዜ ፍቅር ይዞኛል ብዬ ልናገር እችላለሁ፡፡ የአስተዳደጌ ሁኔታ በጣም ጥብቅ ስለሆነ ፍቅር ሳይዘኝ በፊት አይገባኝም ነበር፡፡ በፊት አንድ ሰው ተነስቶ ምግብ አልበላ አለኝ፣ ልሞት ነው፣ ወደድኩሽ ፣እንዲህ ሆንኩልሽ ሲል እሳደብ ነበር፡፡ ሴቶቹ ጓደኞቼ እንደዚህ ብለው ሲያወሩኝ ምን ትጨማለቂያለሽ ብዬ እቆጣ ነበር፤ አሁንም ቢሆን የማይገባኝ ነገር አለ፡፡ ሴቶች መጥተው ይህ ሰውዬ ላይሽ ላይ ሊወድቅ ነው፡፡ ይሉኛል፤ እኔ ግን አይገባኝም፡፡ ዓይን ዓይኔን ቢያዩኝ ፣ እጄን ቢዳብሱኝ ምንም የማይገባኝ ድንጋይ ራስ ነኝ፡፡ ከወንዶችም ከሴቶች ጋር አብሬ ስለምውል፤ የትም አብሬ ብሄድ ፣ ሻይ ብጠጣ ፣ ወንድሜ ነው ፣ ጓደኛዬ ነው ብዬ ነው የማስበው፡፡ በኋላ ግን የተረዳሁት ከመረዳትም አልፎ ስለፍቅር ብዙ ማንበብ የጀመርኩት ራሴን ፍቅር ሲይዘኝ ነው፡፡ ፍቅር ከያዘኝ በኋላ ዕድለኝነቴ አንዳንድ ሰዎች አፍቅረው ያፈቀሩት ሰው ላያፈቅራቸው ይችላል፡፡ እኔ ግን በጣም ያፈቀርኩትን ሰው ነበር ያፈቀርኩት፡፡ ከዛ ስለ ፍቅር ስረዳ የሌሎችን ሰዎች ችግር መረዳት ቻልኩ፡፡ ፍቅር ያልያዘው ሰው ወይም ወልዶ የማያውቅ ሰው የሌላው ችግር አይገባውም፡፡

**ቁም ነገር፡- ወንዶች ሴትን እናት ናት፣ ሚስት ናት፣ እህት ናት እያሉ በተለያየ መንገድ ይገልጿቸዋል፡፡ አንቺ ወንዶችን እንዴት ትገልጪያቸዋለሽ?**

ሙሉ፡- እኛ አጠቃለን ከባህሉ ሳንወጣ ቀረን እንጂ ወንድ አያዝንም ማለት አይደለም ያዝናል፡፡ እንደውም አንድ ሴት ምሳሌ ስትሰጥ ሰምቻለሁ፡፡ በልጅነቷ እኩያ ከሆነው የአጎቷ ልጅ ጋር ክትባት ሊከተቡ ሄዱና እሷ ስታለቅስ ዝም አሉ፤ እሱ ደግሞ ተራው ደርሶ ሲወጋ ሲያለቅስ «አንተ ደግሞ ወንድ ልጅ አይደለህም? እንዴት ወንድ ልጅ ያለቅሳል?» አሉት፡፡ ህመሙ ግን ለሁለቱ እኩል ነው፡፡ ባህላችን ግን ወንድ ጀግና ነው፤ ቆፍጣና ነው በሚለው ስለሚገልጸው ከሴቶች የበለጠ አዝኖ እንኳን ስሜቱን ስለማያወጣው ያዘነ ላይመስል ይችላል፡፡ እኔ ግን ወንዶች እንደማንኛውም ሰው አዛኝ፣ አጋዥ ፣ ሀላፊነት የሚሰማቸው ናቸው ብዬ አምናለሁ፡፡

**ቁም ነገር፡- ከሙዚቃ ጋር ያለሽ ቅርበት እንዴት ነው?**

ሙሉ፡- እኔ ሙዚቃ በጣም እወዳለሁ፡፡ ሙዚቃ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የአርት ስራን በጣም አድናቂ ነኝ፡፡ በሙዚቃ ጎበዝ ባልሆንም ቤቴም ሆነ መኪና ውስጥ አዳምጣለሁ፡፡ የድሮዎቹንም ሆነ የአሁኑ ወጣቶች ሙዚቃዎች በጣም ያስደስቱኛል፡ ፡ እነ ቴዲ አፍሮ፣ ታደለ ገመቹ፣ ታደለ ሮባ፣ አጫሉ እና ሌሎችም የአማርኛ ፣ የትግርኛም በሌሎች ቋንቋዎች የተዘፈኑ ሙዚቃዎችን አዳምጣለሁ፡፡ ይህ የአሁን ወጣቶች የሚዘፍኑት ራፑን ራጋውንም መልዕክቱ ጥሩ ከሆነ አበረታታለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግጥሞቹ ላይ ትንሽ ጥንቃቄ መደረግ ያለበት ሁኔታ አለ፡፡ ሁልጊዜ ከዳሽኝ ከዳኹኝ መሆን የለበትም፡፡ እንደውም አንድ የቆየ ዘፈን አለ የሚገርመኝ፤

‹እባክህ አምላኬ ስጠኝና ልስጣት›
‹የምወዳትን ልጅ አለያየኝ ማጣት›

«እግዚአብሔር ለሱ ከሚሰጠውና እሱ ከሚሰጣት፤ እግዚአብሔር ለእሷ በቀጥታ አይሰጣትም እንዴ?» እላለሁ፡፡ እንዲህ አይነት ዘፈን መልዕክቱ ደካማ ነው የሚሆንብኝ፡፡ ሴቶች ገንዘብ ነው የሚፈልጉት በማለት፤ አንተ ገንዘብ ስጠኝና ልስጣት ማለት ምን ማለት ነው? እሷ የእግዚአብሔር ፍጡር አይደለችም? እግዚአብሔር ለእሷስ አይሰጣትም? ወይ እሷ አልወደደችው ይሆናል፤ እሱ ግን ገንዘብ ስለሌለኝ ነው ብሎ በራሱ የአመለካከት ድህነት የተነሳ ያንን ያስባል፤ ገንዘብም ቢኖረውም ካላፈቀረችው አላፈቀረችውም ነው፡ ፡ ስለዚህ ኪነጥበብ ትልቅ ጉልበት ያለው ስለሆነ ግጥሞቹና የሚያስተላልፏት መልዕክት ትርጉም ያዘሉ ቢሆኑ ጥሩ ነው፡፡

**ቁም ነገር፡-እመሠግናለሁ፡፡**

# ሙሉ ሰለሞን



## ‹‹አመለካከታችን ካልተለወጠ ህግ ብቻውን ሁሉን ነገር ሊያስፈፅም አይችልም››

የዛሬዋ እንግዳችን ከ30 በላይ በሚሆኑ የተለያዩ የሀገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ተቋማት እና ማህበራት በፕሬዚዳንትነት፣ በቦርድ ዳይሬክተርነት እና በአማካሪነት አገልግላለች፡፡ ለአብነትም የኢትዮጲያ ንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት፤ የራይት ቪዥን ማናጀር ፣ የዓለም ባንክ በአፍሪካ አማካሪ፤ የኢትዮጲያ ቀይ መስቀል ማህበር የቦርድ ዳይሬክተር በመሆን ሰርታለች፡፡ ወ/ሮ ሙሉ ሰለሞን በሀገራችን በአመራር ቦታ ላይ አሉ ከሚባሉት ጥቂት ስኬታማ ሴቶች አንዷ ናት፡፡ በተለያየ ጊዜም በርካታ ሽልማቶችን ለማግኘት የቻለች ሲሆን እ.ኤ.አ በ2013 የሴት መሪዎች አዋርድ / women leadership award/ ተሸላሚ ለመሆን በቅታለች፡፡ በኪነጥበቡ ዓለምም የራሷን ድርሻ እያበረከተች እያበረከተች ከምትገኘው ወ/ሮ ሙሉ ሰለሞን ጋር ካደረግነው ረጅም ቆይታ የተወሰነውን ለመሿለኪያ አምዳችን እንዲህ አቅርበናል፡፡

**ትዕግስት ታደለ**

**ቁም ነገር፡- ሰሞኑን በመገናኛ ብዙሀን እየሰማን እንዳለነው ብዙ ጊዜ ጥቃቶች በተደጋጋሚ የሚፈፀሙት ለምን ይመስልሻል?**

*ሙሉ፡-* በሴቶች ላይ የሚደርሰው በሚዲያ ጎልቶ ስላየነው እንጂ ወንዶችም ላይ ጥቃት ይደርሳል፡፡ ነገር ግን በአብዛኛው ህፃናት፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና አዛውንቶች ተጠቂዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ አዛውንቶች ገንዘብና ሀብት ኖሯቸው በአንዳንድ ወጣቶች ገንዘባቸውን ለመውሰድ ከመፈለግ ጥቃት የማድረስ ነገር አለ፡፡ የገዛ ልጃቸው ለገንዘብ ብሎ አባቱን እስከመግደል የደረሰበት ታሪኮችን ሰምተናል፡፡ ሌላው ደግሞ ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት፣ ከዘመድ ጋር የሚኖሩ፣ ወይም የራሳቸው እናትና አባት ካለማወቅ አላስፈላጊ የጉልበት ብዝበዛና ሌሎችም ጥቃቶች በቅርብ ሰዎቻቸው ይደርስባቸዋል፡፡ ሴቶች ደግሞ በአጠቃላይ ተደራራቢ ጥቃትና በደል ይደርስባቸዋል፡፡ ይህ እንግዲህ የአንድ የሁለት ሰው ጉዳይ ሳይሆን፤ የህግ መኖር ያለመኖር ጉዳይም ሳይሆን የአፈፃፀም ጉድለት ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ህጉ ጥሩ ሆኖ አፈጻፀሙ ጥሩ ቢሆንም፤ አመለካከታችን ግን ካልተለወጠ ህግ ብቻውን ሁሉን ነገር ሊያስፈፅም አይችልም፡፡ ስለዚህ ህብረተሰብ ውስጥ ለምንድን ነው ወንጀል የሚበዛው? ለምንድነው ጥቃቶች የሚበዙት? ስርቆት፣ በደል፣ ውሸት የሚበዛው ለምንድነው ተብሎ ሲታይ፤ በአብዛኛው የህብረተሰቡ የአመለካከት ችግር ውጤት ነው፡፡ አንድ ሰው በአስተዳደግ፣ በትምህርት ቤት ህይወቱ ወይም በአኗኗር ሁኔታው፣ እኛ ትንንሽ በምንለው ነገር ተጎዳሁ ይልና ራሱን መጥላት ፣ ሰዎችን መጥላት ውስጥ ይገባል፤ በዚህ ጊዜ የሚያደርገውን ነገር አያውቅም፡፡ ጸያፍ የሚባሉትን ነገሮች ለይቶ እስካለማወቅ ስሜታዊ በሚሆንበት ጊዜ አላስፈለጊ የሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም ፣ ህፃናትን ብቻ ሳይሆን እናቶቻቸውን እስከመድፈር የሚደርሱበት ጊዜ አለ፡፡ ይህ በጤናማ ህሊና ይፈፀማል ተብሎ አይገመትም፡፡ እንደዚህ አይነት ችግሮችን በህግ ብቻ ማስተካከል ይቸግራል፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው እንደዚህ አይነት መጥፎ አመለካከቶችን በአንድ ሌሊት ተምሮ አያድርም፤ በሂደት እያደገ የሚመጣ ነገር ነው፡፡ ይህን ለመለወጥ መጀመሪያ ጥፋተኞቹ ተገቢውን ቅጣት ማግኘታቸው ተገቢ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ዘለቄታዊ መፍትሄ ለማምጣት ከህፃናት መዋያ ጀምሮ፣ በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ፣ በዩኒቨርሲቲዎች እንዲሁም በተለያዩ ማህበራት የአመለካከት ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ስልጠናዎች ቢሰጡ ጥሩ ነው፡፡

አሁን ለምሳሌ የሔርሜላ ጉዳይ ከተፈፀመ 15 ዓመት ገደማ ሊሆነው ነው፡፡ ግን በዚህ 15 ዓመት ከህፃናት መዋያ ጀምሮ እስከ መንግስት ምን ተሰራ? እኛስ በሴቶች ጉዳይ ላይ ፣ በሰዎች መብት ላይ የምንሰራ ሰዎች ምን አደረግን? የሚለው ቀጣይነት ቢኖረው ኖሮ ከ5 ዓመት በኋላ ይህ ችግር ላይኖር ይችል ነበር፡፡ ግን ሁልጊዜ ችግር ሲመጣ ፤ ዘፍነን፤ ሆይ! ሆይ !ብለን ፣ ጋዜጣዊ መግለጫ ብቻ ሰጥተን የሚቆም ከሆነ ችግሮቹ አይፈቱም፡፡ ቀጣይነት ያለው መፍትሄ ካልሰራን የህብረተሰቡን አመለካከት ለውጠን ጤናማ ማህበረሰብን ካልፈጠርን ችግሩ አይቀረፍም፡፡

**ቁም ነገር፡- ፋሽን ተከታይ ነሽ?**

*ሙሉ፡-* አይደለሁም! ብዙ ሰዎች ፋሽን የምከትል ይመስላቸዋል፤ እኔ ግን አንድ ልብስ ፋሽን ቢሆን ለእኔ ካልተመቸኝ አልቀበልም፡፡ ጥሩ ከሆነ ደግሞ እጠቀመዋለሁ፡፡ አሁን ለምሳሌ ፀጉሬን ጊዜ ስለሌለኝ ታጥቤ በአንድ ፀጉር ማስያዣ ቋጥሬ ነው የምሄደው፡፡ ሰዎች ግን ‹ሁልጊዜ ያንቺ ፀጉር እንደተመቻቸ ነው፤ ዝንፍ ብሎ አያውቅም፡፡ ፀጉር ሰሪሽ በየቀኑ ጠዋት ጠዋት ትመጣልሻለች?' ብለው ይጠይቁኛል፡፡ ልብስሽን ማነው ዲዛይን የሚያደርግልሽም ይሉኛል፡፡ እኔ ግን ፀጉሬን የማስይዘው ራሴ ስሆን፤ ልብሱንም ከሸሮሜዳ ፣ ከመርካቶ፤ ከተገኘበት ቦታ ነው የምገዛው፡፡ አንድ ሰው ስራውን ካከበረ ፣ ለራሱ ጥሩ ግምት ካለው፤ ለዛ ፕሮግራም ተገቢውን ልብስ ለብሶ መገኘት አለበት፡፡ እኔ ብዙ ጊዜ ፕሮግራሞች ላይ የኢትዮጵያን የባህል ልብስ የምለብስበት ምክንያት አለኝ፤ ለመዘነጥ ብቻ ብዬ አይደለም፡፡ አንድ ጊዜ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ አንድ የሆነች ጓደኛዬ ፕሮግራም ነበራት፤ እዛ ፕሮግራም ላይ እኔን እና እህቴን ጠርታን፤ በእለቱ ሰዓት ስለደረሰብን እቤት ሄደን ልብስ ከምንቀይር ወደ ፕሮግራሙ በጊዜ ሄደን ስራ ብንረዳ ይሻላል በማለት በለበስነው ልብስ ሄድን፤ ለካ በነገሩ እሷ ተቀይማለች፡፡ ካለፈ በኋላ ምነው ብለን ብንጠይቃት ‹አንቺም እህትሽም ለእኔ ፕሮግራም ክብር አልሰጣችሁትም፤ ዝቅ አድርጋችሁ ነው ያያችሁት፤ ስንት የሀበሻና የፈረንጅ ልብስ እያላችሁ በጅንስ ሱሪ የመጣችሁት › አለችኝ፡፡ ከዛን ቀን ጀምሮ እኔ ሰፈር እንኳን ፀበል ቅመሽ ቢሉኝ የሀበሻ ቀሚስ ለብሼ ነው የምሄደው፡፡ አንዳንዴ በሀበሻ ቀሚሶቼ ላይ የራሴን ዲዛይንና የቀለም ምርጫ ስለምጠቀም እንዲሁም ትናንሽ ተዛማጅ ነገሮችን ስለምጠቀም ሰዎች ፋሽን የምከተል ይመስላቸዋል፡፡ ወይ ደግሞ ሻሼን ፀጉሬ ላይ ቋጥሬ ባርኔጣ አስመስለዋለሁ፤ ቀላልና ግልፅ የሆነ ነገር ነው የምጠቀመው ፤ የሚያምረውም እንደዛ ሲሆን ነው፡፡

**ቁም ነገር፡- ስንት የሀበሻ ቀሚሶች አሉሽ?**

*ሙሉ፡-* ውይ!! አላውቅም፡፡ ሀበሻ ቀሚሶቼን በተመለከተ ሌላ ሰው ነው ተጠያቂ!! እኔ ለእርዳታ ነበር የምሰጠው፡፡ ማንኛውም ልብሴን ከለበስኩት በኋላ ይቀመጥና በዓመቱ መጨረሻ ላይ ለእርዳታ እሰጠዋለሁ፡፡ ነገር ግን በሆነ አጋጣሚ የስራ ባልደረባዬ ሊሰጥ የተቀመጠ የሀበሻ ቀሚሶች አይታ የሀበሻ ቀሚስ አይሰጥም ይቀመጥ ጥለቱ አይገኝም አለች፡፡ እውነትም በፊት ከ30 እና 40 በላይ የሰጠኋቸው የሀበሻ ቀሚሶች አሁን ላይ ጥበባቸው አይገኝም፡፡ ባስቀምጠው ኖሮ የጥንት ከአያቴ ጀምሮ የነበሩ ጥበቦች አይጠፉም ነበር፡፡ ከዛ በኋላ ግን የሀበሻ ቀሚሶችን ማስቀመጥ ጀመርኩ፡፡ ቁጥሩን ግን በውል አላውቀውም፤ ወይ እንግዲህ ወደፊት እቆጥረው ይሆናል፡፡